# የከተሞች መልካም አስተዳደር ኘሮግራም

## (ተሻሽሎ የፀደቀ)

የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


መግቢያ …………………………………………………………………………… 1

የመልካም አስተዳደር መሠረተ ሃሳብና የመልካም አስተዳደር ሁኔታ በኢትዮጵያ ከተሞች

I. የከተማ የመልካም አስተዳደር መሠረተ ሃሳብ …………………………………………... 5

II. የኢትዮጵያ ከተሞች የመልካም አስተዳደር ገጽታ ……………………………………….. 9

ክፍል ሁለት

የከተሞች የመልካም አስተዳደር ኘሮግራም

I. የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ኘሮግራም የፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫዎች …… 19

II. የከተሞች የመልካም አስተዳደር ኘሮግራም ጥቅል ዓላማዎችና ግቦች ……………………... 20

III. የከተማ የመሬትና ኘላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም ……………………………….. 22

IV. የታክስና ፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም ……………………………………… 32

V. የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ ኘሮግራም …………………………………………………… 39

ክፍል ሦስት

የአመራር ሥርዓት፣ ፋይናንስና መርሃ ግብር

I. የኘሮግራም አፈፃፀም አቅጣጫዎች ………………………………………………………… 48

II. የፋይናንስ ፍላጐት ……………………………………………………………………… 55

III. የአፈፃፀም መርሃ ግብር ……………………………………………………………….. 56

*መ□ቢ□*

*አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕ□ብ አሁንም ድረስ በገጠር የሚኖር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የከተሞች መስፋፋት □□□ ፈጣን መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: በአሁኑ □□ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙና ቁጥራቸው ወደ አንድ ሺህ የሚጠጋ ከተሞች ያሉ ሲሆን፣ የከተማ ነዋሪ ሕ□ብ □መ□ዊ የዕድገት መጣኔም ከፍተኛ እንደሆነ □□መ□ል:: ነገር ግን ከተሞቻችን ለረ□ም □□ ተ□ቢ□ን ትኩረት ሳያገኙ በመቆ□ታቸው በሃ□ራዊ□ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና ሳይወጡና ለነዋሪዎቻቸውና በአካባቢያቸው ላሉ የገጠር ነዋሪዎች ሊሰጡ የሚገባቸውን ዓቅም ሳ□ስ□ኑ ቆይተዋል:: በመሆኑም የሃ□ሪቱ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ በቂ የመኖሪያ ቤቶች፣ □መሠረተ-ልማት አውታሮች፣ የሥራ ዕድሎች በበቂ ሁኔ□ የሚገኙባቸው አካባቢዎች ሳይሆኑ ቆይተዋል::*

*ፈጣን ልማት በዘላቂነት ማስመዝገብ የሚቻለው በከተሞቻችን መልካም አስተዳደር ሲሰፍን እንደሆነ ግልጽ ነው:: ይህንን እውን ለማድረግ፣ ከላይ የተመለከቱትን ችግሮች ለመቅረፍ፣ እንዲሁም በሃገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ከማስፈን አኳያና የዜጎችን የልማት ተጠቃሚነትን ለማረ□□ዩ፣ በኢኮኖሚያዊና ማ□በራዊ እንቅስቃሴ- ች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማ□ረ□ □ና የስልጣን ባለቤት እንዲሆኑ ለማብቃት መንግሥት የተለያዩ ፖሊሲ- ችንና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማ□ረ□ ላ□ □□ኛል:: ከነዚህ ፕሮግራሞች መካከልም በ1999 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም አንዱ ነው::*

*በ1999 ዓ.ም ተግባራዊ መሆን የጀመረው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ/□ሮ□ራም ሰነድ እስከ 2002 ዓ.ም ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ የመልካም አስተዳደር ተግባሮችን በዝርዝር □□□ና፣ በተጨማሪም የከተሞች መልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሣብን እንዲሁም በኢትዮጵያ ከተሞች በወቅቱ የነበረውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ምን እንደሚመስል የሚተነትን ሲሆን፣ በሰነዱ ተጠቃለው የቀረቡት ሰባት ንዑስ-ፕሮግራሞች ራሳቸውን ችለው ዝርዝር ፕሮግራም ተዘጋጅቶላቸው ነበር:: በፕሮግራሙ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ንዑስ ፕሮግራሞችና ሃያ ሦስት ፕሮጀክቶች ተካትተው እንደነበር የሚታወስ ነው::*

- *ሀ. የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *ለ. □መሠረተ ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *ሐ. የከተሞች ፋይናንስና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *መ. የአደረጃጀትና □ሰ□ □□ል ሥራ አመራር ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *ሠ. □ሕ□ብ ተሳትፎ ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *ረ. የከተማ ፕላን ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*
- *ሰ. □ሕ□ ማዕቀፍና የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም*

*በ1999 እና በ2000 በጀት ዓመታት የነበረው የፕሮግራም አፈፃፀም ሲታይ፣ የከተሞችን መልካም አስተዳደር በማረጋገጥ ረገድ ጅምር ውጤት መታየት መጀመሩን የሚጠቁም ነው:: ሆኖም በየአካባቢው የታዩት የተሻሉ ልምዶች ተቀምረው በሰፊው ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ባለመደረጉ ፕሮግራሙ የሚፈለገውን ከፍተኛ ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም:: በመሆኑም በ□ህ ረ□□ □ታዩትን በጎ ልምዶችን ቀምሮና □□□ሙ እጥረቶችን ቀርፎ የከተሞች የመልካም አስተዳደር ጥረት ከፍተኛ ውጤት እንዲያስገኝ ለማድረግ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ የእስካሁኑን ልምድ ግምት ባስገባ መልኩ ፕሮግራሙን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል::*

*በተ□ ማሪም በ□ህ □□ተተ□በረ በሚ□ኖ□ □ከተሞች መልካም አስተዳደር □ሮ□ራም ተካትተው የነበሩ በርካ□ ቁጥር ያላቸው ንዑስ-ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ከአፈፃፀም አኳያ በቁጥር መበርከታቸው አሉ□ዊ ተፅዕኖ ነበረው:: በመሆኑም በአፈፃፀም የታዩ እጥረቶችንና መልካም ተሞ□ሮ- ችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ተቀናጅተው በአንድ ላይ ቢፈፀሙ □ተሻለ □□ታማ የሚሆኑትን ንዑስ-ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመለየት ማሻሻያ- ች ማድረግ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተ□ስ□ል::*

የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራምና ሃገር አቀፉ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ተፈፃሚነት በከተሞች ሲረጋገጥ፣ በአጠቃላይ የከተሞች አስተዳደር ሁለንተናዊ አቅም ተገንብቶ በከተሞች የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች ሽፋንና ጥራት እንደሚያድግና ከተሞች ከገጠሩ የሃገሪቱ ክፍል ጋር ያላቸው ትስስር ተጠናክሮ ቀጣይነት ያለው ሃገራዊ ልማትን ለመምራት የሚያስችሉ ማዕከላት እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ተበታትኖ □ሚ□ኘውን የእነዚህን ሁለት ሃገራዊ □ሮ□ራሞች አፈፃፀም መስመር በማስያዝ፣ በከተሞች ያለውን ኃይልና ሥራዎችን አስተባብሮ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመምራት እንዲቻል አንድ ሃገር አቀፍ የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ባለፉት ዓመታት በፕሮግራም አፈፃፀም ላይ የታዩትን የባለቤትነትና አመራር ችግሮች ከወዲሁ ቀርፎ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣ እያንዳንዱ ንዑስ-ፕሮግራምን በክልልና በከተሞች ከማስፈፀም አኳያ በባለቤትነት የሚመሯቸው አካላት ከወዲሁ ተለይተው መታወቅ ይገባቸዋል፡፡ በየደረጃው ንዑስ-ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት የሚያስፈፅሙ አካላት ሥራዎችን ተረክበው በቀጥታ ወደ ሥራ መግባት እንዲችሉ ተሻሽሎ በቀረበው በዚህ ፕሮግራም የንዑስ-ፕሮግራሞችና የፕሮጀክቶች ባለቤቶችና ተባባሪ አስፈፃሚዎች በቅድሚያ ተለይተዋል፡፡

ዘላቂ ልማትን ለማፋጠንና ድህነትን ለማስወገድ የተቀረፀው የሃገሪቱ የአምስት ዓመት ዕቅድ /PASDEP/ እንደሚያመለክተው፣ በከተሞች ከሚከናወኑት ዋና ዋና የልማትና የሥርዓት ማሻሻያ ተግባራት መካከል አንዱ የሆነውን የመሠረተ-ልማት ሥራዎችን አቀናጅቶ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም በቀድሞው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም ተካትቶ የነበረው የመሠረተ-ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራምን የያዘ፣ እንዲሁም በከተሞች የመሠረተ-ልማት አውታሮችንና አገልግሎቶችን የማስፋፋት ተግባራትን እና አገልግሎቱን ከማሻሻልና ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የተሸለ አደረጃጀት የመፍጠርና ተግባራዊ የማድረጉ ሂደትን በማጠቃለል አንድ ሃገር አቀፍ የከተማ መሠረተ ልማት አቅርቦት ማሻሻያ ፕሮግራም የሚዘጋጅ በመሆኑ የመሠረተ-ልማት ሥራዎችና ተያያዥነት ያላቸው የአገልግሎት ማሻሻያዎች በዚህ ፕሮግራም ሰነድ ውስጥ አልተካተቱም፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን በፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ የነበራቸውን ምክንያቶች ለመፍታት፣ እንዲሁም የአቅጣጫ ለውጥ በማድረግ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ርምጃዎችን ያካተተ □ል□ እና ወደ ተጨባጭ ሥራ ሊያስገባ የሚችል የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሦስት ንዑስ-ፕሮግራሞችና በአጠቃላይ አስር ፕሮጀክቶችን አካትቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

1. የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም
2. የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም
3. የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም

ቀድሞ በነበረው የፕሮግራም ሰነድ በንዑስ-ፕሮግራምነት ተይዘው የነበሩ አንዳንድ ሥራዎችም በፕሮጀክት ደረጃ ከሌሎች ንዑስ-ፕሮግራሞች ተግባራት ጋር ተጠቃልለው ይፈፀማሉ፡፡ በቀድሞው ፕሮግራም የመሬት ልማትና አስተዳደር ማሻሻ□ ንዑስ-□ሮ□ራም እና የከተማ ፕላን ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም የነበሩት በአዲሱ ፕሮግራም ተቀናጅተው በከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ሥር ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

በተጨማሪም በመተግበር ላይ በሚገኘው የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም ውስጥ የተያዘው የሕዝብ ተሳትፎ ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም ቀሪ ሥራዎች ተሻሽሎ በቀረበው የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም በተቋማት አቅም

ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም ውስጥ ተዘርዝረው ይፈፀማሉ፡፡ በዚህ በተሻሻለው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም፣ በከተሞች የሚንቀሳቀሱ የፍትሕ አካላትን አቅም የመገንባት እና የአሰራር ሥርዓትን የማሻሻል ተጨማሪ ተግባራት፣ እንዲሁም በከተሞች በስፋት እያደገ የመጣውን የሕዝብን ሃብትና ንብረት የመመዝበር ተግባር እና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ የአመለካከት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራዎች ተቀናጅተው ይፈፀማሉ፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) አማካይነት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምን ይበልጥ እውን ለማድረግ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በዚህ ተሸሽሎ በቀረበው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ይህንን መሠረታዊ የአቀጣጫ ለውጥ፣ የከተሞችን ኃላፊነትና ስልጣን፣ እንዲሁም የተለያዩ ሴክተሮችን የሥራ ድርሻ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም በከተሞች በመከናወን ላይ የሚገኙትን ተዛማጅ ተግባራት አስተባብሮ ለመምራት የሚያስችሉ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

የታክስና የፋይናንስ አሰተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራምን ለማስፈጸም የተሻለ የፕሮግራም አወቃቀር በመጠቀም ቀድሞ በነበረው የፕሮግራም ሰነድ በከተሞች ፋይናንስና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-□ሮ□ራም ውስጥ ተካትተው የነበሩት ሰባት ፕሮጀክቶች በሦስት ፕሮጀክቶች እንዲጠቃለሉ ተደርጓል፡፡

በባለቤትነት ንዑስ-ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ከማስፈፀም አንፃር፣ በፌደራል ደረጃ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር፣ በክልል ደረጃ የክልል ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራምን አፈፃፀም ያስተባብራሉ፡፡ የፋይናንስና አኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና በክልል የሚገኙ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራምን ሙሉ ለሙሉ ተረክበው ያስፈፅማሉ፡፡ የሥራና ከተማ ልማት በከተሞች አቅም ግንባታ ጽ/ቤቱ አማካይነት በተባባሪነት ለታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራምን በፌደራል ደረጃ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚያስተባብረው ሲሆን፣ በንዑስ-ፕሮግራሙ የታቀፉትን ሦስት ፕሮጀክቶችም እንደ የኃላፊነት ወሰናቸው በክልል ደረጃ የሚገኙ የአቅም ግንባታ ቢሮ፣ የክልሉ የአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፣ የክልሉ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣ የፍትህ ቢሮ፣ የክልሉ የመገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲና የትምህርት ቢሮ በተባባሪነት ያስፈፅሙታል፡፡ (ዝርዝሩን በገፅ 51 ይመልከቱ)

ይህ የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም በሦስት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡

ክፍል አንድ የከተሞች መልካም አስተዳደር መሠረተ ሃሳብንና የኢትዮጵያ ከተሞች የመልካም አስተዳደር ሁኔታን የሚተነትን ነው፡፡ ቀድሞ በነበረው የማሻሻያ ፕሮግራም ሰነድ ላይ በዝርዝር የተቀመጡት የመሠረተ ሃሳብ ትንታኔ አስፈፃሚ አካላት ፍሬ ነገሩን ተረድተው የመልካም አስተዳደር ሥርዓትን የመገንባት/የማሻሻል ሂደት የማያቋርጥና የሁሉንም ተሣትፎ የሚጠይቅ፣ እንዲሁም ለተግባራዊነቱ ሥራ ላይ መዋላቸው መረጋገጥ ያለባቸው መርሆዎች ጭብጥን እንዲረዱት ለማገዝ በዚህ ሰነድም ሙሉ በሙሉ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ቀድሞ በነበረው የማሻሻያ ፕሮግራም ሰነድ ላይ የተብራራው የሃገሪቱ ከተሞች የመልካም አስተዳደር ገፅታ፣ ፕሮግራሙ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ የመጡ ለውጦችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማድረግና በአሁን ጊዜ እውን ከሆኑት ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም የዚህ ሰነድ አካል እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በክፍል ሁለት የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም የፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫዎች መግለጫ የቀረበ ሲሆን፣ በዋናነት የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራምንና የንዑስ-ፕሮግራሞችን ዓላማ፣ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት የያዘ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም በከተሞቻችን መልካም አስተዳደር መስፈን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚቀጥሉት ዓመታት የሚፈጸሙትን የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም፣ የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም፣ የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም እና የምክር ቤቶች አቅም ግንባታና የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ዝርዝር ይዘት ተተንትኗል፡፡

በክፍል ሦስት የአመራር ሥርዓቱ፣ የፕሮግራም ፋይናንስና የአፈፃፀም መርሃ-ግብር የተካተተ ሲሆን፣ እያንዳንዱን ፕሮጀክትን በባለቤትነት የሚያስፈፅመው አካል በቅድሚያ የማስፈፀሚያ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ያህ እውን ሲሆን የፕሮግራሙን የፋይናንስ ፍላጎት ማወቅ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ክፍል የተመለከተው የፋይናንስ መጠን በአጠቃላይ ፕሮግራሙን ከማስፈፀም አኳያ ፍንጭ የሚሰጥና በተለይ ክልሎችና ሌሎች አስፈፃሚ አካላት ከወዲሁ እንዲዘጋጁበት ለመጠቆም ያገለግላል፡፡ ቀድሞ የነበረውን የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ክልሎች በዋናነት በፐብሊክ ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራም (PSCAP) ፈንድ፣ በተጨማሪ ደግሞ ከራሳቸው በጀት በመመደብ ሲያስፈፅሙት መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ ነገር ግን የፐብሊክ ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራም በተያዘው በጀት ዓመት መገባደጃ ላይ ስለሚጠናቀቅ፣ አስፈፃሚ አካላትና ክልሎች ከወዲሁ ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

በመጨረሻም ይህ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም ሰነድ ከጥር 25-27 2001 ዓ.ም በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴርና በክልሎች መካከል በነበረው የጋራ መድረክ የፀደቀ ነው፡፡

# ክፍል አንድ

## የመልካም አስተዳደር መሠረተ ሐሳብና የመልካም አስተዳደር ሁኔታ በኢትዮጵያ ከተሞች

### I. የከተማ መልካም አስተዳደር መሠረተ ሐሳብ

የከተማ አስተዳደሮች ከተሞቻቸውንና ነዋሪዎቻቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ዕቅዶችን እያዘጋጁ የሚፈጽሙ፣ አካባቢዎቻቸውን በተመለከተ ሕጎችን በማውጣት እንዲከበሩ የሚያደርጉ በአጠቃላይም የከተማ ነዋሪዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በቅርብ ሆነው የሚያስፈጽሙና የሚከታተሉ አካላት ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት የከተማ አስተዳደሮቹ በየደረጃው ያለውን የሕብረተሰብ ክፍል በቀጥታ የሚያሳትፉ፣ ዕቅዶቻቸውንና በጀቶቻቸውን ለሕዝቡ ግልጽ የሚያደርጉ፣ ለሚያደርጉት ውሳኔ ተጠያቂ የሆኑ፣ ሥልጣናቸውን ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ያወረዱ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የከተማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ብቃትና ዝግጁነት ያላቸው እንደዚሁም የሕግ የበላይነት የሚያከብሩ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ በከተሞች መልካም አስተዳደር ሰፍኗል ሊባል የሚችለውም አስተዳደሮች ሕዝቡን ሲያሳትፉ፣ ሥልጣኑን በአግባቡ ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ሲያወርዱ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ሲ>ያሰፍኑ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የከተማ ልማትና አገልግሎት መስጠት ሲችሉ እና የሕግ የበላይነትን ሲያከብሩና ሲያስከብሩ ነው፡፡

መልካም አስተዳደር ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው መርሆዎች እንዳሉት የሚታወቅ ሲሆን በከተሞች መልካም አስተዳደር ሰፍኗል ሊባል የሚችለው እነዚህ መርሆዎች ተከብረውና ተጠብቀው ተግባራዊ ሲሆኑ ነው፡፡ እነዚህ መርሆዎች የተዋረድ ስልጣንና ኃላፊነት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናና ውጤታማነት፣ ፍትሃዊ የሀብት አጠቃቀም፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ የሕዝብ ተሳትፎና እንደዚሁም የሕግ የበላይነትና የደህንነት ዋስትናን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የነዚህ መርሆዎች ምንነትና ፋይዳ በሚቀጥሉት ክፍሎች ቀርቧል፡፡

## 1. ስልጣንና ኃላፊነትን ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ማውረድ

የመልካም አስተዳደር አንዱ መርሆ የተዋረድ ስልጣንና ኃላፊነትን የሚመለከት ሲሆን ይህም ሕዝቦች በአካባቢያቸው ጉዳይ ላይ የመወሰንና የመፈጸም ሰፊ ነጻነትና ስልጣን ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዚህ መርሆ መሠረት የኢትዮጵያ የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢያቸውን ጉዳይ በሙሉ ኃላፊነት መወሰንና መፈፀም የሚያስችላቸው ሰፊ ነፃነት በሕግ ሊረጋገጥላቸው ይገባል፡፡ ይህ መርሆ በፌደራልና በክልሎች ሕገ-መንግስቶች በግልጽ ከተቀመጠው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህንን በተግባር ለማረጋገጥም መብቱ ለከተሞች በዝርዝር ሕግ ተደንግጎ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህ መርሆ መሠረት ከተሞች የራሳቸው የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸውና ከመንግሥት የበጀት ድጐማ እንዲደረግላቸው የሚያስችል፣ የራሳቸውን ምክር ቤት በሕዝብ ምርጫ እንዲመሠርቱ የሚፈቅድ፣ ከተማ ነክ ውሱን የዳኝነትና ሕግ (የደንብ) የማውጣት ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሕጋዊ ነፃነት ሊረጋግጥላቸውም ይገባል፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ለከተሞች የተሰጠ የአስተዳደር ሥልጣንም በከተማ ደረጃ ብቻ የማይወሰንበትና ለበታች የአስተዳደር እርከኖችም (ለቀበሌዎችም) ሰፋ ያለ ሥልጣን የሚሰጥበት ያልተማከለ አስተዳደር የሚዘረጋበት መሆን አለበት፡፡

የዚህ መርሆ መረጋገጥ በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የከተማ አስተዳደሮችና በሥራቸው ያሉት የአስተዳደር እርከኖች በአካባቢያቸው ጉዳይ ላይ የመወሰንና የመፈጸም ነጻነትና ስልጣና ቢረጋገጥላቸው ነዋሪዎች በልማትና በአስተዳደር ሥራዎች ቀጣይና የተደራጀ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ ዲሞክራሲያዊ ባሕል እንዲዳብር እና ሲቪል ማህበራት እንዲጠናከሩ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም ሕዝቡ በልማትና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች በተለይም በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በተወካዮቹ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ የሚሳተፍበት የቀጥታ ተሳትፎ ዲሞክራሲ ለማጎልበት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ይህ መርህ ህዝቡ የአካባቢውን አስተዳደር በቅርብ እየተከታተለ ተጠያቂ እንዲሆን ለማድረግም የተመቻቸ ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡ እንደዚሁም በዚህ መርህ መሠረት የከተማ አስተዳደሮችና በሥራቸው የሚደራጁት የአስተዳደር እርከኖች ነዋሪው በቅርብ የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች ለማቅርብና ለማስተዳደር

ሥልጣኑና በቂ ሃብት እንዲኖራቸው ቢደረግ ነዋሪው የሚፈልገውን አገልግሎት በፍጥነት ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ ህዝቡም ይህንን ኃላፊነት የተጣለባቸውን የአስተዳደር አካላት ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ይህ ሲባል ስልጣንን በሙሉ በዘፈቀደ እና በአንጼ ለከተማ አስተዳደሮችና ለበታች የአስተዳደር እርከኖች ማውረድ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ መርሆ የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት እንዲችልም ጎን ለጎን ተቋማዊና የሰው ኃይል ዓቅሞችን በየደረጃው ማጎልበት እና የስርዓት ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

## 2. ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን

ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ መሠረታዊ ከሆኑት መርሆች አንዱ የከተማ አመራሮችና ሠራተኞች ለነዋሪው ሕዝብ ግልፅና ተጠያቂ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ መርህ ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓትን፣ የመረጃ ፍሰትንና ለውሣኔዎች ተጠያቂ የመሆን ሥርዓትን ይመለከታል፡፡ ግልፅነት በነፃ የመረጃ ፍሰት ላይ የሚገነባ ሲሆን ተጠያቂነት ደግሞ በማንኛውም ውሳኔ ሰጪነት ማለትም በከተማ አስተዳደር፣ በከተማ ነዋሪውና በግሉ ሴክተር የሚገኙ አካላት ለሕዝቡ ወይም ለሚመለከታቸው ተቋማት ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በከተማ አስተዳደሮች የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ በጀቶችና እቅዶች በግልጽነትና በሚተነበይ መንገድ መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡ ተመራጮችና በሹመት የተመደቡ ኃላፊዎች፣ ሌሎች የሲቪል ሰርቪስ መሪዎች እና ባለሞያዎች ከፍተኛ አርአያነት ያላቸውና በሁሉም ረገድ ራሳቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በየደረጃው በአስተዳደሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለሚደረግ ጥፋትም ፈጣን ተጠያቂነት መኖር ይኖርበታል፡፡ በነዚህም ዙሪያ ለሕዝቡ ወቅታዊና ሁለገብ መረጃዎች በቀጣይነት መቅረብ ያለበት ከመሆኑም በተጨማሪ የሕዝብ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ሊያገኝና የሕዝቡ ሃሳብም ሊደመጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሙስና የከተማ አስተዳደሮችን ዋጋ ሊያሳጣቸውና የከተማ ድህነትም የበለጠ እንዲሰፋ ስለሚያደርግ ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮችን ማስወገድና ሕዝቡ ሊያየው፣ ሊረዳውና ሊያርመው የሚችል ቀላልና ግልጽ አሰራር ማስፈን ያስፈልጋል:: የከተማ አስተዳደሮች ከተለያየ ዓይነት የሙስና ተግባራትና ሕዝብን የማጉላላት አሰራር የፀዱ፣ ሙስናንና የስነ-ምግባር መጓደልን በማይሸከሙ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሊደራጁ ይገባል፡፡ በተጨማሪ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ የነዋሪው ሕዝብ የተሳትፎ ደረጃ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ስለሚታመን ሕብረተሰቡ መብትና ግዴታውን አውቆ ለመብቱ ዘብ እንዲቆም የሚያስችል እገዛ በከተማ አስተዳደሩ መጠናከር ይኖርበታል፡፡

የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ በጀቶችና ዕቅዶች በተጠያቂነትና ግልጽነት መርሆ መሠረት መፈጸማቸው መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር እርምጃ በተጠያቂነትና በግልጽነት መርህ ላይ የተመሠረተ መሆን ለሚመዘገቡት የልማትና የአስተዳደር ውጤቶች ዘላቂነት፣ በሕዝቡ ዘንድም ሰፊ ተቀባይነትና እምነት መኖር ዋስትና ይሆናል፡፡

## 3. የሕዝብ ተሳትፎን ማጎልበት

ሁለተኛው የመልካም አስተዳደር መርህ የሕዝብ ተሳትፎን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ሕዝቡ በቀጥታ እና በወኪሎቹ አማካይነት በአካባቢው የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች ላይ በንቃት የሚሳተፍበት የተመቻቸ ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ ከከተማ አስተዳደር አንጻር ሲታይ የከተማ ምክር ቤቶች በነዋሪዎቻቸው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የቆሙ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የከተማው ነዋሪ ተደራጅቶ አካባቢውን በሚመለከቱ ዋና ዋና የልማትና የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ በቀጥታ ለመሳተፍ የሚያስችለው ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ በሁለቱም አግባቦች አማካይነት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ ዕቅዶችና በጀቶች በሕዝቡ ተሳትፎ የሚቀየሱ፣ የሚፈፀሙና የሚገመገሙ መሆን

አለባቸው፡፡ የወጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና ዕቅዶች በማስፈጸም ረገድ ለሚፈጸም ጥፋትም ሕዝቡ በወኪሎቹና በአደረጃጀቱ አማካይነት ተጠያቂ የሚያደርግበት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የሕዝብ ተሳትፎ የልማት ሃሣብን ከማመንጨት ጀምሮ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ የመሆንና ውሣኔዎች ላይ ተፅዕኖ የማሳደር አቅም እንዲኖረው ማስቻል ትኩረት የሚሰጠው ተግባር መሆን ይገባዋል፡፡ ነዋሪው በተለይም ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ በአግባቡ እንዲሳተፉ ማድረግ ልዩ አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ደሃው የሕብረተሰብ ክፍል በአካባቢው ጉዳይ ላይ ሁለንተናዊ ተሳትፎውን እንዲያሳድግ መበረታታትና መደገፍ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም የአስተዳደርና አስፈጻሚ አካላቱ የልማታዊ ባለሃብቱን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ ተጨባጭ ማሻሻያዎችን በማድረግ የልማት አጋርነቱን ማረጋገጥና ችግር ፈቺ የሆነ አመራር ለመስጠት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ሕዝቡ በተደራጀ መንገድ በቀጥታ የሚያደርገውን ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ የተሳትፎ ግልጽ ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የአስተዳደርና አስፈጻሚ አካላትም ይህንኑ የሕዝብ ተሳትፎ መርህ በሙሉ ልብ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ፣ ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ዙሪያ ለሕዝቡ ወቅታዊና ሁለገብ መረጃዎች በቀጣይነት ለማቅረብ የተዘጋጁና ለሕዝብ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት፣ እንደዚሁም የሕዝቡን ሃሳብም ለማዳመጥ ዝግጁ የሆኑ መሆን ይገባቸዋል፡፡

የሕዝብ ተሳትፎ መረጋገጥ የከተሞችን የልማትና የአስተዳደር እንቅስቃሴ ዘለቄታማ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ነዋሪዎችን በቀጥታና በወኪሎች አማካይነት በስፋት ያሳተፈና መግባባት ላይ የተደረሰበት ሕግና ደንብ ቀርፆ መተግበር የሕጎቹ ተፈፃሚነትና ተቀባይነትን ለማረጋገጥና በዚህም ዘላቂነት ያለው የልማት ሥራዎችን ለማከናወን፣ በተጨማሪም የተሻለ የአስተዳደር ሁኔታን ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ከተማ-አቀፍ የሆነና ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ የተቀረጸና መግባባት ላይ የተደረሰበት አነቃናቂ ተልዕኮ፣ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂካዊ ራዕይና ዕቅድ፣ እንዲሁም ሁሉን አሳታፊ በሆነ መልኩ የተዘጋጀ የረጅም ጊዜ የልማት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ማዘጋጀት ያለውን ኃይል አስተባብሮ ወደ ልማት ለማሰማራትና በዚህም ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ልማት (ከአካባቢ ጥበቃና ከፍትኃዊነት አንጻር) ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ በተመሳሳይ በከተሞች ውስጥ ባሉ አነስተኛ የአስተዳደር አካላት የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶች ሲቀረጹና ሲከናወኑ ከፕሮጀክት ቀረፃ እስከ ትግበራ ባለው አካሄድ ነዋሪዎችን ማሳተፍ ሕዝቡን በዕቅዱ ተግባራዊነት ዙርያ ለማሰለፍና ዕቅዱን ለማሳካት ጠቃሚ ነው፡፡ በአጠቃላይ ህዝቡ በወኪሎቹ ብቻ ሳይሆን ራሱ በቀጥታ በተደራጀ መልኩ የሚሳተፍበት ሥርዓት መዘርጋት ልማቱን ፈጣን፣ የህዝቡን ፍላጎት ያረጋገጠ፣ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ (ፍትሃዊ) ብሎም ዘላቂነት ያለው እንዲሆን ያስችላል፡፡

## 4. ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ማቅረብ

የከተማ አስተዳደሮች ለነዋሪዎቻቸው የመሠረተ-ልማትና ሌሎች ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች በተሟላ ሁኔታ ለማቅረብና እንደዚሁም መንግስታዊ የልማትና የአስተዳደር ሥራዎችን ለማከናወን የቆሙ ናቸው፡፡ አንዱ የመልካም አስተዳደር መርሆ ታድያ እነዚህ አገልግሎቶች፣ የልማት ሥራዎችና የአስተዳደር ተግባራት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ አኳሃን መከናወን እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ይህ መርህ የከተማ አገልግሎቶች፣ የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለነዋሪዎች የሚቀርቡበትን የአሰራር ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን መርህ በተግባር ለመተርጎም የአገልግሎት ሰጭና ተቀባይን መብትና ግዴታን በግልጽ መለየትና ማሳወቅ፣ እና ሥራዎቹን ለመፈጸም የሚያስችል የአደረጃጀትና የሰው ኃየል አቅም መፍጠር፣ አማራጭና ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን መጠቀም

(ለምሳሌ የግሉን ዘርፍ በአገልግሎት አቅርቦቱ ማሳተፍ፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ኮምፒዩተራይ ማድረግ፣ ወዘተ...) ይቻላል፡፡ ይህንን በመጠቀም የከተማ አስተዳደሮች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የልማት ሥራዎችን ማከናወንና አገልግሎቶችን በየደረጃው መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለነዋሪዎቻቸው መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ የከተማ አስተዳደሮቹ የልማት ሥራዎች አፈጻጸምና አገልግሎት አሠጣጡን በቀጣይነት ማሻሻልና ተጠቃሚዎችን ማርካት መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ የከተማ አስተዳደሮች ቀልጣፋና ውጤታማ ሥራዎችን በማከናወንና በቀጣይነትም በማሻሻል ነዋሪውን ተጠቃሚ ማድረግና ማርካት ሲችሉ ብቻ የልማቱና የአገልግሎት አሰጣጡን ዘላቂነት ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

ይህንን መርሆ ተግባራዊ ለማድረግ የከተማ አስተዳደሮች ሁለንተናዊ አቅማቸውን በቀጣይነት ማሳደግ ይገባቸዋል፡፡ የከተማ አስተዳደሮች የሚሰጥዋቸውን አገልግሎቶችና የሚያከናውኗቸው ሥራዎች ግልጽ ግቦችን ያስቀመጡና ለሕዝቡም በየደረጃው ግልጽ የሚደረጉ መሆን ሲገባቸው በተጨማሪም ከተሞች በገቡት ቃል መሠረት ቀልጣፋና ውጤታማ ሥራ ማከናወን ሳይችሉ ሲቀሩ ሕዝቡ ቅሬታውን የሚያቀርብበት እና አስተዳደሮቹ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓትም ሊሰፍን ይገባል፡፡

## 5. ፍትሃዊ የሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ

ይህ መርሆ የከተሞች ነዋሪዎች ያለምንም ዓይነት ልዩነት በእኩልነት በከተሞቻቸው ልማታዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ውሳኔ በመስጠት ሂደት መሳተፍና ከዚህም በእኩል ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የከተሞች ነዋሪዎች አቅም በፈቀደ መጠን በቂ እና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት፣ የሥራ ዕድል፣ የጤና፣ መሬት፣ መጠለያ፣ የመጠጥ ውኃና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን ፍትኃዊና በግልጽ በሚታወቅ ፖሊሲና አሠራር መሠረት የማግኘት መብት ሊረጋገጥላቸው እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ በከተሞች የሚደረገው የልማት እንቅስቃሴና የሀብት ክፍፍል ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎችና አካባቢዎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡ በከተሞች የሚመዘገበው ልማት እና የሚደረግ ማንኛውም የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊ ከሆነ የሚኖረውን ልማት ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግና መልካም አስተዳደረም ለማስፈን የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሃገሪቱ የከተማ ልማት ፖሊሲ ላይ እንደተመለከተው መልካም አስተዳደር ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚጠናከረውና ለቀጣይነቱ ዋስትና የሚያገኘው አሳታፊና ፍትሐዊ ፈጣን ልማት በማምጣት ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በከተሞች ፈጣን፣ ፍትሐዊና ቀጣይ ልማትን ለማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን በቅድሚያ ማስፈን የግድ ነው፡፡ ስለሆነም ፍትሃዊ ልማትና መልካም አስተዳደርን አስተሳስሮ ማስኬድ ብቸኛው የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መንገድ በመሆኑ በከተሞችም ልማትን ለማምጣት የግድ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡

## 6. የሕግ የበላይነትና የደህንነት ዋስትናን ማረጋገጥ

በከተሞች ውስጥ መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያ የፍትህና የጸጥታ አካላት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በከተሞች ውስጥ ሕዝቡ ንብረት የማፍራትና የመጠቀም መብቱ የሚረጋገጠው እንደዚሁም ወንጀልን ለመከላከልና ሕገጠወጦችን ለሕግ ለማቅረብ የሚቻለው የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥ ነው፡፡ የሕግ የበላይነት መርሆን ተግባራዊ ለማድረግ የፍትህ ሥርዓቱ ነፃነቱ የተጠበቀ፣ ተቋማዊና የሰው ኃይል ብቃት ያለውና ለደሃውም የሕብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ሲሆን ነው፡፡ በተመሳሳይ የነዋሪዎችን የግልና የማህበራዊ ደህንነት ዋስትናን የማረጋገጥ ሂደት በከተሞች የመልካም አስተዳደር ስርዓት የማስፈን ርምጃ ውስጥ መካተት ቿሚገባቸው መርሆዎች አንዱ ነው፡፡ ወንጀልን በመከላከልና በመቆጣጠር፤ በድህነት ልያ የሚገኙ ነዋሪዎችን ትምህርትና ስልጠና እንደዚሁም ሥራ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ የይዞታ

ዋስትና በማረጋገጥ፣ ስጫጭኟ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛው ዘርፍ እንዲሸጋገር የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር የግልንና የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና ማረጋገጥ ይገባል፡፡

በከተማ ልማት ፖሊሲው ላይ እንደተመለከተው የከተሞች ልማት ፈጣንና ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ በከተሞች የሕግ የበላይነትንና ሰላምን ማስፈን አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህንንም የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የፍትሕና የፀጥታ አካላት የማብቃት ሥራ መሠራት ይኖርበታል፡፡ በከተሞች የሚኖረው ልማት ፈጣንና ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግ ሁሉም ነገር ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ በተጠያቂነት እንዲሁም በግልጽ የሥራ ድርሻና በቅንጅት የሚፈፀምበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂ ልማት ለማስመዝገብ የሕግና የፍትህ ሥርዓቱ ልማታዊ ባላብቶችን የሚያበረታታና የሚደግፍ፣ ሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን ደግሞ የሚገታ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከተሞቻችን በሥርዓት ለመምራት እና በዚህም ለልማትና ለመልካም አስተዳደር መስፈን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁለገብና ዝርዝር ደንቦችና መመሪያዎች እንዲወጡ ማድረግና ይህንንም የሚፈፀም አቅም መፍጠር ይገባል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የሕግ የበላይነትና የደህንነት ዋስትናን ለማረጋገጥ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ሁለቱን አስተሳስሮ መፈጸም የግድ ይላል፡፡ በከተማ ልማት ፖሊሲ ላይ እንደተመለከተው ለወንጀል መንስኤ የሆኑ ድህነትና ሥራ አጥነትን፣ ሕገ ወጥነትንና ማን አለብኝነትን በፈጣን ልማትና በተጠናከረ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲሁም በብቁ የአስተዳደር አቅም መመከት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በተለያዩ ጽሁፎች በተለያየ መልኩ የሚቀርቡ ቢሆንም ለዚህ ፕሮግራም ዝግጅትና ትግበራ ቁልፍ የሚባሉትን መርሆዎች ከላይ በተገለጸው መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በየርዕሱ እንደተመለከተው የመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ የመልካም አስተዳደር መኖር የከተማ ነዋሪዎች ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተጠያቂነት ያለበትና ግልጽነትን የተላበሰ የመንግሥትና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙ እገዛ ያደርጋል፡፡ መልካም አስተዳደር ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ እና ድህነትን ለመቀነስ ይረዳል፡፡ የመልካም አስተዳደር መኖር ለልማት የሚውል ኢንቨስትመንት በመሳብና በዚህም የኢኮኖሚ እድገትን በማረጋገጥ በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ከተለያዩ አገሮች ልምዶች መረዳት ያቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልካም አስተዳደር የነፍስ-ወከፍ ገቢን በማሳደግ በኩልም ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ሦስት የመልካም አስተዳደር መመዘኛ ነጥቦችን (ሙስናን መቆጣጠር፣ የንብረት ባለቤትነትና የሕግ የበላይነት መረጋገጥና ተጠያቂነት) በመውሰድ ከአንድ መቶ በላይ በሆኑ አገሮች በተደረገ ጥናት የመልካም አስተዳደር ጥራት ከነፍስ-ወከፍ ገቢ መጠን/እድገት ጋር ጠንካራ ወይም የጠበቀ ቀጥተኛ ዝምድና እንዳለው ታውቋል፡፡ ስለሆነም የመልካም አስተዳደር ሁለንተናዊ ፋይዳ በመገንዘብ በከተሞች ያለውን የአስተዳዳር ሁኔታ ማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ሆኗል፡፡

## II. የኢትዮጵያ ከተሞች የመልካም አስተዳደር ገጽታ

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለከተማ ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠቱ በተለያዩ ከተሞች የልማት ሥራዎችና የአስተዳደር የማሻሻያ ኘሮግራሞች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ የተጀመሩትን የልማት ሥራዎች አስፍቶ ለመተግባር የሚያስችሉ የከተማ ልማት ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ወደ ትግባራ ተሸጋግረዋል፡፡ የከተሞች አስተዳደር በተመለከተም በተመሳሳይ ወጥነት ያለው ፕሮግራም በማዘጋጀትና ወደ ትግበራ በማሸጋገር መልካም አስተዳደርን ይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ ታምኖበት የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በከተሞች ያለውን ጅምር የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ

ለማስፋፋትና ይበልጥ ውጤታማ በማድረግ ዘላቂና ፈጣን ልማትን፣ እንደዚሁም የሕዝቡን የስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በሃገር አቀፍ ደረጃ በመተግበር ላይ የሚገኙትን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምንና የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራምን በማጣመር የተቀናጀ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ሰነድ ማዘጋጀት ወቅታዊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ የቀድሞው የማሻሻያ ፕሮግራም ሰነድ ሲዘጋጅ በግብዓትነት ውሎ የነበረው በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ገፅታ የዳሰስ ውጤት ፕሮግራሙ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ጀምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መሻሻሎች የተመዘገቡ ቢሆንም፣ በመሠረታዊ ይዘቱ ግን ከፍተኛ ለውጥ ያልታየበት በመሆኑ ለኘሮግራሙ ቀረፃ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማድረግ ብቻ በግብአትነት እንዲውል ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍል በኢትዮጵያ ከተሞች እየተካሄዱ ያሉ ጅምር የመልካም አስተዳደር የማሻሻያ እንቅስቃሴዎች ያስገኙት ውጤትና አሁኑም ድረስ በከተሞቹ የሚታዩትን የአስተዳደር ችግሮች በመዳሰስ የመፍትሄ ሀሳቦች ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

## 1. የከተሞች የተዋረድ ስልጣንና ኃላፊነት

ከአዲስ አባባ ውጪ ያሉ ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች የአካባቢያቸውን ጉዳይ በሙሉ ኃላፊነት መወሰንና መፈፀም የሚያስችላቸው ሰፊ ነፃነትና የሕግ ድጋፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልነበራቸውም፡፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን የተወሰኑ የሃገሪቱ ከተሞች ራሳቸውን ማስተዳደር የሚያስችላቸው የሕግ ማዕቀፍና የአደረጃጀት ማሻሻያዎች ተከናውነዋል፡፡ በክልሎች ሕገ-መንግሥት የከተማ አስተዳደሮች በአዋጅ እንዲቋቋሙ በተደነገገው መሠረት ክልሎች የከተማ አስተዳደሮች ማቋቋሚያ አዋጆች በማውጣት ከተሞቻቸው በሕግ እንዲቋቋሙና ተገቢው ነጻነትና የሕግ ድጋፍ እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የደቡብ ብ/ብ/ሕ፣ የትግራይ እና የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስታት ለከተሞቻቸው የሕግና ተቋማዊ ማዕቀፍ አውጥተው ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በቻርተር እንዲተዳደሩ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የአፋር፣ የሶማሌ፣ የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልሎች የከተሞች ማቋቋሚያ አዋጆቻቸውን አፅድቀው ተግባራዊ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ ናቸው፡፡ እስከ አሁን ድረስ በሃገር ደረጃ ከአንድ መቶ ስልሳ በላይ የሚሆኑ ከተሞች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት የሕግና የአደረጃጀት ሁኔታ እየተመቻቸ ይገኛል፡፡

ይህ ጅምር የማሻሻያ ተግባር በከተሞች ለመልካም አስተዳደር መስፈን አስፈላጊ የሆነውን የተዋረድ ስልጣንና ኃላፊነት የሚመለከተውን መርህ በመተግበር የከተሞቹ የአስተዳደር ሁኔታን ለማሻሻል ያገዘ ቢሆንም ፕሮግራሙን ማስፋት ይገባል፡፡ እንደዚሁም አሁንም ድረስ በአፈጻጸም ወቅት በስልጣን ክፍፍል፣ በአደረጃጀትና በአፈፃፀም ረገድ የሚስተዋሉትን አንዳንድ ችግሮች በአፋጣኝ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡ አሁንም ድረስ አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ከተሞች የሕግ ድጋፍ ኖሯቸው አካባቢያቸውን የማስተዳደርና በራሳቸው ጉዳይ ላይ ራሳቸው የመወሰን ስልጣን ገና አልተጎናጸፉም፡፡ ስለሆነም በየክልሉ በወጡት የከተማ አስተዳደሮች ማቋቋሚ አዋጅ መሠረት ከተሞች ራሳቸውን የማስተዳደርና በራሳቸው ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን አቅማቸውን ባገናዘበ ሁኔታ ሊያገኙ ይገባል፡፡ አሁን ባለው አደረጃጀት የሕግ ድጋፍ እንዲኖራቸው በአዋጅ የተቋቋሙና በምርጫ የቆሙ ምክር ቤቶች ያሏቸው ከተሞች በርካታ በመሆናቸው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ አለ፡፡ የሕግ አውጪ፣ አስፈፃሚና ተርጓሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር በከተሞች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በሕግ ተለይቶ የተቀመጠ መሆኑ በከተሞች አመራር ስርዓት ላይ ገልፅ አቅጣጫ፣ ካልተማከለ የሥልጣንና የኃላፊነት ክፍፍል መርህ አንፃር ደግሞ ሲታይ በከተሞች የመወሰን ስልጣን እና በአሰራር ላይ አወንታዊ ተፅእኖ በማሳደር ላይ እንደሚገኝ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የከተማ አስተዳደሮች ገቢንና የወጪ በጀት አስተዳደርን በተመለከተ በከተማ አስተዳደሮች ማቋቋሚያ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጣቸው ስልጣን በልዩ ልዩ ምክንያቶች በአግባቡ ሥራ ላይ እየተተረጎመ አይደለም፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የከተሞች የማስፈጸም አቅም ማነስ ነው፡፡ የከተሞች ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም አናሳ መሆን ከተሞች በአዋጅ የተሰጣቸው ሥልጣን በደንብና መመሪያ ተገድቧል፡፡ በታሪፍ አጣጣል የከተሞች ብቃት አጠራጣሪ መሆን፣ እና የታሪፍ ተመን አወጣጥ ሂደቱ ነዋሪውን የማያሳትፍና በነዋሪው ላይ አላግባብ ጫና የሚፈጥር ይሆናል የሚል ስጋት መኖር ከተሞች በአዋጅ የተሰጣቸውን ገቢያቸውን የማሳደግ ስልጣን ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ የከተሞች የገቢ አሰባሰብና የወጪ አስተዳደር አቅም ዝቅተኛ መሆን በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ዙርያ በርካታ የአፈፃፀምና የአሠራር ችግሮችም እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተለይ ቀደም ብሎ በአብዛኛዎቹ የክልል ከተሞች ሁለት የበጀት፣ ሁለት የገቢ አስተዳደር እና ሁለት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መኖሩ የከተማ አስተዳደሮችን ላላስፈላጊ ወጪና የሥራ ድግግሞሽ ዳርጓቸው ነበር፡፡ የዚህ ዓይነቱ አሠራር አሁንም በስፋት ሥራ ላይ የሚገኝ በመሆኑ በከተሞች የተቀናጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ካለማስቻሉም በላይ የፋይናንስ ተጠያቂነትና ግልፅነት ሙሉ በሙሉ እንዳይሰፍን ምክንያት ሆኗል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች ያልተማከለ አደረጃጀትን መሠረት በማድረግና አንዳንድ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከክልል ለከተሞች የሚደረግ ድጐማ መኖሩ ታይቷል፡፡ ሆኖም ከፌዴራል መንግስትም ሆነ ከክልል መስተዳደሮች ለከተሞች የበጀት ድጋፍ የሚደረግበት ወጥ፣ ግልጽና ፍትኃዊ የሆነ የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓትሐቀመር የለም፡፡ በአጠቃላይ በገቢና በወጪ አስተዳደር ረገድ የከተማ አስተዳደሮች ስልጣን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በሂደት ሙሉ የመወሰን ስልጣን እና ስልጣኑን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ሁለገብ የማስፈጸም አቅም መፍጠር የግድ ይሆናል፡፡ በዚህም የመልካም አስተዳደር አንዱ መርሆ የሆነውን በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሌላው ከተዋረድ ስልጣንና ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ያልተማከለ ሥርዓትን በመዘርጋት ረገድ በኢትዮጵያ ከተሞች የተሄደበት ርቀት ነው፡፡ በአዲስ አባባና በአንዳንድ ሌሎች ትልልቅ ከተሞች የአስተዳደር ስልጣኑን ለበታች የአስተዳደር እርከኖች (ለክፍለ-ከተማ፣ ቀበሌ) በማውረድ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ከተሞች በተለይም የቀበሌ የአስተዳደር እርከኖች ተገቢው በጀት፣ የማስፈፀም አቅምና ከዚህ ጋር በተያያዘም በቂ የመወሰን ሥልጣን የሌላቸው በመሆኑ ይህ ለነዋሪው አልግሎቶችን በቅርብ ለመስጠትና ነዋሪውን በቀጥታ ለማሳተፍ እንቅፋት እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆንም የከተሞች የአስተዳደር ሁኔታን ለማሻሻል ውጤታማ በሆነ አኳኃን የአስተዳደር ስልጣኑን ለበታች የአስተዳደር መዋቅሮች በማውረድ በራስ ጉዳይ ራስ የመወሰን መብት ማረጋገጥ፣ እና የሕዝቡን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል፡፡ በአልተማከለ አስተዳደር መርህ መሠረት ሥልጣን ወደ ሕዝቡ እየቀረበ መሄድ ስላለበት የቀበሌና ሌሎች የበታች የአስተዳደር እርከኖች ትኩረት ተሠጥቷቸው እንዲጠናከሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በነዚህ መዋቅሮች ያለው አደረጃጀት በአሰራር፣ በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስና በበጀት በመደገፍና በማጠናከር የማስፈፀም ብቃታቸውን ማሳደግ ይገባል፡፡

## 2. የከተማ አስተዳደሮች ቅልጥፍናና ውጤታማነት

በአሁኑ ጊዜ በርካታ የሃገሪቱ ከተሞች የሕግ፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያዎች ያደረጉ ሲሆኑ ሌሎች እስካሁን በማሻሻያው ያልታቀፉ ከተሞችም ማሻሻያውን ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ እንደዚሁም ብዙዎቹ የሃገሪቱ የከተማ አስተዳደሮች የአገልግሎት ማሻሻያ ፕሮግራምን ጨምሮ የተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ ንዑስ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን፣ እነዚህ የማሻሻያ ፕሮግራሞች በተካሄደባቸው ከተሞች ነዋሪዎች ከቀድሞው በተሻለ ሁኔታ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በማግኘት ላይ እንዳሉ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

በተለይ በያዝነው ዓመት የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በአብዛኛዎቹ ክልሎች ተጠናቅቆ አዲስ አበባን ጨምሮ በተወሰኑ ከተሞች የሙከራ ትግበራ ተጀምሯል፡፡ በተለይ ሃገር አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን የከተማ ልማት ፕሮግራምና የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራምን በክልሎችና በከተሞች ተፈፃሚ ለማድረግ አስፈፃሚ አካላት የተሻለ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ስለሆነም በተለይ የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም ዓላማዎችን ከማሳካት አኳያ እስካሁን ከነበረው አካሄድ የተገኙ ምርጥ ያደረጃጀት አግባቦችን በመቀመር በየደረጃው ያሉ የንዑስ-ፕሮግራሞች አስፈፃሚ አካላት ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው አደረጃጀቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) መቀመር አስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ለነዋሪዎቻቸው በተሻለ ሁኔታ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በማቅረብ መልካም አስተዳደር ለማስፈን እንዲችሉ ቀጣይ የሆኑ የፖሊሲና የሕግ፣ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያዎች እና የሰው ኃይል ልማት ማካሄድ እንደሚገባቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን ሁኔታ ባጭሩ ለማሳየት እንዲቻል በመሬት፣ በከተሞች ፕላንና ፋይናንስ ዙርያ ያለውን ሁኔታ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### ሀ. የመሬት ልማትና አስተዳደር

በከተሞች የመሬት አቅርቦት መጠነኛ መሻሻል ያሳየ በመሆኑ በከተሞች ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የተሻለ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በአገሪቱ ትልልቅ ከተሞች ለኢንዱስትሪ ልማት የሚውሉ ቦታዎችን በመለየትና በማልማት ለኢንቨስትመንት ዝግጁ እንዲሆኑ የተደረገው ጥረት አበረታች ውጤት እያስገኘ ይገኛል፡፡ የከተማ መሬት በአገሪቱ የሊዝ አዋጅ መሠረት ለማስተዳደር እንዲቻል ክልሎች የሊዝ አፈጻጸም ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀሳቸውና በዚህም መሠረት በርካታ ከተሞች አዲስ የሚሸጡት መሬት በሊዝ ሥረዓት እንዲተዳደር ማድረጋቸው በበጎ መልኩ የሚታይ ነው፡፡ እንደዚሁም ከተሞች አቅማቸው በፈቀደው መጠን ለነዋሪዎቻቸው የቤት መሥሪያ ቦታ ለማቅረብ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ከተሞች የመሬትና የቦታ ይዞታዎች አስተዳደርን ለማሻሻል ጅምር ጥረቶች እንዳሉ ታውቋል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ከተሞች በመሬት ልማትና አስተዳደር ረገድ በሚፈለገው ደረጃ ቀልጣፋና ውጤታማ ሥራ አከናውነዋል ለማለት አይቻልም፡፡ የከተሞች የመሬት ልማትና አስተዳዳር በነዋሪዎች ዘንድ አሁንም ድረስ  እሮሮ የሚታይበት ነው፡፡ በከተሞች ያለው የመሬት አጠቃቀምና አቅርቦት ግልፅና ወጥነት ባለው የአሠራር ስርዓትና አደረጃጀት ባለመደገፉ፣ እንዲሁም ማንም እንዳሻው የማያዛባው የመሬትና መሬት ነክ ንብረት መረጃ ሥርዓት አለመኖር ሳቢያ ውሱን የሆነው የከተማ መሬት ለምዝበራ፣ ሙስናና ብክነት ተጋልጧል፡፡

በከተሞች መሬት ለአልሚዎች ከመሰጠቱ በፊት ለባለይዞታዎች ፍትሃዊ የካሣ ክፍያ እንዲከፈል የሚያስችል ወጥና ግልጽ ሥርዓት አልነበረም፡፡ በቅርቡ ለዚህ መፍትሄ እንዲሆን የካሣ አዋጅና ደንብ የወጡ ሲሆን፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችም በየክልሉ ተዘጋጅተዋል፡፡ ይህ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ተግባር ቢሆንም የነዚህ ሕጎች አፈፃፀም የተሟላና ወጥነት ያለው አለመሆን የአሠራር ሥርዓቱን ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም ለልማት የሚቀርቡ የከተማ ቦታዎች ብዙ ጊዜ የመሠረተ ልማት በቅድሚያ አይሟላላቸውም፡፡ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የከተማ ቦታዎች የስፋት ስታንዳርድና የሽንሻኖ ስርአት የላቸውም፡፡ የከተማ መሬት በተለያየ ስልት (በጨረታ፣በድርድር፣ ወዘተ…) በሊዝ የሚቀርብበት አሰራር በመኖሩ ግለፅነትና ፍትሃዊነት የጎደለው አፈፃፀም በከተሞች ተስተውሏል፡፡ በከተሞች ዙሪያ ያለ የገጠር መሬት ወደ ከተማ ከመካተቱ በፊት የመሬት አጠቃቀምና የመልሶ ማቋቋም ሂደት ለመምራት የሚያስችል ግልጽና ወጥነት ያለው የአሠራር ሥርዓትም አልነበረም፡፡ በሌላ በኩል በከተሞች ሕገወጥ የመሬት ይዞታን ለመከላከልና ለማስተካከል የሚሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ሕገወጥ የመሬት ይዞታ በስፋት ይታያል፡፡ መሬትን ለተሻለ ልማት

ከማስለቀቅና የካሣ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በአዋጭነቱና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ተገቢው ጥናት አይደረግም፡፡ ከዚህ ውጭም በመሬት ዝግጅት፣ ልውውጥና ምዝገባ እንዲሁም በቴክኖሎጂ አጠቃቀም በመሣሠሉት የግሉ ሴክተር ተሣትፎ አናሣ በመሆኑ በመሬት ዙሪያ ቀልጣፋና ውጤታማ ሥራ እንዳይሠራ ምክንያት ሆኗል፡፡

በከተሞች በአሁኑ ወቅት በመተግባር ላይ ያለው የመሬት ሊዝ አሠራር መሻሻል የሚያስፈልገው እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ የሊዝ፣ የምሪት፣ የምደባና የሕገወጥ ይዞታ ጐን ለጐን በከተሞች የሚካሄዱ በመሆናቸው ቀልጣፋና ውጤታማ የመሬት ገበያ ለመፍጠር አዳጋች ሆኗል፡፡ በበርካታ ከተሞች አሁኑም መሬት ያለጫረታ በከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች በሚተመን ዝቅተኛ ዋጋ ወይም ከክፍያ ነፃ እና ከሊዝ ሥርዓት ውጪ ይሠጣል፡፡ የከተማ መሬት የሊዝ ሥርዓት ተግባራዊ ያልሆነባቸው በርካታ ከተሞች አሁንም አሉ፡፡ በእነዚህ ከተሞች የከተማ መሬት በጣም በዝቅተኛ ክፍያ በኪራይ የሚሰጥ በመሆኑ ከተሞች ፈጣንና የተሻለ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራ እንዳይካሄድባቸው እንቅፋት ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ አስተዳደሮች (ማዘጋጃ ቤቶች) መሬት በምደባ በስፋት የሚተላለፍበት አካሄድ በመኖሩ የመሬት ሊዝ ዋጋና ገቢ አነስተኛ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ እንዲሁም የመሬት ልማትና አስተዳደር ስራዎች የሕግና የአሠራር ክፍተቶች ያሉባቸው በመሆኑ ለሙስና በር የሚከፍቱ መሆናቸውንና በአግባቡ ተፈትሸው ሊስተካከሉ እንደሚገባ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

በመሬት ዙሪያ የተካሄዱት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሕገወጥ መንገድ መሬት የመያዝና ይህንኑም በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጥበት ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህም በከተሞች ፈጣንና ቀልጣፋ የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ለማረጋገጥ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ የመሬት ሽያጭና ለሌላ ወገን የማስተላለፍ ተግባር የመሬት ታክስ ከመሰብሰብ፣ የይዞታን ትክክለኛነት ከማረጋገጥና ከመሳሰሉት አላማዎች አንጻር የመሬት የመረጃ ሥርዓት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታመን ቢሆንም ይህንን የመሬትና መሬትጠነክ ንብረት ምዝገባ የሚያከናውን አካል ካለመኖሩም በላይ ግልፅ የሆነ አሠራር እንዳልተዘረጋም ታይቷል፡፡

### ለ. የከተማ ፕላን

የከተማ ፕላን ነዋሪው በቀጥታ የሚጠይቀው አገልግሎት ባይሆንም የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ሌሎች የልማት ሥራዎችና አገልሎቶች ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ አኳሃን ለመፈጸም ስለሚያስቸላቸው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ከተሞች በፕላን የሚመሩ እንዲሆኑ ማድረግ ከተሞች መሠረተጠልማቶችንና መሬትን አስተማማኝ በሆነ መልኩና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለማቅረብ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የከተማ ፕላን መኖር ኢንቨስትመንትን በመሳብ ዘላቂነት ያለው ልማትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ የከተማ ፕላን እና ፕላኑን ለማስፈጸም የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም ሲኖር ደግሞ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር (የከተማ ሕገጠወጥነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር)፣ የከተማ-የገጠርና የከተማ-ከተማ ትስስሮችን ለማጠናከር፣ አካባቢን (ኢንቫይሮመንት) ለመጠበቅ፣ ምቹ የመኖሪያ አካባቢ ለመፍጠር፣ የንብረት ዋስትናን ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የከተማ ፕላን በማዕከል በአንድ ኢንስቲትዩት ይዘጋጅ ነበር፡፡ በዘርፉ ያልተማከለ አሰራርን የተከተለ አቅም ግንባታ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ስለነበር የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንደዚሁም የግሉ ዘርፍ የፕላን ዝግጅት አቅም አናሳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም በአገሪቱ በአጠቃላይ የከተሞች ኘላንን የማዘጋጀትና የማስፈፀም እንዲሁም የመከታተል አቅም ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቷል፡፡ እስካሁን ድረስ ፕላን የተዘጋጀላቸው ከተሞች ከመቶ አይበልጡም፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ ፕላኖች እንዳሉ ይታመናል፡፡ የሚዘጋጁ ፕላኖችም በወቅቱ በሥራ ላይ የማይውሉበት እና

ሙሉ በሙሉ የማይከበሩበት ሁኔታም በስፋት እንደሚታይ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ይህም ሁኔታ የከተማ ኘላንን መሠረት በማድረግ መሠረተ ልማት የተሟላላቸውን የለሙ መሬቶች በማዘጋጀትና ለአልሚዎች በማቅረብ የከተሞች ዕድገት እንዲፋጠን ለማድረግ እንቅፋት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት በከተሞች የግንባታዎች መጓተትና በወቅቱ ሥራ አለመጀመር እንደዚሁም $ ሕገወጥ ግንባታዎች መበራከት ይስተዋላል፡፡ በርካታ የኢትዮጵያ ከተሞች ፕላን ስለሌላቸው ወይም ቢኖራቸውም የማስፈጸም አቅማቸውና ዝግጁነታቸው ውሱን በመሆኑ ከተሞች ያለአግባብ ወደጐን በመለጠጥ የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ለከፍተኛ መሬት ብክነት፣ የመሠረተጠልማት ወጪና  የካሣ ክፍያ ወጪ እየተዳረጉ ነው፡፡

ከባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን በተለይ በዘርፉ አቅም ግንባታ ተግባር የተሻለ ትኩረት በመሰጠቱ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብ/ብ/ህ ክልሎች የከተማ ፕላን ዝግጅት ኢንስቲትቶች ለማቋቋም ተችሏል፡፡ በአፋር፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉልና ጋምቤላ ክልሎች የማቋቋም ሂደት ተጀምሯል፡፡ ነገር ግን በየክልሉ ካለው የከተማ ፕላን ዝግጅት ፍላጎት አንጻር እነዚህ የፕላኒንግ አሃዶች አቅማቸው አሁንም እጅግ አነስተኛ በመሆኑ የተጀመረው የአቅም ግንባታ ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እመርታ በሚያስገኝ መልክ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያሻል፡፡ እንደዚሁም የከተማ ኘላን አገልግሎት የሚሰጡ የግል አማካሪ ድርጅቶች በበቂ መጠን እንዲፈጠሩና እንዲያድጉ ለማድረግ ለዘርፉ የተመቻቸ የሬጉለተሪ ሁኔታ በመፍጠርና አስፈላጊ ድጋፍ በመስጠት ሚናቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በከተማ ልማት ፖሊሲው ላይ እንደተመለከተው የከተማ ኘላን አጠቃላይ አቅጣጫ የገጠርና ከተማ እንዲሁም የከተማና ከተማ ትሥሥርን መሠረት ያደረገና የሚያጠናክር፣ የልማት እቅድንና የመሬት አጠቃቀምን የሚያቀናጅ፣ የሃገርና የክልል የልማት እቅዶችን መነሻ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚዘጋጀው የከተማ ፕላን ይዘቱ ፈጣንና ፍትሐዊ ልማትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን የመንግሥት፣ የባለሃብትና የሕዝብን ሚና የለየና ያቀናጀ፣ ሦስቱንም አካላት በስፋት በቀጣይ የምክክር መድረክ የሚያሳትፍና ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡ የሚዘጋጀው የከተማ ፕላን ለአፈፃፀሙ የተቋማዊ አቅም ግንባታና በጀትን አብሮ ያቀደ፣ በማስፈፀሚያ ሕግ የተደገፈ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ መሆን አለበት፡፡ ይህም በቀጣይነት የሚሻሻልና በዝርዝር ማስፈፀሚያ ኘላን እንዲደገፍ በማድረግ ሕያውና ሊተገበር የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የሚዘጋጀው የከተማ ኘላን ከተሞችን በሥርዓት ለማሳደግና የልማት ማ(ከልና ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያግዝ፣ እንዲሁም ለኑሮና ለሥራ አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚረዳ መሆን አለበት፡፡

## ሐ. የከተሞች ገቢ

አዲስ አበባ፣ አዳማና የመሳሰሉ ከተሞች ባለፉት ጥቂት አመታት ገቢያቸው እስከ ሦስት እጥፍ በሚደርስ መጠን ለማሳደግ ችለዋል፡፡ ለገቢው ማደግ አስተዋጽኦ ካበረከቱት መካከል የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ተግባራዊ መሆን፣ በየእርከኑ የሚሠበሰቡ የገቢ ዓይነቶች ተለይተው ገቢን የማሰባሰብ ስልጣን ለታችኞች የአስተዳደር የተዋረድ እርከኖች መሰጠት፣ ገቢን የሚያሻሽሉ ዘመናዊ አሠራሮች መዘርጋትና የሰው ኃይል አቅም ማጠናከር፣ መሬት በተሻለ መጠን በሊዝ መሸጥ የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሌሎች ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮችም ባለፉት 10 ዓመታት የታክስና የታሪፍ አዋጃቸውን በተወሰነ ደረጃ አሻሽለው ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሆኑና ገቢያቸውም አንፃራዊ መሻሻል እንዳሳየ ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ውጪ ባሉ በርካታ ከተሞች ያለው ገቢ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ብዙም ለውጥ እንዳልታየበት በዘርፉ ከተካሄዱት ዳሰሳዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች የታክስና ታሪፍ አዋጅ ሳይከለስ ለ30 አመታት የቆየ በመሆኑ ምክንያት ከከተሞች የሚሰበሰበው ገቢ ዝቅተኛ ነው፡፡ በከተማ ልማት ፓሊሲው እንደተመለከተውና በቅርቡ

በተደረጉት ጥናቶችም እንደተረጋገጠው እስካሁን ድረስ አብዛኛዎቹ ከተሞች ገቢ የማሰባሰብና የመጠቀም ስልጣናቸው በአግባቡ አልተረጋገጠላቸውም፡፡ ብዙዎቹ ከተሞች ትርጉም ያለው የራሳቸው ገቢ የሌላቸው ሲሆን ከክልልና ከፌዴራል የሚሠጣቸውን ድጐማ በቁጠባ የመጠቀም አመለካከትና ሥርዓትም የላቸውም፡፡ በከተሞች ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የከተማ አስተዳደሮች ገቢያቸውን ለማሻሻል አዳዲስ የገቢ ምንጮችን ለመፍጠር፣ አዳዲስ ግብር ከፋዮችን ወደ ግብር ከፋይነት ለማስገባት፣ ከተለያዩ የገቢ አርእስቶች መሰብሰብ የሚገባውን ውዝፍ ግብር በወቅቱ ለመሰብሰብና ሕገወጥ ነጋዴዎች የግብር ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ደካማ ነው፡፡ የታክስ አሰባሰብ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንደዚሁም የሕግ የበላይነት ችግሮች ከሚታይባቸው የከተማ ሥራዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ ገቢ ለልማትም ሆነ ለመልካም አስተዳደር ሥርዓት መጠናከር ወሳኝ ግብዓት መሆኑን በመረዳት በአሠባሰብ ረገድ የተገኘው ውጤት አጥጋቢ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የከተሞች የገቢ አቅም ዝቅተኛ ሆኖ በመቆየቱ ኅብረተሰቡ ከአስተዳደሮቹ የሚጠብቀውን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለማግኘት ማነቆ ሆኗል፡፡

### 3. ግልጽነትና ተጠያቂነት

በከተሞች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደተመለከተው በሕግ የተደነገጉ የሕግ አውጪ፣ አስፈፃሚ፣ የከንቲባና የሥራ አስኪያጅ የኃላፊነትና የሥልጣን ወሰኖች አሏቸው፡፡ የሥልጣን ክፍፍሉና የሥልጣን ተዋረዱ በዚህ መልኩ በሕግ ተለይቶ የተደራጀ መሆኑ በከተሞች ተጠያቂነትንና ግልጽነትን ለማስፈን ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በከተሞች የግልፅነትና የተጠያቂነት አሠራር እንዲኖርና ብሎም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚቻለው ግን የተደነገገው ሕግ በአግባቡ ተግባራዊ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በክልሎች የከተሞች ማቋቋሚያ አዋጅ ከወጣ በኋላ ከአዋጁ መመንጨት የሚገባቸው ደንቦችና ዝርዝር መመሪያዎች ወቅታቸውን ጠብቀው ባለመውጣታቸውና ሰነዶቹም ለሕዝብ ይፋ ባለመሆናቸው የክልል ከተሞች ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነትና ግልጽነት ያለውን ሥርዓት ለማስፈን አልቻሉም፡፡ በሌሎችም ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው ችግር ደንቦቹና መመሪያዎቹ እያሉም ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ያለማስተካከልና የከተማውን ባሕሪ በሚያንፀባርቅ መልኩ አለመከለስ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ከተሞች የተለያዩ ጊዜ ያለፈባቸውን ደንቦችና መመሪያዎች ይጠቀማሉ፡፡ ይብዛም ይነስም በሁሉም የክልል ከተሞች የተለያዩ ህጎችና ደንቦች መኖራቸው ግን አልቀረም፡፡ ሁለተኛው ችግር የወጡ ሕጎችን ህዝቡ እንዲያውቃቸው የሚደረግበት ሥርዓት አለመኖሩ ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የሚታየው ችግር በአስፈፃሚ አካላት የወጡ አሠራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ያለ የግንዛቤ፣ የተነሳሽነትና የዝግጁነት እናሳነት ነው፡፡ ደንብና መመሪያ እያለም በሠራተኛው የአቅምና የግንዛቤ ማነስ፣ እንዲሁም በተነሳሽነትና በአመለካከት ችግር የተከሰቱ ችግሮች ያሉ ሲሆን በአንዳንድ ከተሞችም አሠራር በፈጠረው ክፍተት የተነሳ የሚፈፀም የሥነምግባር ጉድለት እንዳለ ተስተውሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሁሉም ክልሎች በመሬትና ከመሬት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እንዲሁም በታክስ አሰባሰብ ዙርያ ያለው የሙስና ሁኔታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በከተሞች በተደጋጋሚ የሚከሰቱት በመሬት ይዞታና ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ ደንቦችና መመሪያዎች በሚፈጥሩት ክፍተት እና በሚታዩት የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ምክንያቶች እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኃላፊነቶችንና ተግባራትን ግልፅ የሚያደርጉ ደንቦችና መመሪያዎች ባለመኖራቸው እና ልማታዊ አስተሳሰብ አስተማማኝ የበላይነት ባለመያዙ ሳቢያ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር እንዳይኖር አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡

መልካም አስተዳደርን ከማረጋገጥ አኳያ በአንድ ከተማ ከሁሉ በፊት ነዋሪዎችን ያሳተፈ የዕቅድና የበጀት ዝግጅት መኖር እንዳለበት ይታመናል፡፡ በዚህ ረገድ በአንዳንድ ከተሞች የዕቅድና የበጀት ዝግጅት በተወሰነ ደረጃ ተሳትፎ የተደረገበት ቢሆንም ዘላቂነት ባለው የአሠራር ስርዓት ተግባራዊ እየተደረገ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተወሰኑ

ከተሞች የከተማ አስተዳደሮች የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅዶቻቸውን በየደረጃው የኅብረተሰቡን አካላት የማወያየትና በምክር ቤቶቻቸው የማፀደቅ ተሞክሮዎች እያዳበሩ መሆናቸው በጎ ልምድ ነው፡፡ በከተሞች የሚዘጋጀው ዕቅድና በጀት በአብዛኛው ለሕዝብ ይፋ የሚሆንበት የአሠራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ የፋይናንስ፣ የበጀትና የኦዲት ሪፖርቶችን ነዋሪዎች እንዲመክሩበትና እንዲወያዩበት አይደረግም፡፡ ይሁንና በአንዳንድ ከተሞች የከተማውን የመገናኛ ብዙኃን በመጠቀም ነዋሪዎቹ በወቅታዊ የከተማ ጉዳዮች ላይ የሚወያዩበትና የሚያውቁበት አሠራር መኖሩ ለግልፅነትና ለተጠያቂነት አስተዋጽኦ ማድረጉ የታየ ቢሆንም ይህ ተግባር በሁሉም ከተሞች እየተሠራበት እንዳልሆነ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በሁሉም የክልል ከተሞችና የከተማ አስተዳደር የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በሩብ ዓመቱ ለየምክር ቤቶቻቸው ቢያቀርቡም ለነዋሪውም ሆነ ለሚመለከታቸው አካላት በተገቢው ሁኔታ አይገለፅም፡፡ በከተሞች የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን የአፈፃፀም ሪፖርት ለከተማው ነዋሪ የሚቀርብበት ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሕብረተሰቡ ስለ ገቢ ዕቅድ፣ በግብር አወሣሠን አካሄድና አፈፃፀም ግልፅ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት መረጃዎችን የሚያገኝበት ዘዴዎች በሁሉም ከተሞች በወጥነት አልተቀየሰም፡፡ በከተሞች ግልፅነትና ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተወሳሰቡ ችግሮች የሚታዩ መሆኑን የዳሰሳ ጥናቶቹ ያመለክታሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በከተሞች ትክክለኛ የሆነ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ አለመኖርና በአግባቡ የኦዲት ሥራ አለመከናወኑ ዋንኞቹ ችግሮች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የግብር አወሳሰንና አሠባሰብን በተመለከተ በአንዳንድ ከተሞች ግልፅ የሆነ ደንብና መመሪያ ካለመኖሩም በላይ የንብረትና ግዥ፣ የኮንትራት አስተዳደር እንደዚሁም የመሬትም ሆነ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ግልፅነት የጐደላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የአሠራር ሂደቶች ሙስና የሚታይባቸውና ተገልጋዩ ሕብረተሰብም የሚያውቃቸው ናቸው፡፡ በመንግሥት ሥራ አስፈፃሚ አካላትና በሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛው ለሚፈፅመው ጥፋትም አጥፊዎች የሚጠየቁበት ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት የለም፡፡ ስለዚህ በከተሞች መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ለከተሞች ዕድገት ወሳኝ ሚና ስለሚኖረው እነዚህን ጉዳዮች በውል ተገንዝቦ መፍትሄ መሻት አስፈላጊ ነው፡፡

## 4. የከተሞች የሕዝብ ተሳትፎ

በከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ የሕዝብ ተሳትፎ የታየ ሲሆን፣ አሁንም ድረስ ሕዝቡ በልማትና በአስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እያደረገ ያለው የቀጥታ ተሳትፎ በሚፈለገው መጠን አልጎለበተም፡፡ ሆኖም ሕዝቡ በሚኖርባቸው ከተሞች የራዕይ ቀረፃ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅትና አመታዊ እቅዶች ዝግጅትና ትግበራ ላይ የነበረው ተሳትፎ ባለፉት አመታት መጠነኛ መሻሻሎች አሳይቷል፡፡ በከተሞች ዘላቂ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ በአካባቢያዊ ልማትና በጽዳት ሥራዎች፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር፣ በፀጥታና በሌሎችም ማኀበራዊ አገልግሎቶች ዙርያ የሚንቀሳቀሱ በርካታ የሕዝብ አደረጃጀቶች አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የብዙሃን፣ የሲቪክና የዘርፍ ማኀበራት አደረጃጀቶች በልማት ሥራዎች ዙሪያ ያላቸው ተሣትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ የግሉ ሴክተር በሚደረጉ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴዎች በተደራጀ መንገድ አለመሳተፉና ለከተማ እድገት የግል ባለሃብት የማይተካ ሚና እንዳለው ተገንዝቦ የከተሞች ልማት ወሳኝ ድርሻውን እንዲወጣ የሚያደርግ ወጥ ሥርዓት እስካሁን በአስተማማኝ ሁኔታ አልተዘረጋም፡፡ በሁሉም ዘርፎች ሴቶች ያላቸው የተሳትፎ ውሱንነት ከመሠረቱ ለመለወጥ ልዩ ትኩረት ሊሠጠው የሚገባው ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ ወጣቶች በአካባቢያቸው የልማትና የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ በሚፈለገው ደረጃ ገንቢ ሚና እስካሁን ሊጫወቱ አልቻሉም፡፡

ስለሆነም በጅምር ላይ ያለውን የሕዝቡን የቀጥታና የኅብረተሰቡን የተለያዩ አካላት የተደራጀና የነቃ ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ግልፅ ሥርዓት ማስቀመጥና በፍጥነት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት ያሻል፡፡

በሃገሪቱ በ1997 እና በ2000 ዓ.ም በተካሄዱ ምርጫዎች በከተሞችም ያለው ሕዝብ ተወካዮቹን ለመምረጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረገባቸው ሆነው አልፈዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የከተማ አስተዳደሮች የከተማውን ሕዝብ የሚወክሉ የከተማና እንደከተማው ተጨባጭ ሁኔታ በየደረጃው ደግሞ የክፍለ ከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች ተቋቁመዋል፡፡ የእነዚህን ምክር ቤቶች አሰራር ሥርዓትና አደረጃጀት ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን፣ እንዲሁም የአባላት ሥነ-ምግባር ምን ሊመስል እንደሚገባ የሚደነግጉ ደንቦች በፌደራል ደረጃ ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የከተማ እና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንቦች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የምክር ቤቶቹን አቅም በመገንባት የወከላቸውን ሕዝብ በአግባቡ የሚያገለግሉ፣ ድምፁን የሚያሰሙና ለልማት የሚያንቀሳቅሱ የማድርግ ሥራዎች ተኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

## 5. በከተሞች የሕግ በላይነትና የደህንነት ዋስትና

የሕግ የበላይነትን ማስከበር ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ቁልፍ ነው፡፡ ለሕግ የበላይነት መከበርም የፍትህ አካላት እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው በመደራጀት በቂና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት መቻላቸው ወሳኝ ነው፡፡ የከተማ ፍርድ ቤት ባለባቸውም ሆነ በሌለባቸው አካባቢዎች ተዘዋዋሪ ፍርድ ቤቶች ትርጉም ያለው ሥራ በመስራት ላይ የሚገኙ ቢሆንም የፍትህ አገልግሎት ለነዋሪው ተደራሽ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ሲታይ ሰፊ ስራ በቀጣይነት መስራት መቻል አለበት፡፡ በከተሞች አሁንም የፍትህ እጦትና እንግልት እንዳለ በከተሞች የተደረገው የዳሰሳ ጥናት ያመለክታል፡፡ ለአመታት ሳይታዩ የቆዩና የተከማቹ ፋይሎች በርካቶች ናቸው፡፡ በዳኞች የሥነ-ምግባር ችግሮች፣ የፍትህ ማዛባት፣ ከሙስና ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የአገልጋይነት አመለካከት አለመኖር እንዲሁም የሰው ኃይል እጥረትና የአቅም ውሱንነት ችግሮች ይታያሉ፡፡ የከተማ ፍርድ ቤቶች በከተማ ደረጃ ማደራጀት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ላይ የሚደርሰውን የሥራ ጫና በማርገብ ፍትሕን ተደራሽና የፍርድ ሂደትን ቀልጣፋ ያደርጋል፡፡ በከተሞች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ በሕግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት መካከል የከተማ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች፣ የግብር ይግባኝ ጉባኤ፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳሰሳ ጥናቱ በተከናወነበት ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቁመው ለፍትህ ሥርዓት መጠናከር አመርቂ ሚና መጫወት መቻላቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም ከተማ-ነክ የሆኑና አነስተኛ ጉዳዮች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች እየሄዱ በፍትህ ሥርኣቱ መጨናነቅን ከሚፈጥሩ ይልቅ እላይ በተጠቀሱ ፍርድ ቤቶች አማካይነት እንዲታዩ ቢደረግ የፍትህ አገልግሎቱን ለማሻሻል ሊያግዝ ይችላል፡፡ ስለሆነም ሌሎች ክልልሎችም እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አጣጥመው አደረጃጀቶቹን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ሁኔታ ቢመቻች ለፍትህ ሥርዓቱ መሻሻል አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ እነዚህ የፍትህ አካላት ምንም እንኳን ነፃ ሆነው እንዲሠሩ የተደራጁ ቢሆንም ተቋማቱ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በሚሠጡበት መንገድ ያላቸውን የሰው ኃይል፣ አሠራርና አደረጃጀት በመፈተሽ ማጠናከር ካልተቻለ አሁን ባሉበት ሁኔታ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በማስፈፀም በኩል በርካታ የአቅምና የዝግጁነት ችግሮች ያሉባቸው ናቸው፡፡

በተጨማሪም የፍትህ አካላት ሁለንተናዊ አቅምና ዝግጁነትን ማሳደግ፣ የሥነ-ምግባር ደንቦችና አሠራሮችን መዘርጋት፣ እና በየመድረኩ ያሉትን ችግሮች በማቅረብ የከተማ ነዋሪው እንዲሳተፍ በማበረታታትና ነዋሪው ሙስናና አድልዖን የማይሸከም እንዲሆን ግንዘቤውን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በከተሞች የፀጥታ አስከባሪ አካላት አወቃቀርን በተመለከተ የተደረገው ጥናትም በተመሳሳይ ሁኔታ የፍትህ ሥርዓቱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድና የነዋሪውን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ነገር ግን ከፍተኛ የዘመናዊ አሠራር፣ የሰው ኃይል ብቃትና የቁሳቁስ ችግር በስፋት ይታያል፡፡ የፖሊስ መዋቅር አደረጃጀት እስከ ቀበሌ (ማዘዥያ ጣቢያ) ድረስ የተዘረጋ አይደለም፡፡ በከተሞች ካሉት ወንጀሎችና ሕገ-ወጥ ድርጊቶች መስፋፋት አኳያ ሲመዘን አደረጃጀቱን የበለጠ ያልተማከለ የማድረግ ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በከተሞች በተደጋጋሚ የሚታዩትን የወንጀል ተግባራት አስቀድሞ በመለየትና ሕብረተሰቡን ባሳተፈ ሁኔታ በመከላከል በኩል የፖሊስ እንቅስቃሴ መጠናከር እንደሚገባው ይታመናል፡፡ በመዋቅሩ ያለው የሰው ኃይል ውስን መሆንና በሕዝብ አደረጃጀቶች በሚፈለገው ደረጃ የተደገፈ አለመሆን ችግሩ እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም የከተማ ነዋሪውን ሰላማዊ ኑሮና ደህንነት በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲቻል ወንጀልን የመከላከልና የመቆጣጠርን ሁለንተናዊ አቅም ማጠናከር ይገባል፡፡

በአካባቢ ኮምዩኒቲ ፖሊሲንግ አደረጃጀት በኩልም በአንዳንድ ከተሞች የአካባቢው ነዋሪ ተደራጅቶ የአካባቢውን ፀጥታ እራሱ የሚጠብቅበት ሁኔታ እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩልም ነዋሪው እንደየአቅሙ በየወሩ ለፀጥታ ሥራ ገንዘብ በማውጣት አካባቢው እንዲጠበቅ የሚያደርግበት ሁኔታም አለ፡፡ ይሁንና ይህ መልካም ተሞክሮ ተጠናክሮ የከተማው ነዋሪ ዙሪያ መለስ ተሳትፎ የተረጋገጠበት ጠንካራ የአካባቢ ፖሊሲንግ አካሄድ ስርአት በየደረጃው እንዲቋቋም ቢደረግ ለከተሞቻችን ለውጥ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በተመሳሳይ በከተሞች ያለው የሥራ አስፈጻሚ አካል ለሕግ የበላይነት በቁርጠኝነት የቆመ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን የሚከላከልና የሚቆጣጠር መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህም ረገድ በከተሞች የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም አናሳ ተቋማዊና የሰው ኃይል አቅም ውጤቱን የሚፈለገውን መጠን እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ በመሆኑም በከተሞች ሕገ-ወጥ የንግድ ሥራዎች፣ ልዩ ልዩ ደንብ መተላለፎች፣ ሕገ-ወጥ የመሬትና የመንግስት ቤት ይዞታ ሯ ወዘተ ይስተዋላሉ፡፡ እንደዚሁም በአንዳንድ አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሙስና ወንጀልና የሥነ-ምግባር መጓደል ችግሮች ይታያሉ፡፡ ስለሆነም ለሕግ የበላይነት በቁርጠኝነት የቆመ የሥራ አመራርና ሠራተኛ መፍጠር፣ ሕገ-ወጥነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተቋማት፣ አሰራሮችና ደንቦች ማሟላት፣ እንደዚሁም ሙስናና የስነ-ምግባር ችግር የሚፈጽሙትን በፍጥነት ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡

የዜጎችን ማኅበራዊ ዋስትና በማረጋገጥ ነዋሪው በመንግስት እምነት እንዲኖረውና ተረጋግቶም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውን እንዲመራ ከማድረግ አኳያ በተለይም በከተሞች የነዋሪው በመሬት የመጠቀም ዋስትና በሕገ-መንግስቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት የተረጋገጠ መሆኑ አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የከተሞች የልማት ሥራዎች ማዕከል ድህነትንና ሥራ አጥነትን ማቃለል መሆኑና በከተሞች የሥራ ዕድልን ለመፍጠር በብድር አቅርቦት፣ በማምረቻ ቦታ፣ በገበያ ትስስርና በመሳሰሉት የድጋፍ ዓይነቶች የተጀመረው እንቅስቃሴ የከተማ ነዋሪውን ማህበራዊ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስለሆነም በአገሪቱና በክልሎች ሕጎች የተደነገጉትን የነዋሪውን ደህንነት የሚያረጋግጡ ሕጎች አጠናክሮ መተግበር፣ ልማትን በማፋጠን እና ድህነትን በመቀነስ ረገድ አመርቂ ውጤት ያስገኙትን የከተማ ልማት ዕቅዶቻችንን በተሻለ ፍጥነት መፈጸም ይገባል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም

### I. የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም የፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫዎች

በኢትዮጵያ ከተሞች በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በዚህ ሰነድ ተዘርዝረው ይቀርባሉ፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች ተዛማጅ በከተሞቻችን የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለማሻሻል እንዲቻል ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ተግባራዊ በመሆን ላይ ያለው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም መነሻ ያደረጋቸውን የኢትዩጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የከተማ ልማት ፖሊሲ፣ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች ሰነድ፣ የማስፈጸሚያ አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች፣ የአምስት ዓመቱ የልማትና የድህነት ማስወገጃ ዕቅድ፣ የከተሞች የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅ፣ እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ ሥራ ላይ የዋሉ አዋጆችን ነው፡፡ በተጨማሪም በሃገር አቀፉ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ በመተግበር ላይ የሚገኙት የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም፣ የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም፣ የበላይ አመራር ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም እና የመንግሥት የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም በዝርዝር በመመልከት ከመልካም አስተዳደር ሥራዎች ጋር በተቀናጀ አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ እንደ አበይት መነሻዎች ተወስደዋል፡፡

እንዲሁም ይህ ፕሮግራም ኢትዩጵያ የተቀበለቻቸውን አለም ዓቀፍ የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦችን ለማሳካት እየተደረገ ያለውን ጥረትም ግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ፕሮግራሙ መሰረት አድርጎ የተነሳባቸው ዋና ዋና የፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 1. ለመልካም አስተዳደር መሻሻል ትልቅ ፋይዳ ባላቸው ሥራዎች ላይ ማተኮር

በሁሉም የከተማ ሥራዎች ላይ የሚታዩትን የአስተዳደር ችግሮች በሚቀጥሉት ቀሪ የፕሮግራም አመታት በዚህ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም አማካይነት ሙሉ በሙሉ ለመፍታት ያለው አቅም ውሱን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተካተቱት ሥራዎች በከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ እሮሮ የሚታይባቸውና ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉት ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ከከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር እና ፕላን ጋር የተያያዙ ሥራዎች፣ በተለይም የመሬትና መሬት-ነክ መረጃ ሥርዓትን ከማጠናከር አኳያ መንግሥት የተለየ ተኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀስባቸው ናቸው፡፡ ለመሬት የመረጃ ሥርዓት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት፣ በከተሞች ለልማት የተመቻቸ ሁኔታና ከፍተኛ የመልካም አስተዳደር ለውጥ ለማስመዝገብ ጥረት ይደረጋል፡፡

እንደዚሁም በታክስና ፋይናንስ አስተዳደር ዙሪያ የሚታየውን ለልማት ያልተመቻቸ ሁኔታ የመቀየር ተግባር በዚህ ፕሮግራም ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በተያየዘም ሃገሪቱ ከምትመራበት የፌደራል ሥርዓት የሚመነጨው ስልጣንና ኃላፊነትን እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን የማውረድን መርሆ ለማረጋገጥ እንዲቻል ከተሞች አስተማማኝ የፋይናንስ አቅምና ፋይናንሱን የማስተዳደር ሙሉ መብትና አቅም እንዲጎናፀፉ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት የከተሞች የታክስ ሥርዓትና የፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍም በፕሮግራሙ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶቶት የሚከናወን ሥራ ነው፡፡ በከተሞች የአስፈፃሚ ተቋማትን አቅም የመገንባትና በተለያዩ ደረጃ ያለ የከተሞች ምክር ቤቶችን ጨምሮ አመራሩንና ባለሞያዎችን የማብቃት ተግባራት በፕሮግራሙ ሌላው የሚከናወን ሰፊ ሥራ ነው፡፡ የፍትህ ሥርዓቱን በአጠቃላይ በማሻሻል የሕግ የበላይነትን ለማስፈንና የነዋሪዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ፡ አገልግሎት አሰጣጡ ከአድሎዓዊ አሰራርና ከሙስና የጸዳ ለማድረግ በፕሮግራሙ አማካይነት የተቀናጀ ጥረት ይደረጋል፡፡ የእነዚህ ተግባራት የተሣካ አፈጻፀም የከተማ መልካም አስተዳደር ሁኔታን ለማሻሻል እና ፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሃዊ ልማት ለማረጋገጥ የሚደረጉትን ጥረቶች ለማሳካት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይታመናል፡፡

## 2. በከተማ ልማት ፖሊሲ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱት ንዑስ-ፕሮግራሞቸ በከተማ ልማት ፖሊሲ ውስጥ የተካተቱትን የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተደዳር፣ እንዲሁም የተጠናከረ የከተሞች አቅም ግንባታ አቅጣጫዎችን የተከተሉ ናቸው። በከተማ ልማት ፖሊሲው በግልጽ እንደተመለከተው የከተማ ልማታችን ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂነት ያለው ሊሆን የሚችለው በከተሞች መልካም አስተዳርና ዲሞክራሲ ሲሰፍን ነው። በአንጻሩም አስተማማኝ መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ያለፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂ ልማት የሚታሰብ አይሆንም። ስለሆነም ሁለቱንም አቀናጅቶ ለመፈጸም እንዲቻል የከተማ ልማት ፖሊሲውን መሠረት በማድረግ የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሙና የከተማ ልማት ፓኬጁን አስተሳስሮ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅተዋል።

## 3. ዋና ዋና የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ

በፕሮግራሙ የተካተቱ ንዑስ-ፕሮግራሞች ከላይ የተገለጹትን የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ለማረጋገጥ የተዘጋጁ ናቸው። ስለሆነም የከተማ የመሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ፣ የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ እና የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራሞች ያልተማከለ የስልጣን ተዋረድና ኃላፊነትን፣ የሕዝብ ተሳትፎን፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትን፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነትን፣ እና የሕግ የበላይነትን መርሆዎችን የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል።

# II. የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም ጥቅል ዓላማዎችና ግቦች

## 1. የፕሮግራሙ ጥቅል ዓላማዎች

- በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ በማሻሻል በከተሞች ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥና በዚህም የከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ፣
- የከተሞች አስተዳደርን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ከተሞች ቀጣይነት ያለው ዘርፈ-ብዙ ልማት ማስተናገድ የሚችሉ ማዕከላት እንዲሆኑ ለማድረግ፤ በገጠሩ አካባቢ እየተመዘገበ ያለውን ልማት በመደገፍ ፍትሃዊ፣ ፈጣንና ዘላቂ ሃገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ለማረጋገጥ፣ እና
- በከተሞች የተሻለ የአስተዳደር ሁኔታ ለማስፈንና የከተማ ነዋሪዎችን የስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ነው።

## 2. የፕሮግራሙ ጥቅል ግቦች

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማሳካት እንዲቻል የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች በመነሳት ጥቅል ግቦችን አስቀምጧል። ከዚህ አንጻር በቀሪዎቹ የፕሮግራም አመታት በመሬትና ፕላን ሥርዓት፣ በታክስና ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት እና በተቋማት የማስፈጸም አቅም ረገድ የሚከተሉት ግቦች ላይ ለመድረስ አልሟል።

**ግብ አንድ**

ከተሞች በቂ የሕግ ድጋፍና ነጻነት ኖሯቸው የሚቋቋሙ እና የከተማ ሥራን በሥርዓት ለመምራት የሚያስችሉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተሟልተው የሚገኙባቸው፣ ያልተማከለ የአደረጃጀት ስርዓት የሚከተሉና በተዋረድ የመወሰን ስልጣናቸውን ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን በማውረድ የሚተዳደሩ ይሆናሉ፡፡

**ግብ ሁለት**

ከተሞች ከአምስት ዓመቱ የልማትና የድህነት ማስወገጃ ዕቅድ አንጻር ከነዋሪዎቻቸው የሚጠበቅባቸውን ፈጣንና ፍትኃዊ ልማትን ለማረጋገጥ እንደዚሁም ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል የፋይናንስ፣ የሰው ኃይልና ተቋማዊ አቅም ይኖራቸዋል፡፡

**ግብ ሦስት**

ከተሞች በተጠቃሚዎች እርካታ ላይ ያነጣጠረና በቀጣይነት የሚሻሻል ቀልጣፋ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ ሁለገብ አገልግሎት በየደረጃው መስጠት ይጀመራሉ፡፡

**ግብ አራት**

በሀገሪቱ ከተሞች የሚመጡ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ዕቅዶችና በጀት ከዝግጅታቸውም ጀምሮ ህዝቡ በስፋትና በንቃት የሚሳተፍባቸው እና አፈጻጸማቸውም በቀጣይነት የሚገመገማቸው ይሆናል፡፡

**ግብ አምስት**

የከተማ አስተዳደሮች ሕዝቡ በቀላሉ ሊያየው፣ ሊረዳው ሊያርመው የሚችል ግልጽ መመሪያ እና የአሰራር ስርዓት የሚከተሉ፤ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋትም ፈጣን ተጠያቂነታቸውን የሚያረጋግጥ ሥርዓት የተዘረጋባቸውና በአጠቃላይ ከሙስናና ሕዝብን ከማጉላላት አሠራር የፀዱ ይሆናሉ፡፡

**ግብ ስድስት**

ከተሞች የሕግ የበላይነትና የነዋሪዎቻቸው ደህንነት የተረጋገጠባቸው፤ የከተሞችን የተለየ ባህርይ ግምት ውስጥ ያስገባ የዳኝነት ሥርዓት የተዘረጋላቸው፣ ወንጀልንና ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን ለማክሰም የሚያስችል ስርዓት፣ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ አመራርና ባለሙያ ያላቸው ይሆናሉ፡፡

ከላይ የተገለጹት ጥቅል ዓላማዎችና ግቦች በፕሮግራሙ አማካይነት በሚከናወኑ ማሻሻያዎች ድምር ውጤቶች የሚያመለክቱ ሲሆን በየንዑስ ፕሮግራሙ የሚኖሩ ዓላማዎችና ግቦች ደግሞ በሚቀጥለው ክፍል በየንዑስ-ፕሮግራሙ ቀርበዋል፡፡

## III. የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም

**ዓላማ**

የመሬት ልማትና አስተዳደር እንዲሁም የከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አፈፃፀም ግልፅ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ፍትሃዊና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲከናወን በማስቻል በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን ለማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር ነው፡፡

የሚከተሉት አራት ፕሮጀክቶች በንዑስ-ፕሮግራሙ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ሀ. የመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ፕሮጀክት

ለ. የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

ሐ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

መ. የከተማ ፕላን የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት

## ሀ. የመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

በዘመናዊ የኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የሚታገዝ የተቀናጀ የመሬትና መሬትጠነክ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የከተማ ልማትና አስተዳደር ሥራን ውጤታማነትና ቀልጣፋነት በማረጋገጥ በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭን ለማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡

**ግብ አንድ**

የመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ሥርዓት የሕግ ማዕቀፍ፣ የተቋምና የአሠራር ሥርዓት ተዘጋጅቶለት በከተሞች ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ተግባር 1 በረቂቅ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ እና ማቋቋሚያ አዋጆች፣ የካዳስተር ቀያሽ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅና አፈጻጸም ደረጃ መወሰን ደንብ ላይ ማስተካከያ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ፣

ተግባር 2 በከተሞች ሕጋዊ ካዳስተር (legal cadastre) ለመገንባት የቤዝ ማፕ ዝግጅትን/ወቅታዊ የማድረግ ሥራን ማከናወን፣

ተግባር 3 የመሬትና መሬት ነክ ንብረት የመረጃ ሥርዓት በከተሞች ተግባራዊ የሚሆንበት የቴክኖሎጂና የመረጃ ኢንፍራስትራክቸር የአፈጻጸም ደረጃ በጥናት መወሰንና የመሬት መረጃ ሶፍትዌር ማዘጋጀት፣

ተግባር 4 ለምዝገባ ሥራ የሚያገለግሉ መመሪያዎችና የምዝገባና የካዳስተር ቅየሳ አሠራርና የመረጃ አጠቃቀም ስታንዳርድ ማንዋሎች ማዘጋጀት፣

ተግባር 5 ሕጋዊ ካዳስተር (Legal cadastre) የሚመራ፣ የሚያስተዳድርና የሚከታተል አካል በፌዴራል፣ በክልልና በሕዝብ ብዛታቸውና የልማትና የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም አፈፃፀም ብቃታቸው በተመረጡ 20 የከተማ አስተዳደሮች በአዋጅ ማደራጀት፣

ተግባር 6 ከአንድ የከተማ መሠረታዊ ካርታ የሚዘጋጀው ሕጋዊ የካዳስተር (Legal cadastre) ማፕ ለሌሎች የከተማ ካዳስተርና መረጃዎች (ለታክስ፣ መሠረተ-ልማት፣ ፕላን፣ ወዘተ...) መነሻ ግብዓት እንዲሆን በጥንቃቄ ማዘጋጀትና የመረጃው ጥራትና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ የሚጠበቅበትን ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 7 በመሬትና መሬት-ነክ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር የተሰማሩ ባለሞያዎችና የሥራ ኃላፊዎች የሚተዳደሩበት የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተፈፃሚ ማድረግ፣

ተግባር 8 በመሬትና መሬት-ነክ መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መስራት፣

ተግባር 9 ብቃትና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የሰው ኃይል በጥንቃቄ መልምሎ በመረጃ ሥርዓት አስተዳደር መዋቅር ማሰማራት፣ ለዚህም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በከተማ ሥራ አመራር በማስተርስ ዲግሪ የሚመረቁትን በዋናነት መጠቀም፣

ተግባር 10 ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የመሬት መረጃ ሥርዓትን በተመለከተ አጫጭር ሥልጠናዎች በቋሚነት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

ተግባር 11 የሚመለከታቸው አካላት ከኢንፎርሜሽን ኔትዎረክ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመሆን የሚደራጀው መረጃና ኔትዎረክ ጥራትና ደህንነቱ አስተማማኝ መሆኑን በየደረጃውና በየጊዜው ማረጋገጥ፣

ተግባር 12 ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ዋና ከተሞችን ጨምሮ የአነስተኛና የመካከለኛ ከተሞች የመሬትና የመሬት-ነክ መረጃ ፍላጎታቸውን በመለየት የመሬት ምዝገባና መረጃ አያያዝ ሥርዓት ለመዘርጋት (የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የአደረጃጀት፣ ወዘተ) የልማት ፕሮግራም መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ ከተመረጡ ፓይለት ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት ለተለያዩ ከተሞች ተስማሚ የሆነ ተቋማዊና የመረጃ ኢንፍራስትራክቸር መረጣ በማድረግ መገንባት፡፡

**ግብ ሁለት**

የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫና ግብይት፣ እንዲሁም የመሬት አስተዳደር ሥራ በትክክለኛ መረጃና አሰራር የተደገፈ ይሆናል፡፡

ተግባር 1 የንብረት ግምትና የግብር አሠራር ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 የመሬትና ንብረት ዝውውር እንዲሁም ባለቤትነት ማስረጃ ተገቢ የአሰራር ሥርዓት ተቀምጦለት በወቅቱ ተመዝግቦ የሚሰራበትን መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3 ከመሬት ገበያው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቅርብ ለተቆራኙ መሬት ነክ መረጃ ፈላጊዎች የሚደርስበት አሰራር መፍጠር ፣

ተግባር 4 ልዩ ልዩ የማስታወቂያና የማስተማሪያ መድረኮች በመፍጠር ሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

ተግባር 5 የንብረት ግምት አሠራር ፣ ባለቤትነት ማረጋገጫና የንብረት ዝውውር አሠራር አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣

ተግባር 6 የተገኙ ጠቃሚ ልምዶችን በመለየትና በመቀመር የሰለጠነ የሰው ኃይል በማደራጀት በቀጣይ በሌሎች ከተሞች ተከታታይ ሥራ የሚከናወንበት ስትራቴጂና ኘሮግራም መቅረፅ፣

ተግባር 7 በከተሞች የመሬት መረጃ ሥርዓት አፈጻጸም ሂደትን መከታተል፣ መደገፍ፡፡

## ለ. የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

በከተሞች የሊዝ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት፣ አቅርቦቱን ፍትሐዊና ቀልጣፋ ማድረግና ውሱን ሃብትን በአግባቡ በመጠቀም ልማትን ማፋጠን፡፡

**ግብ አንድ**

የሊዝ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የተሟላ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የከተማ አስተዳደር በተቋቋመባቸው ከተሞች ሥራ ላይ እንዲውልና በቀጣይነትም እንዲሻሻል ማድረግ፡፡

ተግባር 1 በክልሎች የተዘጋጀው የሊዝ ደንብ ሁሉም ከተሞች በሊዝ ሥርዓት ብቻ እንዲተዳደሩ በመደንገግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ መስጠት፣

ተግባር 2 የሊዝ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ በሆነባቸው ከተሞች በምሪት ይዞታ የሚተዳደሩ መሬቶች ወደ ሊዝ ሥሪት የሚሸጋገሩበትን የአፈፃፀም ስትራቴጂ በመንደፍ ለክልሎች ማስተላለፍ፣ ለተግባራዊነቱም ድጋፍ መስጠት፣

ተግባር 3 የሊዝ ሥርዓትን በተመለከተ በተለያዩ የኅብረተሰብና አስፈፃሚ አካላት ያለውን የተሳሳተ አመለካከት የማጥራት ተግባራትን በማከናወን የጋራ ግንዛቤ መፍጠር፣

ተግባር 4 በከተማ አስተዳደሮች አዲስ የሚሰጥ መሬት በሊዝ ሥርዓት እንዲሆን ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት ለክልሎች ማሰራጨትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣

ተግባር 5 ጨረታ መሬት በሊዝ የሚቀርብበት ብቸኛው አሠራር እንዲሆን ማድረግና አሠራሩን ግልፅና በመደበኛነት የሚከናወን ለማድረግ በማፕ የተደገፈ፣ ጨረታ ስለወጣበት አካባቢ የተሟላ መረጃ በተለያየ ሚዲያና አግባብ የሚሰጥ እና በማዕከል በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ማድረግ፣

ተግባር 6 በሊዝ የተወሰደ የከተማ መሬት ላይ ግንባታ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም በሊዝ ላይ የሚከፈለውን ቅድመ-ክፍያ ወጥ ማድረግ፣

ተግባር 7 ለኢንቨስትመንት የሚሰጡ ቦታዎች የመጠንና የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ስታንዳርዶች ማዘጋጀት፣

ተግባር 8 ለኢንቬስትሜንት የሚቀርብ መሬት ንብረቶች ያልሰፈሩበትና የይገባኛል ክርክር የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥና የሳይት ፕላን በማዘጋጀት ለተጫራቾች ማሳወቅ፣

ተግባር 9 የሊዝ መነሻ ዋጋ መለኪያ ስታንዳርድ እና የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ክልሎች አጽድቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት**

የከተማ መሬት አቅርቦቱ ግልፅ ቅደም ተከተል እና የአፈፃፀም ሥርዓት ኖሮት መፈፀም ይጀምራል፡፡

ተግባር 1 ለቤት ልማት የሚሰጥ የከተማ መሬት ቅድሚያ ለተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ መስጠት፣ የኮንዶሚኒየም ግንባታ በሚካሄድባቸው ከተሞች ለማኅበራትና ለግለሰቦች በቀጥታ ማደልን ማስቆም፣ እንዲሁም በመካከለኛና ትላልቅ የግል ሪል ስቴት ኩባንያዎች ለሚገነቡ የመኖሪያ ሕንፃዎች የሚቀርብ ቦታ በጨረታ፣ የከተሞቹን ፕላንና የከተማውን የሽንሻኖ ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 2 በግል ሪል ስቴት ኩባንያዎች ለሚገነቡ የቢዝነስ ሕንፃዎችና ሆቴሎች የሚቀርብ ቦታ በጨረታ፣ የከተሞቹን ፕላንና የከተማውን የሽንሻኖ ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 3 ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቬስትሜንት የሚውል የኢንዱስትሪ ዞን ዝግጅት በመሬት ፍላጎት ላይና በከተሞቹ የማደግ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄና የተሟላ መመሪያ ኖሮት እንዲፈፀም ማድረግ፣ የመሠረተ-ልማት የተሟላለትና ለዚህ ጉዳይ የወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 4 ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ክላስተሮችን ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሰጠው የከተማ ቦታ የመሠረተ-ልማት የተሟላለትና ለዚህ ጉዳይ የወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 5 በቀጣይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የሚቀርብ የከተማ ቦታ በጥንቃቄ፣ በቁጠባና ከፍተኛ የማምረቻ ቦታ ችግር ላለባቸው ብቻ በግልፅነት ማቅረብ፣

ተግባር 6 መንግሥት ለሚገነባቸው ት/ቤቶችና የጤና ተቋማት የቦታ አቅርቦት ማመቻቸት እና በግል ለሚገነቡ ተመሳሳይ ማኅበራዊ ተቋማት ቦታ በጨረታ ብቻ ማቅረብ፡፡

**ግብ ሦስት**

ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበት ሕግ ማስፈጸሚያ ደንብ፣ የአፈጻጸም መመሪያና ማንዋል የተሟላና ወጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ተግባር 1 ለሕጉ አፈጻጸም የሚረዱ ሞዴል የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀትና ማፀደቅ፣

ተግባር 2 በደንብ፣ በሞዴል መመሪያ እና ማንዋል ላይ እስከታችኛው የአመራር፣ አስፈጻሚ እና የባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር፣

ተግባር 3 የወጡት ሕጎች የተሟላና ወጥ ተፈፃሚነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በየደረጃው ክትትል መኖሩን ማረጋገጥ፣

ተግባር 4 ለእነዚህ ሕጎች ተገዢ የማይሆኑ ዜጎች ላይ በሕጉ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ፈጥኖ በመውሰድ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣

ተግባር 5 ለልማት ከሚውል መሬት ላይ ለሚነሱ ቀድሞ በግብርና ይተዳደሩ ለነበሩ ገበሬዎች ወደ ከተማ እንቅስቃሴ እንዲገቡ የሚያስችል የቢዝነስ ፕላንና ነፃ የማማከር አገልግሎት ማቅረብ፣ እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋት የሚደረገውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**ግብ አራት**

በከተሞች ለልማት የሚፈለግን መሬት ቀድሞ በመለየት፣ በመያዝ እና በማልማት ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

ተግባር 1 ከአገልግሎት በታች የዋሉ መሬቶችን ቀድሞ በመለየት፣ በማዘጋጀት እና በመያዝ (Land Banking)፣ ለተሻለ ልማት ለማዋል የሚያስችል የአሰራር ስልት መንደፍ፣

ተግባር 2 የመሬት ልማትን በተመለከተ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ሞዴል ደንብና መመሪያ ማዘጋጀትና የጋራ መግባባት በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 3 ለማንኛውም ዓይነት ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶችን በማዘጋጀት በንብረት መዝጋቢው ድርጅት (registry) መሬቶቹን ቆጥሮ በማዘጋጃ ቤቱ ስም እንዲመዘገቡ በማድረግ መያዝ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣

ተግባር 4 ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚቀርቡ የቦታ ስፋት መጠን ስታንዳርድ (Optimum Plot Size) እና የሽንሻኖ ሥርዓት መመሪያ ማዘጋጀትና የጋራ መግባባት በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ።

**ግብ አምስት**

በመሬት ላይ የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራትን የማሰቆምና የማስተካከል ሥራ ግልፅ ፣ ፍትሐዊና ከከተማው ኢኮኖሚ ጋር በተሳሰረ ሁኔታ መፈፀም ይጀምራል።

ተግባር 1 በመሬት ላይ በሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተረቀቀው ደንብ እንዲፀድቅና ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ፣ ደንቡ በፀደቀባቸው ክልሎች ደግሞ ተግባራዊነቱን ማጠናከር፣

ተግባር 2 ሕገ-ወጥነትን የሚከላከሉና የሚቆጣጠሩ በየደረጃ የሚገኙ አካላትን አቅም (በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀት፣ በአሰራር፣ ወዘተ...) ማጠናከር፣

ተግባር 3 የመሬት ሕገ-ወጥነትን በተመለከተ በየደረጃው ያለውን የአመለካከት ችግር ለመቅረፍ ለሕብረተሰቡ፣ ለአስፈፃሚ አካላትና ለአመራሩ ትምህርት መስጠት፣

ተግባር 4 የከተማ አመራር ለችግሩ ትኩረት በመስጠት ሕገ-ወጥነትን በመከላከልና በመቆጣጠር ለተሰማሩ አስፈፃሚ አካላት የተጠናከረ ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ፣

ተግባር 5 የተፈፀሙ ሕገወጥ የመሬት ወረራዎችንና ግንባታዎችን የተሟላ መረጃ በመያዝ ማፍረስ፣

ተግባር 6 አዲስ ሕገወጥነትን ሳያበረታታና የከተሞች ፕላን አተገባበርን ሳያደናቅፍ ነባር ሰነድ አልባ ይዞታዎችን መልክ ለማስያዝ የሬጉላራይዜሽን ሕግና ወጥ የሆነ የአፈፃፀም ሥርዓት በማስቀመጥ ተፈፃሚ ማድረግ፣ በዚህም ሰነድ አልባ ይዞታዎች የተሟላ ሕጋዊነት እንዲኖራቸው ማድረግ።

## ሐ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

በመሬት ልማትና አስተዳደር ግልፅና ውጤታማ አደረጃጀትን ተግባረዊ በማድረግ ለተጠቃሚው ብቁ አገልግሎትን በማቅረብ ልማትን ማፋጠን፡፡

**ግብ አንድ**

በመሬት ልማትና አስተዳደር ያሉትን ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች እንዲሁም አደረጃጀቶችን በመፈተሽ ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ ስታንዳርዳይዝ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 የመሬት ልማትና አስተዳደርን በተመለከተ በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ በተለይም በአዲስ አበባ ያሉትን ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች በመፈተሽ ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ ስታንዳርዳይዝ አድርጎ ማቅረብ፣

ተግባር 2 በመሬት አስተዳደር ዙሪያ ለማምጣት ከሚታሰበው መሠረታዊ መሻሻል አንፃር በየክልሉ የተዘጋጁ የመሬት ጉዳይን የተመለከቱ የሥራ ሂደቶች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በወሳኝነት ለመቅረፍ የሚያስችሉ መሆናቸውን መፈተሽና ማረጋገጥ፣

በዚህ መሠረትም፡-

ሀ. ለከተማ መረጃ ሥርዓት እና ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ተገቢውን ትኩረት መስጠታቸውን መፈተሽና በዚሁ መሠረት አደረጃጀቶችን መፍጠር/ማስተካከል/ማጠናከር፣

ለ. ለከተማ መሬት ሊዝ አፈፃፀም ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት መስጠታቸውን መፈተሽና በዚሁ መሠረት አደረጃጀቶችን መፍጠር/ማስተካከል/ማጠናከር፣

ሐ. ለከተማ መሬት ልማትና አቅርቦት ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት መስጠታቸውን መፈተሽና በዚሁ መሠረት አደረጃጀቶችን መፍጠር/ማስተካከል/ማጠናከር፣

መ. ለከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረቶች የካሣ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት መስጠታቸውን መፈተሽና በዚሁ መሠረት አደረጃጀቶችን መፍጠር/ማስተካከል/ማጠናከር፣

ሠ. ለከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር አቅም ግንባታ ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት መስጠታቸውን መፈተሽና በዚሁ መሠረት አደረጃጀቶችን መፍጠር/ማስተካከል/ማጠናከር፣

ተግባር 3 በየደረጃው የሚፈጠሩ አደረጃጀቶች ወጥና በከተማ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን የሥራ መጠንና ስፋት ሊሸከሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

ግብ ሁለት

የመሬት ልማትና አስተዳደር፣ እንዲሁም የመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ አገልግሎቶች በቂ እውቀት፣ ክሕሎትና ቀና አመለካከት በያዘ የሰው ኃይል ይመራል፡፡

ተግባር 1 በመሬት ልማትና አስተዳደር፣ እንዲሁም በመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ የአቅም ግንባታ ስልትና የስልጠና መርሃ ግብር መንደፍ፣

ተግባር 2 የስልጠና ሞጁሎች እንዲዘጋጁ በማድረግ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 3 ስልጠናዎቹን ለበለሞያዎችና ለአመራር አካላት በምዕራፍ መስጠት

- በመሬት ቅየሳ፣ በካዳስተር ሰረቬይንግ፣ በመሬት ነክ ንብረት ዋጋ ትመና፣ በንብረት ግምገማ (Appraisal)፣ በሊዝ ሕግና የአፈጻጸም ሥርዓት አሠራር፣ በመሬት ልማትና አያያዝ (Land Banking) በመሬት መረጃ አያያዝ፣ በመሬት ሊዝ አዋጅና ደንብ፣ በጨረታ አሠራር ስልት፣ በሊዝ መነሻ ዋጋ ስታንዳርድ፣ በካሳ ሕግ፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች፣ ወዘተ…

ተግባር 4 ከሞያ ማሳደጊያ ስልጠናዎች በተጓዳኝ አገልገሎቶቹን በሚሰጡ ሠራተኞችን አመለካከትና ሥነ-ምገባር የማሻሻያ ተከታታይ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት፣

ተግባር 5 የስልጠናውን ሂደትና ውጤት መገምገም፣ ለተከታታይ የአቅም ግንባታ ኘሮግራም ማሻሻያ በግብዓትነት መጠቀም፣

ተግባር 6 በመሬት ልማትና አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ፣ በሊዝ አሰራር፣ በካሣ አከፋፈል፣ በመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ግምት አሠራር የኅብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት መብቱን የሚያስከብር ነዋሪን መፍጠር፡፡

## መ. የከተማ ፕላን የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

በሃገሪቱ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን እንዲሁም የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል አቅም መፍጠር፡፡

ግብ አንድ

የከተማ ፕላን ዝግጅትንና አፈፃፀምን በተሟላ መልኩ ለማከናወን፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም በፌደራል፣ በክልሎችና በከተሞች ይገነባል፡፡

ተግባር 1 የተዘጋጀውን የከተማ ፕላን አዋጅ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ይበልጥ ማስተዋወቅና ክልሎችና ከተሞች የሚየዘጋጇቸው ፕላኖች አዋጁ በሚያዘው መሠረት መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣

ተግባር 2 የፌደራል የከተሞች ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ለግሉ ዘርፍ ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት እንዲችል የሰው ኃይል አቅሙን መገንባት፣

ተግባር 3 የከተማ ፕላኑን አዋጅ ለማስፈፀም የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ በየክልሉ እንዲፀድቅ ማድረግ፣

ተግባር 4 ቀደም ሲል የተዘጋጁት የከተማ ፕላን ማንዋሎችና ለአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ካርታ አዘገጃጀት የተረቀቁ ማንዋሎች/መመሪያዎች ለሁሉም ክልሎች/ከተሞች እንዲዳረሱና ባለሞያዎችም እንዲሰለጥኑባቸው ማድረግ፣

ተግባር 5 የሚዘጋጁት ፕላኖች በየከተማው ምክር ቤት ፀድቀው የየከተማው ሕግ እንዲሆኑና እንዲከበሩ ማድረግ፣ በዚህ መልክ የጸደቁ ፕላኖች ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ የከተማ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፣

ተግባር 6 የፌደራል የከተሞች ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ለክልሎችና ለከተሞች በከተማ ፕላን ዝግጅት፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ የመስጠትና ግሉን ዘርፍ የማጠናከር ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣

ተግባር 7 ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የከተማ ፕላን እንዲዘጋጅ የከተማ ፕላን ሥራ ፍቃድ የሚሰጥና ተገቢውን ቁጥጥር የሚያደርግ አካል በፌደራል መሰየም፣

ተግባር 8 በክልሎች ተቋቁመው ሥራ የጀመሩ የከተማ ፕላን ተቋማትን ማጠናከር፣ ተቋማቱ ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች ተቋቋመው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን፣

ተግባር 9 በሁሉም ከተሞች የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖችን የሚያስፈፅሙ አካላትን ማጠናከርና አቅማቸውን መገንባት፡፡

**ግብ ሁለት**

በከተማ ፕላን ዘርፍ ያለውን ፍላጎት ለማርካት ብቁ የሆነ እንዲሁም ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችል የግል ዘርፍ ይፈጠራል፡፡

ተግባር 1 የፀደቀውን የከተማ ፕላን አዋጅ እና በየክልሉ እንደሚፀድ የሚጠበቀው የማስፈፃሚያ ደንብን መሠረት በማድረግ የግሉ ዘርፍ በከተማ ፕላን ዝግጅት የሚሳተፍበትን መመሪያ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ፣

ተግባር 2 በቤቶች ልማት ፕሮጀክት አዳዲስ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን በማደራጀት ዙሪያ የተገኘውን ልምድ በመጠቀም ግልፅ በሆነ አሰራር የግል የከተማ ፕላን አማካሪዎችን ማደራጀት፣

ተግባር 3 በመመሪያው መሠረት የሥራና የንግድ ፍቃድ አውጥተው ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉትን የግል አማካሪዎች በተዘጋጁት ሕጎችና ማንዋሎች ዙሪያ ስልጠናና የተለያዩ ድጋፎች ( ብድር፣ የሥራ ትስስር፣ ወዘተ... ) እንዲያገኙ ማድረግ፣

ተግባር 4 የግል አማካሪዎች የሚያዘጋጇቸው ካርታዎችና ፕላኖች በአዋጁና በተዘጋጁት ማንዋሎች/መመሪያዎች እንዲሁም የጥራት ደረጃ/ ስታንዳርድ ወጥቶላቸው በዚያ መሠረት መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ በየክልሉ ቁጥጥር ማጠናከር፣

ተግባር 5 የፀደቀውን የከተማ ፕላን አዋጅ እና በየክልሉ እንደሚፀድ የሚጠበቀው የማስፈፃሚያ ደንብን መሠረት በማድረግ የግሉ ዘርፍ በከተማ ፕላን ዝግጅት የሚሳተፍበትን መመሪያ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ፣

ተግባር 6 የግል አማካሪዎች በፕላን ዝግጅት ብቻ ሳይሆን በአፈፃፀም ለከተሞች ድጋፍ የሚሰጡበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡

**ግብ ሦስት**

የከተማ ፕላን ዝግጅት ባለሞያዎችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት የሚያስችል የትምህርትና የስልጠና አቅም ይፈጠራል፡፡

ተባግር 1 የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን በከተማ ፕላን ዘርፍ ተቀብሎ የማሰልጠን አቅም በአመት ወደ አንድ ሺ ማሳደግ፣

ተግባር 2 በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅና በሌሎች የሃገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች በከተማ ፕላን ዘርፍ የማስተርስ ስልጠናዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ተግባር 3 በከተማ ፕላን ዘርፍ በስልጠና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ እንዲከናወን ማድረግ፣

ተግባር 4 ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋራ ጠንካራ የትብብር ግንኙነት በመፍጠር የማሰልጠን አቅምን ማሳደግ፣

ተግባር 5 የከተማ ፕላን አዘገጃጀት፣ አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ አጫጭር ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፣

ተግባር 6 እጩ ተመራቂዎች በኢንተርንሺፕ ፕሮግራም የሚታቀፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

**ግብ አራት**

የከተማ ልማት ሥራዎች የአገር አቀፍ የከተማ ልማት ፖሊሲንና ፖሊሲውን መሠረት አድርገው የሚዘጋጁ ክልላዊ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን መሠረት አድርገው የሚከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

ተግባር 1 ለትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች በውጭ አማካሪዎች የተዘጋጁትን ረቂቅ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ከወጣው የከተማ ልማት ፖሊሲና ከየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመፈተሽ ማፅደቅ፣

ተግባር 2 የሌሎች ክልሎችን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ለጋምቤላ፣ ለአፋር፣ ለሶማለሌና ለሐረሪ ክልሎች እንደዚሁም ለአዲስ አበባና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 3 የተዘጋጁ ክልላዊ ስትራቴጂዎችን ማስተዋወቅ /ግንዛቤ ማስጨበጥ/፣

ተግባር 4 የተዘጋጁ ክልላዊ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን መተግበር፣

ተግባር 5 በክልል ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የክልል የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን አስመልክቶ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፡፡

**ግብ አምስት**

በክልል ደረጃ ለከተሞች የሚሠጡ ድጋፎች በከተማ-ገጠር እና በከተሞች መካከል ያለውን ትስስር በሚያጠናክሩና ቀጣይነት ያለው ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡

ተግባር 1 የገጠርንና የከተማን ትስስር ለማጠናከር የሚያስችል ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 2 በየክልሉ የሚገኙ የትልልቅና አነስተኛ ከተሞችን ሚና በመለየት ትስስራቸውን ማጎልበት የሚያስችሉ የልማት ድጋፎችን መስጠት፣

ተግባር 3 የከተሞችን ሚና የሚመጥን ፈርጀ ብዙ የልማት ድጋፍና አቅርቦት በማካሄድ የከተሞችን ትስስር ማጎልበት፡፡

**ግብ ስድስት**

አነስተኛና መካከለኛ ከተሞች በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች ጋር ተሳስረውና ተቀናጅተው እንዲያድጉና ለቀጣይና ለዘላቂ ልማት ተገቢውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 በ15 የናሙና ከተሞች የሳተላይት ምስልን በመጠቀም መሠረታዊ ካርታና ፕላን ለማዘጋጀት እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ውጤታማነት ከወጪ፣ ከጊዜና ከጥራት አንፃር መገምገምና እርምጃ መውሰድ፣

ተግባር 2 የኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ድርጅት ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ካርታዎችን/ፕላኖችን በፍጥነትና በአነስተኛ ወጪ ማዘጋጀት ስለሚቻልበት ስልት ጥናት አድርጎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**ግብ ሰባት**

የከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል አደረጃጀት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ይሻሻላል፡፡

ተግባር 1 የከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል አደረጃጀት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣

ተግባር 2 በእስካሁኑ ተሞክሮ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራምን ከማስፈፀም አኳያ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የታዩትን መልካም ተሞክሮዎች በመቀመር፣ በክልልና በከተማ ደረጃ በከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን መቅረፅ፣

ተግባር 3 እንደ የከተሞቹ ደረጃ የሥራ ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## IV. የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ኘሮግራም

**ዓላማ**

ከተሞች የመልካም አስተዳደርን በማስፈን ዘላቂነት ያለው የመሠረተ ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ እንዲችሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የጐለበተ የፋይናንስ አቅም እና የተሻሻለ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ እንደዚሁም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭን በማድረቅ ለልማት የተመቻቸ የታክስ ሥርዓት ለመፍጠር ነው፡፡

የሚከተሉት ሦስት ኘሮጀክቶች በንዑስ-ኘሮግራሙ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ሀ. የታክስ ሥርዓትና የገቢ አቅም ማሻሻያ ፕሮጀክት

ለ. የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ፕሮጀክት

ሐ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ኘሮጀክት

### ሀ. የታክስ ሥርዓትና የገቢ አቅም ማሻሻያ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

ከተሞች ተገቢውን የመሠረተ-ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ የሚያስችላቸውን ፍትሐዊና አስተማማኝ የፋይናንስ ሃብት ድልድል እና ቀልጣፋና ውጤታማ የገቢ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፡፡

ግብ አንድ

ከአገር አቀፍና ከክልል የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ጋር በተጣጣመ መልኩ የከተሞችን ገቢ ለማሳደግ የሚረዱና ገቢ የመሰብሰብ አቅምን የሚያሳድጉ፣ አሰባሰብና አጠቃቀምን የሚያሻሽሉ መመሪያዎችና ማንዋሎችን በማዘጋጀት በከተሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 የታክስ ማሻሻያ ኘሮግራም ዓላማዎችንና ሕግጋትን መሠረት በማድረግ ከተሞች በአዋጅ የተሰጣቸውን ታሪፍ የማውጣት ስልጣን በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችላቸው ደንብና መመሪያዎች በክልሎች እንዲወጡ ማድረግ፣

ተግባር 2 ተጠንተው በክልሎች እጅ የሚገኙትን የከተሞች ታሪፎች ከመጽደቃቸው በፊት በየደረጃው እስከ ቀበሌ ድረስ ኅብረተሰቡ እንዲወያይባቸውና በመጨረሻም በየክልሉ ም/ቤት እንዲፀድቁና በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ተግባር 3 በግልጽ መስፈርት ላይ የተመሠረተ የከተሞች ፍትሐዊ የግብር ምደባ፣ የግብር ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፣

ተግባር 4 ከእዚህ ጋር በተያያዘም በየከተማው ያለውን ግብር ከፋይንና ያለበትን ውዝፍ የግብር መጠን በመለየት በአግባቡ መመዝገብና በወቅቱ መሰብሰብ፣

ተግባር 5 ከተሞች ከንግድ አገልግሎት ገቢ፣ ከከተማ ቦታና ቤት ግብር እና ከሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች የሚገኙ ገቢዎችን አስተዳደር ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት እና ሌሎች በኮምፒዩተር የተደገፉ የአሠራር ማንዋሎች ማዘጋጀትና መተግበር፣

ተግባር 6 የገቢ አስተዳደር ማሻሻያ ሥርዓት በተዘረጋላቸው ከተሞች የገቢ አሰባሰብ ባልተማከለ መልኩ /ለምሣሌ በቀበሌዎች፣ በባንኮች እና በመሳሰሉት/ እንዲከናወን ማድረግ፣

ተግባር 7 የግብር አሰባሰብ ውጤታማነት ደካማ በሆነበት የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት እንዲሳተፉ ማድረጢ ከአዋጭነትና ከቅልጥፍና አንፃር በክልል ደረጃ በተማከለ መልኩ እንዲሁም በትልልቅ ከተሞች ድጋፍ የአነስተኛና በአቅራቢያ የሚገኙ ከተሞች ገቢ የሚሰበሰብበትን መንገድ መቀየስ፣

ተግባር 8 ከግብር ከፋዩ ስለተሰበሰበው የገቢ አፈፃፀም እና አጠቃቀም ለኅብረተሰቡ መረጃ የሚቀርብበትን የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ሥርዓት ለከተሞች ተስማሚ በሆነ መልኩ መቅረጽ እና በተወሰኑ ናሙና ከተሞች ሥራ ላይ ማዋል፣

ተግባር 9 ኅብረተሰቡ የተሳተፈበትና ልማትን ማዕከል ያደረገ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ ወይም ማሳደጊያ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ማድረግና መተግበር፡፡

**ግብ ሁለት**

ከተሞች ፍትሐዊ፣ ግልጽና አስተማማኝ የፋይናንስ /የበጀት/ ድጋፍ የሚያገኙበት ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ተግባር 1 በተለይ መሰረተጠልማትን ከማስፋፈት አኳያ ከፌደራል መንግሥት ለከተሞች የሚደረጉ ድጋፎችን ግልፅና ወጥነት ባለው ሁኔታ ለመምራት የፋይናንስ ድጋፍ ማስተላለፊያ ፖሊሲ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 2 ክልሎች ለከተሞቻቸው የፋይናንስ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችላቸውን ቀመር ለማዘጋጀት የሚረዳቸው የገንዘብ አደላደል አጠቃላይ መመሪያ ወይም ናሙና ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣

ተግባር 3 በክልሎችና በከተሞች መካከል የገቢና የወጪ የፋይናንስ ኃላፊነቶችን በአግባቡ በመለየት ክልሎች ለከተሞቻቸው እንደ ሁኔታው የተለያዩ /ጥቅል፤ በዓላማ የተገደበ ወዘተ../ የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጡበትን ቀመር አሻሽለው እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣

ተግባር 4 በክልሎች የተዘጋጀው የከተሞች የሃብት ክፍፍል ቀመር እንዲተገበር ማድረግ፡፡

**ግብ ሦስት**

የታክስ ሥርዓቱ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ የሚያደርቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

ተግባር 1 የታክስ አሰባሰብና አስተዳደር የተሟላ የሕግ ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ፣

ተግባር 2 በከተሞች ፍትሃዊና ውጤታማ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠር፣

ተግባር 3 በከተሞች የታክስ ሥርዓቱን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ የሚችል፣ የሚያስተዳድርና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ ሥነጠምግባሩ የተጠበቀ የሰው ኃይል ማፍራት፣

ተግባር 4 የታክስ ሥርዓት ማሻሻያውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ፣

ተግባር 5 የግብር አወሳሰን ሂደትን አስመልክቶ ግልፅነት እንዲፈጠር እና ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ እንደሆነ የአመራሩን፣ የባለሞያውንና የሕዝቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎችን መስራት፣

ተግባር 6 የታክስ አወሳሰንና አስተዳደር ሥርዓት አስፈፃሚ ባለሞያዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## ለ. የፋይናንስ አስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

የከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት አግባብ ባላቸው የሕግ ማዕቀፍ፣ የፋይናንስ አወቃቀር፣ የአሰራርና የቁጥጥር ሥርዓት እንዲመራ ማድረግ፡፡

**ግብ አንድ**

በከተማ አስተዳደሮች በሕግ፣ ደንብና መመሪያዎች የሚመራ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 ክልሎች የከተሞቻቸውን ኃላፊነትና ተግባራት፣ ተጠያቂነትን እና የሃብት አጠቃቀምን ግልጽ የሚያደርጉበትና የሚመሩበት የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች ከአገር አቀፍ ደንብና መመሪያ ጋር በማጣጣም ማውጣትና በከተሞች ተግባራዊ የሚሆኑበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 2 በፌደራልና በክልሎች ደረጃ የወጡትን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግና ከከተሞች አደረጃጀት ጋር በተጣጣመ መልኩ ከተሞች የሚመሩበትን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ ማውጣት፣ ማጽደቅና ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 3 የከተሞች ማቋቋሚያ አዋጆች በክልልና በከተማ አስተዳደሮች መካከል ያሉትን ፋይናንስ ነክ ኃላፊነቶች ግልጽ ባደረገ መልኩ እንደገና እንዲፈተሹ ማድረግ፣

ተግባር 4 በፌደራልና በክልል የወጡትን ወጥነት ያላቸው ስታንዳርድ የጨረታ ግዥ የመወዳደሪያ ሰነዶች (Standard Bid documents) ለከተሞች በሚሆን መልኩ አጣጥሞ ማዘጋጀትና ተግባር ላይ ማዋል፣

ተግባር 5 በከተሞች የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ እና ስታንዳርድ የጨረታ ሰነዶች አፈፃፀምን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት**

ከከተሞች ስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ የተቀናጀና ልማትን ማዕከል ያደረገ የከተሞች ፋይናንስ ዕቅድ አሠራር ሥርዓት በከተሞች ይዘረጋል፡፡

ተግባር 1 ለከተሞች የተዘጋጁትን የፋይናንስ ዕቅድ አዘገጃጀት ማንዋሎችን መሠረት በማድረግ ከተሞች የመካከለኛ ጊዜ የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ እንዲያዘጋጁና ይህንንም ለዓመታዊ የበጀት ዝግጅት መነሻ በማድረግ በከተማ ምክር ቤት እንዲያፀድቁ ማድረግ፣

ተግባር 2 የከተማው ነዋሪ ኀብረተሰብ /በተለይም ሴቶች፣ ወጣቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ወ.ዘ.ተ. /በልማት ኘሮጀክቶች ወይም በካፒታል የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ችግሮችንና ፍላጐቶችን ከመለየትና ቅደም ተከተል ከማውጣት አኳያ በንቃት እና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚሳተፉበትን ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና ይህንንም ለመተግበር የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3 የፋይናንስ ዕቅድ አሠራር ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈጻጸም መከታተል፣ መገምገም እና የማጠናከሪያ እርምጃዎችን መውሰድ፣

ተግባር 4 በወጪ ማዕከላት ላይ የተመሠረተ እና የተጠቃለለ የከተሞች የበጀት አሠራር እንዲኖር የሚያደርግ የበጀት አወቃቀር ሥርዓት መዘርጋት እና ከፌደራልና ከክልሎች ጋር የተጣጣመ የከተሞች የበጀት አሠራር ማንዋል አዘጋጅቶ ማሰራጨት፣

ተግባር 5 የበጀት ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈፃፀም መከታተል፣ መገምገም እና የማጠናከሪያ እርምጃ መውሰድ።

**ግብ ሦስት**

ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ ሥርዓት በመዘርጋት ብክነትን የሚከላከል የግዥ፣ የንብረት አስተዳደር እና አወጋገድ ሥርዓት በከተሞች እንዲተገበር ይደረጋል።

ተግባር 1 የከተሞች የአገልግሎት አጠቃቀም /የነዳጅ፣ መኪና ጥገና፣ የጽሕፈት መሣሪያ፣ ወዘተ./ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ ኖርሞችንና የውስጥ አሠራር መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 ወጪ ቆጣቢ ሥርዓቱን ለማጠናከር በሦስተኛ ወገን ሊሰጡ የሚችሉትን የአገልግሎት ዓይነቶችን መለየት፣ ለዚህም ከቅልጥፍና፣ ከውጤታማነትና ከዋጋቸው አንፃር አዋጭነታቸውን ለማወቅ፣ ሥራውን ለማከናወን የተደራጀ የፋይናንስና የቴክኒክ ብቃት ያላቸው ተዋዋይ ድርጅቶች መኖራቸውን እና የመሳሰሉትን ለመለየት የሚረዱ መመዘኛዎችን የያዘ መመሪያ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 3 ከተሞች ያላቸውን ውስን ሀብት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንዲችሉ በየደረጃው ላሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የግንዛቤ ማዳበሪያ ዓውደ ጥናቶችና ሴሚናሮችን በማዘጋጀት የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ፣

ተግባር 4 በአጠቃቀም ሂደት ለብክነት የሚጋለጡ ወጪዎችን በየጊዜው በመፈተሽና በመገምገም ወጪ ቆጣቢ ሥርዓቱን ማስተካከል።

**ግብ አራት**

በከተሞች ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ ግልፅና ትክክለኛ የሂሣብ መግለጫ ማቅረብ የሚያስችል የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል።

ተግባር 1 ለከተሞች በመዘጋጀት ላይ ያለው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ የገቢና የወጪ መደብ (Chart of Accounts) እና የአሠራር ማኑዋል፣ በፌደራልና በክልል ካለው የአሠራር ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ እንዲጠናቀቅ ማድረግና ማሰራጨት፣

ተግባር 2 በየደረጃው ለሚገኙ የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ስለ ሂሣብ አያያዝ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር/ዐውደ ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 3 ከተሞች ያለፉትን ዓመታት ሂሣባቸውን ዘግተው በማጠናቀቅ ለአዲሱ የሂሣብ አሠራር ዝግጅት እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 4 የሂሣብ አሠራሩን ከነጠላ ሂሣብ አመዘጋገብ ሐስፀነገለጽ (Single Entry) ወደ ድርብ የሂሣብ አመዘጋገብ (Double Entry) ሥርዓት መቀየር፣

ተግባር 5 የከተማው የሂሣብ አያያዝ /የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተቀላጠፈና ወጪ ቆጣቢ አሠራር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የአንድ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል (Single Pool) የአሠራር ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋል፣

ተግባር 6 የሂሣብ አያያዝ ማሻሻያ ኘሮግራሙ በአግባቡ መተግበሩን በየደረጃው መከታተልና መገምገም፡፡

**ግብ አምስት**

በየደረጃው በከተሞች ግልፅ እና ወጥነት ያለው የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

ተግባር 1 በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ የተደረገውን የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ማሻሻያ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ለከተሞች መመሪያዎችንና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ ማፀደቅ፣

ተግባር 2 የነጠላ የትሬዠሪ የባንክ ሂሣብ አሠራርን (Single Treasury Account) በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሠራር መመሪያ አዘጋጅቶ የባንክ አገልግሎት ባላቸው ከተሞች በሥራ ላይ ማዋል፣

ተግባር 3 የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ማሻሻያ ፕሮግራምን አፈፃፀም መከታተል፣ መገምገም እና ለቀጣይ ተግባራዊነቱም ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፡፡

**ግብ ስድስት**

የከተሞች ሃብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆጣጠር እና በየደረጃው ያለውን አካል ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የተጠናከረ የውስጥና የውጪ ኦዲት /ቁጥጥር ሥርዓት/ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጀውን የኦዲት መመሪያና የአሠራር ማንዋል ለከተሞች እንደሚሆን አጣጥሞ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣

ተግባር 2 ለከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች በውስጥ ኦዲት አደረጃጀትና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 3 ከተሞች ሂሣባቸውን በወቅቱ በመዝጋት የውጭ ኦዲተር ቀጥረው እንዲያስመረምሩ ለማድረግ የሚያስችልና በየጊዜው አስፈላጊውን በጀት የሚመድቡበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 4 ከተሞች የተጠናከረ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲችሉ የየክልሉ ኦዲት ቢሮዎች ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

ተግባር 5 በውጭ ኦዲተሮች የተዘጋጀው የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት በወቅቱ ለከተማው ም/ቤት የሚቀርብበትን የአሠራር ሥርዓትና በውጭ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተጠቀሱ የማሻሻያ እርምጃዎችን እና በከተማው ም/ቤት የሚሰጡ አስተያየቶችን በወቅቱ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 6 በመርሃ ግብሩ ዓመታት በናሙና ከተሞች ውስጥ የክንዋኔ ኦዲት ሙከራ ማድረግ፣ የኦዲት ማሻሻያ ፕሮግራም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን መከታተልና መገምገም፡፡

**ግብ ሰባት**

በወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ይሻሻላል፡፡

ተግባር 1 በወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ያለበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚረዳ የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ማከናወን፣

ተግባር 2 በዳሰሳ ጥናቱ የተገኙትን እጥረቶች ለመቅረፍና የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ መከናወን የሚገበቸውን ተግባራት መለየት፣

ተግባር 3 የአፈፃፀም መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## ሐ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ኘሮጀክት

**ዓላማ**

የከተሞችን የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት፣ የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም፣ የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት አቅምን ለማሳደግ ነው፡፡

ግብ አንድ

በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻያዎች በብቃት ተግባራዊ የሚያደርግ በቂ የሰው ኃይል ይሰለጥናል፡፡

ተግባር 1 ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና እና መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በታሪፍ ደንብና መመሪያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 3 ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 4 ለ4320 ባለሙያዎች በበጀት አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 5 4320 ለሚሆኑና በ432 ከተሞች ለሚገኙ የሂሣብ ባለሞያዎች በሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 6 4320 ለሚሆኑ ባለሞያዎች በጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ አፈፃፀም ማሻሻያ ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 7 ለ864 ኦዲተሮች የፋይናንስና የክንዋኔ ኦዲት ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 8 2160 ለሚሆኑና በ432 ከተሞች ለሚገኙ በገቢ አሰባሰብ ለተሰማሩ ሠራተኞች በገቢ አስተዳደር ሥርዓት ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 9 በ42 ከተሞች ለሚገኙ 168 ለሂሣብ እና የበጀት ባለሞያዎች፣ ገቢ ሰብሳቢዎችና ኦዲተሮች በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅት፣ የሂሣብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ላይ በተግባር የተደገፈ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 10 በየከተማው በሚገኙ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የፋይናንስ ባለሙያዎች እና ጽ/ቤቶቹን በበላይነት ለሚያስተዳድሩ የቦርድ አባላት አሰልጣኞችን በመለየት እንደአግባብነቱ በፕሮጀክት ሰነድ እና በቢዝነስ ዕቅድ /ብጭሰፀነጽሰሰ ፕለቷነ/ አዘገጃጀት፣ የሂሣብ አያያዝ እና በገቢ አስተዳደር ላይ 10 ቀናት ስልጠና መስጠት፡፡

**ግብ ሁለት**

በየደረጃው በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅት፣ የሂሣብ አያያዝ እና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ አሠራሩ ዘመናዊና የፋይናንስ የመረጃ ፍሰቱም ቀልጣፋ ይሆናል፡፡

ተግባር 1 በከተሞች የኮምፒዩተር መረጃ መረብ እንዲዘረጋ ማድረግ፣

ተግባር 2 የተዘጋጀውን የኮምፒዩተር አሠራር ሥርዓት ለመተግበር የሚረዳ የአጠቃቀም ማንዋል (User Manual) እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

ተግባር 3 የማሻሻያ ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች የኮምፒዩተር እና ሌሎች ተጓዳኝ ዕቃዎች የፍላጐት ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 4 ቀደም ሲል በፌዴራል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና በየክልሉ የፋይናንስ ቢሮዎች ውስጥ የተቋቋሙትን የኮምፒዩተር አሠራር ድጋፍ ሰጪ ዩኒቶች እንዲጠናከሩና ለከተሞች ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

ተግባር 5 የኮምፒዩተር ፕሮግራም በሚዘረጋባቸው ከተሞች ሁለገብ የኮምፒዩተር ባለሙያ እንዲኖር ማድረግ፣

ተግባር 6 ስለማሻሻያ ፕሮግራሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር ለኃላፊዎች እንዲሰጥ ማድረግ፣

ተግባር 7 የማሻሻያ ፕሮግራሙን በቅድሚያ በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች፣ በመቀጠልም በየደረጃው በሌሎች ከተሞች መዘርጋትና አፈፃፀሙን መከታተል፡፡

ግብ ሦስት

በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር፣ የገቢና የንብረት አስተዳደር እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሥራ ሂደት ለውጥን መሰረት ያደረጉ አደረጃጀቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

ተግባር 1 በከተሞች የፋይናንስ አሰተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ የተሻሉ ልምዶችን መቀመር እና የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ፣

ተግባር 2 በከተሞች የገቢ አቅምን ከማሳደግ አኳያ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ የተሻሉ ልምዶችን መቀመር እና የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ፣

ተግባር 3 በዚሁ መሠረት ጠንካራ አደረጃጀቶች መፈጠራቸውን ማረጋገጥ፡፡

## V. የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም

□ላማ

በከተማ ጉዳዮች ላይ በየደረጃው የሚገኙ የሕግ አውጪው፣ የፍትሕ እና የከተማ አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችሉ፣ እንዲሁም የከተማ ነዋሪውን የተሳትፎ አቅም የሚያሳድጉ የአደረጃጀት፣ የሰው ኃይል ልማትና የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎች ለማከናወን ነው፡፡

**ንዑስ ፕሮግራሙ ሦስት ፕሮጀክቶች አሉት፡-**

ሀ. የከተማ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

ለ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

ሐ. የፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት

### ሀ. የከተማ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም

**ዓላማ**

በከተሞች ያለውን የምክር ቤቶች አቅምን በመገንባት የውክልና የሕዝብ ተሳትፎን በአግባቡ መምራት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር፣ እንዲሁም የተደራጀና የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎን በማጠናከር ነዋሪዎችን አስተማማኝ የልማት አጋር፣ ተጠቃሚና ባለቤት ለማ□ረ□ ነው፡፡

**ግብ አንድ**

የከተሞችና የቀበሌ ምክር ቤቶችን ግልፅነትና ወጥነት ባለው ሥርዓት ለመምራት፣ አባላቱም ኃላፊነታውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው የምክር ቤት የአሠራርና የአባላት የሥነ ምግባር ደንብ ጸድቆ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ተግባር 1 በፌደራል የተዘጋጀውን ሞዴል የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንቦች ክልሎች እንደየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አሻሽለው እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 2 በክልሎች የተዘጋጁትን የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንቦች በክልል ምክር ቤቶች ማፀደቅና ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 3 በክልሎች የተዘጋጁትን የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት**

20000 የከተማ ምክር ቤት አባላት በየክልሉ የመንግሥት ሥራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋማት በከተማ ሥራ አመራር፣ በመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በአመራር ክህሎት ይሰለጥናሉ፡፡

ተግባር 1 የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅት ማጠናቀቅ፣

ተግባር 2 የአሰልጣኞች ምልመላ ማከናወንና የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 3 የምክር ቤት አባላት የስለጠና መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ ስልጠናውን መስጠት፣

ተግባር 4 ስልጠናው በተገቢው የጥራት ደረጃ መካሄዱን መከታተልና መደገፍ፡፡

**ግብ ሦስት**

በየደረጃው ለሚገኙ የምክር ቤት አባላትና በምክር ቤቶች ለሚቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎች በከተማ ጉዳዮች ላይ የተሻለ ግንዛቤና የተሳትፎ አቅም እንዲኖራቸው እንዲሁም ከኃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ በሚገናኙ ጉዳዮች የተለያዩ ሥልጠና በመስጠት ተሳትፎአቸው ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 በከተሞች ምክር ቤቶች የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ማቋቋም እና ምክር ቤቶቹ ሕጎችን የማውጣትና የሚወጡትን ሕጎች አፈጻጸም በአግባቡ የመከታተል አቅም እንዲኖራቸው የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣

ተግባር 2 በቀበሌ ምክር ቤቶች የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም እና ኮሚቴዎቹ የተቋቋሙበትን ዓላማ እንዲያሳኩ ስልጠናዎችን መስጠት፣

**ግብ አራት**

በከተሞች የሕዝብ ተሳትፎን ለማጠናከር የተለያዩ የሕብረተሰብ አካላትን አመኔታ ያገኙ አሳታፊ አደረጃጀቶችና መድረኮች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ለማድረግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ተግባር 1 የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎን በአግባቡ አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎ ማንዋል/ መመሪያ ይዘጋጃል፣ ጸድቆ ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 2 ለልማት፣ ለማኀበራዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ንቅናቄ ለመፍጠርና የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎን በተቃና ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣

ተግባር 3 ወጣቶችና ሴቶች በብዙሃን ማኀበራት መታቀፍ የወል ጥቅምንና መብትን ለማስከበር ወሳኝ መሆኑን ተረድተው በወጣቶችና በሴቶች ማኀበራት እንዲደራጁ የማሳወቅና የቅስቀሳ ስራዎችን ማከናወን፣

ተግባር 4 በቀበሌዎች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ከነዋሪዎች የተውጣጡ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከኃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ በሚገናኙ ጉዳዮች ላይ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ማድረግ፣

ተግባር 5 የከተማ ነዋሪውን ወሳኝ በሆኑ የከተማ ጉዳዮች ላይ በግንባር ለማነጋገር የሚያስችሉ ሕዝባዊ ኮንፍረንሶችን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ማካሄድ፣

ተግባር 6 በከተማ መሪ ኘላን፣ በከተማ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዙሪያ በተለይ ከፍተኛ ወጪን በሚያስከትሉ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ቅደም ተከተል ላይ የተለያዩ የኅብረተሰብ አካላት በየደረጃው እንዲመክሩበት ማድረግ፣

ተግባር 7 መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ዕድሮች፣ ከግሉ ዘርፍ፣ ከብዙሃን ማኅበራትና ከሞያ ማኅበራት የከተማ አስተዳደር የጋራ የትብብር መድረክ መመስረትና ቋሚ የምክክር መርሃ-ግብር ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 8 የአካባቢ ማሻሻያ ኘሮጀክቶች ነዋሪው በተለይም ተጠቃሚው የተለያዩ አግባቦችን በመጠቀም አቅምን ባገናዘበ መልኩና በፍቃደኝነት ላይ ተመርክዞ ወጪን እንዲጋራ በማድረግ ተሳትፎውን ማጎልበት፣

ተግባር 9 የግሉ ሴክተር በከተሞች የተለያዩ ብቁና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን በመስጠት ተሳታፊ እንዲሆን አዋጪ የሆኑ የከተማ አገልግሎቶችን ለግሉ ሴክተር outsource ማድረግ።

## ለ. የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

- የከተማ አስተዳደሮች የመልካም አስተዳደር ባህርያትን የተላበሱ አሰራሮች እንዲኖራቸው የሚያስችል የሥራ ግንኙነት፣ ሥልጣንና ኃላፊነት፣ የሕግና ተቋማዊ የአደረጃጀት መዋቅር እና የመረጃ ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ ፣ እና
- የአስፈፃሚ አካላት ሥራ አመራርና ባለሞያዎች የከተማ ልማትን የሚያፋጥኑ ከባቢያዊ የፖሊሲ ሃሳብ የማመንጨት፣ ስትራቴጂና ሕጐችን የማርቀቅ፣ ድጎነትና ሥራ አጥነትን የማስወገድ፣ የአገልግሎት አሠጣጥ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ የማድረግና የአካባቢ ገጠር ልማትን ለመደገፍ ቴክኒካዊ ብቃት ለመያዝ የሚያስችላቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

**ግብ አንድ**

የከተማ መልካም አስተዳደር ፕሮግራምንና የከተማ ልማት ፕሮግራምን ውጤታማ በሆነ መልኩ ከማስፈፀም አኳያ ከተሞች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ የሚጠቀሙባቸው የከተማ አስተዳደር የሥራ ሂደቶች ይፈጠራሉ።

ተግባር 1 የመንግሥት የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግና ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ የሥራ ሂደቶችን መለየትና ማጥናት፣

ተግባር 2 እስካሁን ከተደረገው እንቅስቃሴ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን ተሞክሮዎች መዳሰስና ምርጥ ልምዶችን በመቀመር ማስተላለፍ፣

ተግባር 3 በፌደራል ደረጃና በክልሎች የተለዩ የሥራ ሂደቶችን የማቀራረብና ተደጋጋፊ የማድረግ ተግባራትን ማከናወን፣

ተግባር 4 የተጠኑት ጥናቶች ሳይሸራረፉ ወጥና የተሟላ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ክትትልና ድጋፍ መስጠት።

ግብ ሁለት

የከተሞች አደረጃጀት ሞዴል የሕግ ማዕቀፍን ለማስፈፀም የሚረዱ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

ተግባር 1 በልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የከተሞች አደረጃጀት ሞዴል የሕግ ማዕቀፍ የአፈፃፀም መመሪያዎች ክፍተቶችን በመለየት የአፈፃፀም ስልትና ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 ሞዴል መመሪያዎችን ዐውደ ጥናት በማዘጋጀት ሀገራዊ ልምዶች እንዲዳሰሱና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ ፣

ተግባር 3 በውይይት የዳበሩትን ሞዴል መመሪያዎች ለክልሎች መላክና ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ መስጠት፣

ተግባር 4 የአፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

ግብ ሦስት

የከተሞች የትብብር ግንኙነት ማጠናከሪያ ቋሚ መድረክ እና የከተሞች ቀን ይመሠረታል፡፡

ተግባር 1 በከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም የታቀፉ ከተሞች መስራችነት ሌሎች አባላትን በየደረጃው እየጨመረና ግንኙነቱን እያጠናከረ የሚመጣ የግኑኝነት መድረክ አወቃቀር ጥናት ማጠናቀቅና ማፅደቅ፣

ተግባር 2 ከክልሎችንና ከተሞች ጋር ውይይት ማድረግና መግባባት ላይ መድረስ፣

ተግባር 3 የመድረኩ ጽሐቤት በሚፈለገው የሰው ኃይል፣ ቢሮና ማቴሪያል እንዲሟላ ማድረግ፣

ተግባር 4 በከተማ ልማት ዘርፍ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችንና የተገኙ ውጤቶችን የሚዘግብ አመታዊ መጽሔት (State of Ethiopian Cities) ማዘጋጀትና ማሰራጨት፡፡

ተግባር 5 የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን አከባበር መነሻ ጥናታዊ ሰነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 6 በዚሁ መነሻ ሰነድ መሠረት የከተሞች ቀን አፈፃፀም ዕቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድርግ፣

ተግባር 7 በከተሞች ቀን በክልሎችና በከተሞች መካከል የልማትና በመልካም አስተዳደር ፕሮግራሞች ትግበራ ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው የሚሸለሙበትና ለሌላው አርዓያ የሚሆን ሥራቸው የሚቀርብበት ሥርዓት መዘርጋት፡፡

**ግብ አራት**

የከተማ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ፣ የፖሊሲና ፕሮግራም ሃሣቦችን ለማመንጨት የሚያስችሉ የከተማ መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ ይደራጃሉ፡፡

ተግባር 1 በከተማ ልማት ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ዋና ዋና ተቋማትን የመረጃ ፍላጐት ማጥናት፣ የሚፈለጉ መረጃዎችን መለየት፣

ተግባር 2 አግባብነት ባላቸው የፌዴራልና የክልል መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙትን የከተማ ልማትን የሚመለከቱ የመረጃ ሃብቶች ማሰባሰብና በዘመናዊ መንገድ ማደራጀት፣

ተግባር 3 መረጃዎችን ወቅታዊ ለማድረግ፣ ለተጠቃሚዎች ሳይዛቡና ሳይፋለሱ በቀላሉ ለማድረስ የሚያስችል የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፡፡

**ግብ አምስት**

የከተማ ሥራ አመራር ባለሞያዎችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት የከተማ ሥራ አመራር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የባለሞያ አቅርቦት በጥራትና በመጠን ተሻሽሎ ውጤታማ ይሆናል፣ በከተማ ሥራ አመራር ድህረ ምረቃ ኘሮግራም የማሰልጠን አቅም በዓመት ወደ 1000 ያድጋል፡፡

ተግባር 1 የስልጠና ፕሮግራሙ ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የሥልጠና ዕቅድ መሠረት እየተከናወነና ጥራቱም የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ክትትልና የአፈፃፀም ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 2 የተሳታፊዎች ምልመላ በጥንቃቄ ወቅቱን ጠብቆ መከናወኑን ማረጋገጥ፣

ተግባር 3 በፕሮግራሙ የሰለጠኑ ተመራቂዎች በከተሞች አግባብ ባላቸው የሥራ ቦታዎች ላይ ተመድበው እያገለገሉ መሆኑን መከታተል፣

ተግባር 4 ሥልጠናው በሥራ ላይ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ መገምገም፣

ተግባር 5 የፕሮግራሙ የአፈፃፀም አቅጣጫ ቀጣይነትን በተመለከተ የገበያ ሁኔታን ያገናዘበ ግምገማ በማድረግ ርምጃ መውሰድ፣

ተግባር 6 የስልጠውን ጥራት ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎች መውሰድ፡፡

**ግብ ስድስት**

የ450 የከተማ አስተዳደር ፣ የማዘጋጃ ቤት ከተሞችና ታዳጊ ከተሞች 6000 የከተማ አሰተዳደር አስፈጻሚ አካላት የሥራ አመራር ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በከተማ ልማት ፖሊሲ፣ በከተሞች የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅና በመልካም አስተዳደር ፕሮግራም፡ እንዲሁም በስትራቴጂክ ዕቅድ ዝገጅት፣ በአመራር አሰጣጥና ማስተባበር (leadership)፣ በኘሮጀክት ማኔጅመንት፣ የኮንትራት አስተዳደር፣ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ አጋርነትን መምራት፣ በአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት በተከታታይ ዙሮች አጫጭር ሥልጠና ይወስዳሉ፡፡

ተግባር 1 የሥልጠና ዕቅድ ማዘጋጀትና እንዲፀድቅ ማድረግ፣

ተግባር 2 ስትራቴጂው በከተማና በቀበሌ በየደረጃው የሚገኙ የሥራ አመራር አካላት የውሳኔ አሠጣጥ' የማስተባበርና የመምራት ክህሎታቸውን የሚያሳድጉ፣ ክልልና ከተሞች የሚገኙ የተለያዩ ሴክተሮችን ለሚመሩ አካላት በተቀናጀ የከተማ ስትራቴጂክ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ተመሳሳይ ቀኝት እንዲኖራቸው እና ሲቪል ሰርቪሱን ለለውጥ የሚያንቀሳቅሱበትና አመለካከቱን በሚፈለገው አቅጣጫ እንዲሆን የሚያግዙ የስልጠና ዓይነቶችን በዋናነት እንዲያካትት ማድረግ፡፡

ተግባር 3 የሥልጠና ማንዋሎች ማዘጋጀት፣

ተግባር 4 የአሰልጣኞች ስልጠና ማዘጋጀትና መስጠት፣

ተግባር 5 አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣

ተግባር 6 ወቅታዊ የተሃድሶ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማመቻቸት፡፡

**ግብ ሰባት**

በማሠልጠኛ ተቋማት ገብተው ለመሣተፍ እድል ያላገኙና በክልልና ከተማ አስተዳደሮች በተለያዩ የሙያ መስክ በማገልገል ላይ ለሚገኙ 12000 ባለሙያዎችና ቴክኒሺያኖች በከተማ ሥራ አመራር የአጭርና ረጅም ጊዜ የርቀት ትምህርት ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1 የስልጠና ስትራተጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 ከክልል ቢሮዎች ማሠልጠኛ ተቋማትና ተጠቃሚዎች ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር፣

ተግባር 3 የሥልጠና ካሪኩለምና ኘሮግራም ማዘጋጀት፣

ተግባር 4 ሥልጠናውን የሚያግዝ ተቋማዊ አደረጃጀት ማስተካከል፣

ተግባር 5 የሠልጣኞች ምርጫ መመዘኛ ማዘጋጀትና ምልመላ ማካሄድ፣

ተግባር 6 የሥልጠና አፈጻጸም ሂደት ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣

ተግባር 7 የተሃድሶ ስልጠና በማመቻቸት የአቅም ግንባታውን ሥራ ቀጣይነት ማረጋገጥ፣

ተግባር 8 ሥልጠናው በሥራ ላይ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ መገምገም፡፡

**ግብ ስምንት**

የከተማ ልማት ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ ዝግጅት ይጠናቀቃል፣ ይፀድቃል፡፡

ተግባር 1 በረቂቅ ስትራቴጂው ላይ ከበላይ አመራሩ ጋር ውይይት በማድረግ የጋራ ግንዛቤና አቅጣጫ መያዝ፣

ተግባር 2 ስትራቴጂው በሀገራችን በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ እየታየ ያለውን ዕድገት ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 3 በረቂቅ ስትራቴጂው ላይ ከባለሞያዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣

ተግባር 4 ሀገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ማዘጋጀትና ከክልሎች ጋር የጋራ ግንዛቤ መያዝ፣

ተግባር 5 የመጨረሻውን ረቂቅ ማዘጋጀትና እንዲፀድቅ ማድረግ፡፡

## ሐ. የፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት

**ዓላማ**

የሕግ፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያዎችን በማድረግ በከተሞች ቀልጣፋና ብቃት ያለው የፍትሕ አገልግሎት ለማቅረብ፣ የአስተዳደር ብልሹነት ለመዋጋትና የነዋሪዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ ነው፡፡

**ግብ አንድ**

በከተሞች የሚወጡ ሕጎች የሚፈለገውን ልማት ለማምጣት እንዲቻል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውን የሚያበረታቱ እንዲሆኑና የዜጎችን መብት እንዲያስከብሩ ይሻሻላሉ፡፡

ተግባር 1 ያልተማከለ የአስተዳደር መርህን መሠረት በማድረግ የከተሞች ማቋቋሚያና ሌሎች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንድምታ ያላቸውን አዋጆችን አግባብነት መፈተሽ፣

ተግባር 2 በክልልና በከተማ ደረጃ የወጡ አዋጆችን በክልልና በከተሞች ምክር ቤቶች እንደየአግባቡ ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላት በታዩ ማነቆዎችና በተዘጋጁ ረቂቆች ላይ አስተያየት እንዲሰጡባቸው ማድረግ፣

ተግባር 3 የተሻሻሉ የሕግ ረቂቆቹን ለሚመለከተው የከተማ ወይም የክልል ምክር ቤት አቅርቦ ማፀደቅ፣

ተግባር 4 የሕግ ሰነዶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

ግብ ሁለት

በከተሞች የማኀበራዊ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው ሥራ ይጀምራሉ፡፡

ተግባር 1 በከተሞች የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ሥራ በተመለከተ ያለውን ልምድ መቀመርና ለሌሎች ከተሞች ስለሚተላለፍበት ስልት መቀየስ፣

ተግባር 2 የማህበራዊ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብን ረቂቅ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3 በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ክልሎች፣ ከተሞች፣ አግባብነት ያላቸው አካላትና ባለሞያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣

ተግባር 4 በተገኘው አስተያየት መሠረት ረቂቁን በማዳበርና በማዘጋጀት ለክልሎች ማሠራጨት፣

ተግባር 5 ደንቡ በክልሎች/በከተሞች እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 6 ፍርድ ቤቶቹ ተደራጅተው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠት፡፡

ግብ ሦስት

በከተሞች ደንብ የማስከበር አቅም ይበልጥ ይጠናከራል፡፡

ተግባር 1 በከተሞች የደንብ ማስከበር አገልግሎት ሥራን በተመለከተ ያለውን ልምድ መቀመርና ለሌሎች ከተሞች ስለሚተላለፍበት ስልት መቀየስ፣

ተግባር 2 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የከተሞች የደንብ ማስከበር አገልግሎት ማቋቋሚያ ደንብ ረቂቅ ማዘጋጀት

ተግባር 3 በረቂቅ ደንቡ ላይ ክልሎች፣ የከተማ አስተዳደሮች አግባብነት ያላቸው አካላትና ባለሞያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣

ዕቾቨኃ 4 በተገኘው አስተያየት መሠረት ረቂቁን በማዳበር ሞዴል ደንቡን ለክልሎች ማሠራጨት፣

ዕቾቨኃ 5 ደንቡ በክልሎች/በከተሞች እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 6 የደንብ ማስከበር አገልግሎቶቹ ተደራጅተው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠትÝÝ

**ግብ አራት**

የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ የደንብ አስከባሪ አካላት እና የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ይሻሻላል፡፡

ተግባር 1 የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶችን፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤትን፣ የደንብ አስከባሪ አካላትን እና የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሪገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣

ተግባር 2 በእስካሁኑ ተሞክሮ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሙን ከማስፈፀም አኳያ በከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ በከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ በደንብ አስከባሪ አካላት እና በፖሊስ አገልግሎት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የታዩትን መልካም ተሞክሮዎች መቀመር፣

ተግባር 3 የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ በከተሞች የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ በደንብ አስከባሪ አካላት እና በፖሊስ አገልግሎት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተለዩ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን መቅረፅ፣ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**ግብ አምስት**

በከተማ አስተዳደር ሙስናን ለመከላከልና ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜም በቀላሉ ለይቶ በማውጣት የሕግ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

ተግባር 1 በከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች ለሚገኙ ዳኞች፣ ለከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕጎች፣ ለፖሊስ እና ለሌሎች የፍትሕ አካላት በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚከሰቱ የሙስና ወንጀሎችን ለመመርመር፣ ለመክሰስና ለመዳኘት የሚያስላቸውን አቅም ለማጎልበት ተከታታይ ስልጠናዎችን መስጠት፣

ተግባር 2 በከተሞች ለፖለቲካ ተሿሚዎችና ለመንግሥት ሠራተኞች የሥነ ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 3 የከተማ-ነክ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የደንብ አስከባሪ አካላት፣ የአቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ባለሞያዎች እና ፖሊሶችን ተጠያቂነት ለማጠናከር የፍትሕ አካላት የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 4 በከተሞች በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሥነ ምግባር ትምህርትን የሥርዓተ ትምህርቱ አካል ማድረግ፣

ተግባር 5 ኅብረተሰቡን የፀረ ሙስና ዘመቻው አካል ለማድረግ በተለያዩ ሚድያዎች በመቀስቀስ የአመለካከት ለውጥና የተቆርቋሪነት ስሜት እንዲፈጠር ማድርግ፣

ተግባር 6 በክልል/ከተሞች ለሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ የሚከሰት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን የመመርመርና በአግባቡ የመዘገብ አቅማቸውን ለማሰደግ የምርመራ ጋዜጠኝነት /Investigative Journalism / ሥልጠና መስጠት፣

ተግባር 7 ሕዝባዊ ማኅበራትና የተለያዩ የሞያ ማኅበራት በከተማ አስተዳደሮች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን በወኪሎቻቸው አማካይነት በከተሞች ምክር ቤቶች ለሚቋቋሙ የቅሬታ ሰሚና የፀረ-ሙስና ኮሚቴዎች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 8 በመንግሥት መ/ቤቶችና በመገናኛ ብዙሃን መካከል የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፡፡

**ግብ ስድስት**

የከተማ ሁለገብ የልማት መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ የሚሆኑበት ሥርዓትን በመዘርጋት ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የከተሞች አስተዳደር ይገነባል፡፡

ተግባር 1 የከተሞች የስትራቴጂክ ዕቅድን፣ ዓመታዊ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን፣ የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎችን፣ የኦዲት ሪፖርቶችን፣ የጨረታ አሠራር ሂደቶችን የሚዘግቡ ሰነዶች፣ ለኢንቨስትመንት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን ያደራጁ አነስተኛ መፅሐፍት ቤቶች ማቋቋም፣ ወይም በሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ውሰጥ የተለየ ማዕዘን ይዘው እንዲደራጁ ማድረግ፣

ተግባር 2 ለኢንቬስትመንት የሚያገለግሉ መረጃዎችንና የተለያዩ ደንቦችና መመሪዎችን ለፈላጊዎች የሚያቀርብ የሽያጭ መስኮት በከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች ማቋቋም፣

ተግባር 3 በመንግስት ተቋማትና በቀበሌዎች ወቅታዊ የከተማ መረጃዎችን በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች በተቀመጡ የማስታወቂያ ሠሌዳዎች ላይ መለጠፍ፣

ተግባር 4 በመንግስት ተቋማትና በቀበሌዎች የተገልጋዩን አስተያየት ማሰባሰቢያ ሳጥኖች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች በማስቀመጥ አስተያየቶችን በመሰብሰብ ጥቅም ላይ ማዋል፣

ተግባር 5 የተለያዩ ብዙሃን መገናኛን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎች ለነዋሪው እንዲያቀርቡ ማድረግና የሕዝቡን አስተያየቶችና ጥቆማዎችን መቀበል፣

ተግባር 6 የተለያዩ የከተማ መረጃዎችን በኢንተርኔት መረብ ለማሰራጨት የሚረዳ የከተማ አስተዳደር ድረ-ገጽ መክፈት፡፡

# ክፍል ሦስት

## የአመራር ሥርዓት፣ ፋይናንስና መርሃ-ግብር

### I. የፕሮግራም የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

#### 1. ግልጽና አሳማኝ የሥራና የከተሞች ቅደም ተከተል አውጥቶ መንቀሳቀስ

በእያንዳንዱ ንዑስ-ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱት ተግባራት በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም ስራዎች በሁሉም ከተሞች በአንድ ጊዜ መተግበር አይቻልም፡፡ ስለሆነም ወደ አፈጻጸም ከመገባቱ በፊት ንዑሳን ፕሮግራሞቹንና በውስጣቸው የተካተቱ ፕሮጀክቶችና ሥራዎች ግልጽና አሳማኝ ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡ በንዑስ ፕሮግራሞቹ የተመለከቱት የማሻሻያ ተግባራቱ ከመፈጸማቸው በፊት በሥራ ላይ ያለውን የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ገምግሞና ከአለም አቀፍ ልምዶች አያይዞ እንዲሻሻል ማድረግ፣ ያሉትን የአሰራር ሥርዓትና የአደረጃጀትና የሰው ኃይል ሁኔታዎች ገምግሞ ማሻሻልና ከሚመለከታቸው አካላት ጋራ መግባባት ፈጥሮ ወደሚቀጥለው ምዕራፍ መሸጋገር ይገባል፡፡ በመቀጠል የሚከናወነው ሥራ እነዚህን ማሻሻያዎች በተመለከተ ለፈጻሚዎች የተሟላ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ኦሪየንቴሽንና ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ ማስማራት ይሆናል፡፡ ተሻሽለው የተዘጋጁት ሦስት የከተሞች የመልካም አስተዳደር ንዑስ-ፕሮግራሞች እነዚህን የሥራ ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ሲሆን ወደ አፈጻጸም ሲገባም በዚሁ መሠረት ለመፈጸም መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

ንዑስ-ፕሮግራሞቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈጸም እንዲቻል ሌላው ቅደም-ተከተል ወጥቶለት ሊከናወን የሚገባው ጉዳይ በማሻሻያ ፕሮግራሙ በቅድሚያ ሊታቀፉ የሚገባቸው ከተሞችን የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንድ የማሻሻያ ሥራዎች በሁሉም ከተሞች በአንዴ ለመተግባር አዳጋች ናቸው፡፡ ስለሆንም በሁሉም ከተሞች በአንዴ ተግባራዊ ማድረግ በማይቻልባቸው ሥራዎች በአማካሪዎች ጥናት የተካተቱ ከተሞች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ በመቀጠልም ባለፉት ዓመታት የከተማ ማሻሻያ ፕሮግርምንና በተለይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የከተሞች የመሠረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚተገበርባቸው ከተሞች ላይ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በንዑስ ፕሮግራሞቹ የታቀፉት የማሻሻያ ሥራዎች በነዚህ ከተሞች ተጀምረው በየጊዜው የሚስፋፉ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ዋና ከተሞችም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው አንዳንድ የመሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑባቸው በእቅድ ተይዟል፡፡

#### 2. አራቱንም የክትትልና የድጋፍ ሥርዓቶች መዘርጋት

የንዑስ ፕሮግራሞቹ አፈጻጸምን በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል አራቱንም የክትትልና የድጋፍ መሳሪያዎች ተጠናክረው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በክልልና በከተማ ደረጃ ባሉና ሥራው በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ የሥራ አፈጻጸም ክትትል የሚያደርጉና ድጋፍ የሚሰጡ ክፍሎች በየመዋቅሩ ይደራጃሉ ወይም ያሉ ከሆነ ደግሞ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ እንደዚሁም በሕግ አውጪው መዋቅር ውስጥ ፈጻሚው አካል ሥራዎቹን በአግባቡ እየተገበረ መሆኑን መከታተል የሚችል አቅም እንዲፈጠርለት ይደረጋል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የሕዝቡን የተደራጀና ቀጥተኛ ተሳትፎ በየእርከኑ በማጠናከር የአፈጻጸም ክትትሉ እንዲጎለብትና ከሕዝቡ የሚፈለገው ድጋፍ እንዲገኝ የተመቻቸ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ በመጨረሻም በፕሮግራሙ የታቀፉት ሥራዎች አንድ ምዕራፍ ላይ ሲደርሱ የተሟላ ጥናት በማካሄድ አፈጻጸማቸውና ውጤታቸው እንዲገመገም ይደረጋል፡፡

ከዚህ አንጻር በመጀመሪያ በእያንዳንዱ ፈጻሚ አካል መዋቅር ውስጥ ያሉት የዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ፣ የውስጥ ቁጥጥር፣... ወዘተ ክፍሎች እንዲጠናከሩና የእያንዳንዱን ንዑስ-ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች አፈጻጸሞችን በተሟላ አኳኃን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ ፈጻሚ አካላት ስለሚመለከታቸው ንዑስ-ፕሮግራም፣ ፕሮጀክትና ዝርዝር ሥራዎች በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ለማድረግ አስፈላጊው ኦሪየንቴሽንና ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን የዕቅድ አፈጻጸሙንም በቀጣይነት ክትትልና ግምገማ የሚያደርጉበት ሥርዓት ተቀይሶ ይተገበራል፡፡ የውስጥ የቁጥጥር አካል በአግባቡ ተደራጅቶ አፈጻጸሙን በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሕግ አውጪው አካል አስፈጻሚውን በቅርብና በመደበኛነት የፕሮግራሞቹንና የፕሮጀክቶቹን አፈጻጸም የሚከታተልበት ሥርዓት ተቀይሶ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የተለያዩ የሕዝብ አደረጃጀቶች፣ የሙያና ብዙሃን ማህበራት በቅርቡ ያሉትን ሕግ-አውጪና አስፈጻሚ አካላትን የሚቆጣጠሩበትና የሚገመግሙበት ስርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ በመጨረሻም በየጊዜው በሚካሄድ ሙያዊ የዳሰሳ ጥናት የፕሮግራሙን አፈጻጸም፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳቦች፣ የተገኙ የተሻሉ ልምዶችን፣ የፕሮግራሙን ፋይዳ መገምገምን የሚመለከት ነው፡፡ በነዚህ አራት የውጭና የውስጥ የክትትልና የግምገማ አግባቦች በመጠቀም የፕሮግራሙን አፈጻጸም የተሻለ እመርታ እንዲያሳይ ይደረጋል፡፡

### 3. *ሥራዎቹን በፕሮጀክት መልክ በመቅረጽ መፈጸም*

በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱት ተግባራት በጣም በርካታ በመሆናቸው ለአፈጻጸም በሚያመች መልኩ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሥራዎቹ በፕሮጀክት መልክ እንዲቀረጹ ተደርገዋል፡፡ ተመሳሳይ ግብ ለማሳካት የተቀረጹትን ተግባራት በአንድ ላይ በማደረጃት፣ ለእያንዳንዱም የጊዜ ገደብ፣ አስፈጻሚ አካልና በጀት እንዲለይለት በማድረግ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ እንዲታቀፉ ሆኗል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ፕሮግራም በድምሩ አስር (10) ያህል ፕሮጀክቶች እንዲኖሩት የተደረገ ሲሆን፤ እነዚህም የመሬትና ከተማ ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም አራት ፕሮጀክቶች፣ የታክስና ፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ሦስት ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም ሦስት ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ሥራዎቹን በፊት ከነበሩት ሃያ ሦስት ፕሮጀክቶች በመቀነስ በዚህ መልክ አደራጅቶ ለመፈጸም መንቀሳቀስ ለክትትልና ለግምገማ የተሻለ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ታምኖበታል፡፡ በተጨማሪም ሥራዎች በፕሮጀክት መደራጀታቸው ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ፋይናንስ ለማፈላለግም አመቺ እንደሆነ ይገመታል፡፡

### 4. አስፈፃሚ አካላትን በግልፅ ለይቶ መንቀሳቀስ

እስካሁን ከነበረው የፕሮግራም አፈፃፀም ሥራዎችን በባለቤትነት ከመምራት አኳያ የተከሰቱ ችግሮችን ከወዲሁ ቀርፎ ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን የንዑስ-ፕሮግራሞችና የፕሮጀክት ባለቤት ተቋማት፣ እንዲሁም ተባባሪ አካላት በፌደራል፣ በክልልና በከተሞች ደረጃ ተለይተው መታወቅ አለባቸው፡፡ በፌደራልና በክልል ደረጃ ያሉ ባለቤቶችንና ተባባሪ አካላት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተለይተዋል፡፡ በከተማ ደረጃ ፕሮግራሙን በባለቤትነት የሚያስፈጽመው የከንቲባ ኮሚቴው ሲሆን፣ ንዑስ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በባለቤትነትና በተባባሪነት ተግባራዊ የሚያደርጉ አካላትን እንደ የክልሉ ተጨባጭ ሁኔታና በከተሞች የተደራጁ የአስፈፃሚ አካላት አቅም ክልሎች በቅድሚያ መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 5. *ሥራዎቹን አቀናጅቶ መፈጸም*

በፕሮግራሙ ውስጥ በተካተቱት ፕሮጀክቶችና ተግባራት በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲቻል በከተሞች ውስጥ የሚተገበሩ በመሆናቸው በመካከላቸው ትስስር መኖሩ የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም የሥራና የኃላፊነት ድግግሞሽና መደራረብ እንዳይፈጠር የንዑስ ፕሮግራሞቹ ፈጻሚና የፕሮግራሙ አስተባባሪ አካላት እንደዚሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት

ተናበውና ተቀናጅተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱት ተግባራት በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ ከተጀመሩና ተያያዥነት ካላቸው ሥራዎች ጋር ተሳስረው መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በፕሮግራሙ ውስጥ የታቀፉና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ሥራዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በሚመለከታቸው አካላት የተጀመሩ መሰል ስራዎች ጋር ተሳስረው መፈጸም አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የከተማ ገቢንና ወጪን የሚመለከቱ፣ ከሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር እንደዚሁም ከፍትህ ሥርዓት ጋር የተያያዙ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ የማሻሻያ ሥራዎች በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ በሚመለከታቸው አካላት እየተካሄዱ ከሚገኙ መሰል ፕሮግራሞች ጋር ተቀናጅተው መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡

## 6. የፕሮግራሙ አፈጻጸም የክትትልና የግምገማ ሥርዓት

6.1 ፕሮግራሙን ማወያየትና መዘርዘር

ሀ. በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ሁሉንም የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት በማወያየት እንዲዳብር፣ እንደዚሁም የጋራ አመለካከት፣ ተነሳሽነትና የባለቤትነት ስሜት እንዲያድግ ይደረጋል፣

ለ. ተሻሽሎ በተዘጋጀው አገራዊ ፕሮግራም መሠረት እያንዳንዱ የፌደራል አካል፣ ክልሎችና ከተሞች ዝርዝር ዕቅዳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ ዕቅዱ የቀጣይ ቀሪ የፕሮግራም ዓመታት መርሐ-ግብር፣ የ2002 በጀት ዓመት እቅድ የያዘ ይሆናል፡፡

6.2 የፕሮግራም አፈጻጸም ክትትል ሥርዓት መዘርጋት

አራቱን የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት የሚያስፈጽሙ አደረጃጀቶችን በየደረጃው ማጠናከር

ሀ. በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ በሚገኙ ፕሮግራሙን በሚያስፈጽሙ መዋቅሮች የዕቅድ ዝግጅትና ክትትል፣ የውስጥ ቁጥጥር/ኦዲት/፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ ... ወዘተ ክፍሎች እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣

ለ. በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ምክር ቤቶች ውስጥ የፕሮግራሙን አስፈጻሚ አካላትን የሚከታተሉና የሚቆጣጠሩ ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣

ሐ. የተደራጁ የብዙሃንና የሙያ ማኅበራት ለፕሮግራሙ አፈጻጸም ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግና አፈጻጸሙንም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣

መ. የፕሮግራሙን አፈጻጸም፣ ውጤት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ... ወዘተ በማጥናት ለላቀ አፈጻጸም ድጋፍ የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ አማካሪ ድርጅቶች፣... ወዘተ በዚህ ሥራ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

6.3 የተጠናከረ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት

ሀ. የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮግራሙ አፈጻጸም በውስጥ መዋቅራቸው ቢያንስ በየሦስት ወሩ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋሉ፣

| ንዑስ-ፕሮግራምና ዋና አስፈፃሚ | ፕሮጀክት | አስፈፃሚ አካላት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ፌደራል | ክልል | ከተማ |
| የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም (የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር) | የመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | |
| | የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | |
| | የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | |
| | የከተማ ፕላን የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና የክልል የፕላኒንግ አሃዶች | |
| የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም (የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር) | የታክስ ሥርዓትና የገቢ አቅም ማሻሻያ ፕሮጀክት | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | |
| | የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ፕሮጀክት | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | |
| | የተቋም ግንባታና የሰው ኃይል ልማት ኘሮጀክት | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | |
| የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም (የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር) | የከተማ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የክልል አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት | |
| | የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | |
| | የፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት* | የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር | የአቅም ግንባታ ቢሮ | |

* የፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክትን በክልል ደረጃ በቅንጅት የሚያስፈፅሙት አካላት በርካታ ሲሆኑ፣ የአቅም ግንባታ ቢሮ በዋነኛነት፤ የአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፣ የክልሉ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ፣ የፍትህ ቢሮ፣ የክልሉ የመንገኛ ብዙሃን ኤጀንሲና የትምህርት ቢሮ በተባባሪነት ያስፈፅሙታል።

ለ. የክልል አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮግራሙ አፈጻጸም በየሦስት ወሩ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ያስተላልፋሉ፣

ሐ. የሪፖርቶቹ አቀራረብ በፕሮግራሙ ላይ የተቀመጡትን ግቦችና ተግባራት እንደዚሁም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተመለከቱትን አመልካቾች መሠረት ያደረገ ይሆናል፣

መ. የተጠናከረ የመስክ ጉብኝት በመደበኛነት በማካሄድ ስለ ፕሮግራሙ አፈጻጸም ቀጣይነት ያለውና ጥብቅ ክትትል ይካሄዳል

- የፌዴራል አስፈጻሚና አስተባባሪ አካላት ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ አንዴ ፕሮግራሙ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው አካባቢዎች የመስክ ጉብኝት ያካሂዳሉ፣
- የክልል አስፈጻሚና አስተባባበሪ አካላት ፕሮግራሙ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች በየሩብ ዓመቱ የመስክ ጉብኝት ያካሂዳሉ፣
- የከተማ አመራሮች ወደ ከተሞቻቸው የበታች መዋቅሮች እና ፕሮግራሙ ተፈጻሚ ወደ ሚሆንባቸው አካባቢዎች በመውረድ የፕሮግራሙን አፈጻጸም ይከታተላሉ፣

ሠ. የፕሮግራሙን አፈጻጸም የሚያሳዩ ማንኛውም ዓይነት መረጃዎች በአግባቡ በየመዋቅሩ ተደራጅተው ይያዛሉ፣ ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው እንዲተላለፉ ይደረጋል፣ ለሕዝቡም ግልጽና ተደራሽ ይሆናሉ፣

## 6.4 የክትትልና የመገምገሚያ አመልካቾችን መቅረጽ

የፕሮግራሙን አፈጻጸም በትክክል ለመከታተል የሚያስችሉ አመልካቾች ተቀርጸው በየጊዜው ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለመከታተል በየንዑስ ፕሮግራሙ እንደ ዋና አመልካች ከሚያገለግሉት የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡-

### ሀ. የመሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም አፈጻጸም ዋና ዋና አመልካቾች

- ለመሬትና መሬት-ነክ ንብረት መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ቅድመ ሁኔታ ያሟሉ ከተሞች ቁጥር (ኢንፍራስትራክቸር፣ የሰው ኃይል፣ አደረጃጀት፣ ሶፍትዌር፣ የመረጃ ደህንነት፣ የፀደቀ ባለሞያዎች የሥነ ምግባር ደንብ፣ ወዘተ.)
- የንብረት ግምትና የግብር አሠራር ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ፀድቆ ተግባራዊ የሆነባቸው ከተሞች ቁጥር፣
- በመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ዙሪያ የተጣራ መረጃ መሰብሰብና ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የጀመሩ ከተሞች ቁጥር፣
- በመሬትና መሬት ነክ መረጃ ማዕከላት የተመዘገበ መሬት መጠን / በመቶ/፣
- ሊዝ ተግባራዊ መሆን የጀመረባቸው ከተሞች ብዛት፣
- ሊዝ ተግባራዊ መሆን በጀመረባቸው ከተሞች በሊዝ የተያዘ መሬት ድርሻ ያሳየው ዕድገት፣
- ሙሉ ለሙሉ በሊዝ የሚቀርቡ መሬቶች በጨረታ ብቻ የሆኑባቸው ከተሞች ብዛት፣
- ለተለያዩ ልማትና አገልግሎት የተሰጠ መሬት መጠን፣
- ከመሬት ሊዝ የሚገኝ ገቢ ዕድገት፣
- የካሳ ክፍያ አነሰኝ ጥያቄና አከፋፈሉ የሚወስደው ጊዜ መቀነስ፣
- ለሕዝብ ጥቅም ከሚለቀቅ መሬት ለሚነሱ ነዋሪዎች የቢዝነስ/ ፕሮጀክት ሃሣቦች ያዘጋጁና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቹ ከተሞች ብዛት፣

- ለግሉ ዘርፍ የተሰጡ የከተማ ፕላን የሥራ ፈቃዶችና ወደ ሥራ የገቡ የግል አማካሪዎች ብዛት፣
- በከተማ ፕላን የተከናወኑ ስልጠናዎች አይነት፣ የሰልጣኞች ቁጥር፣
- የተዘጋጁ መሰረታዊ ካርታዎች ብዛት፣
- የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖች ብዛት፣
- የተዘጋጁ የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች መሠረት የተደረጉ የአሠራር ማስተካከያዎች፣
- የሚዘጋጁ ፕላኖች ከከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ አኳያ የተቃኙ መሆናቸው፣
- የተደራጁ የግል የከተማ ፕላን አማካሪ ድርጅቶች ብዛት፣
- ወዘተ.።

## ለ. የታክስና ፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም ዋና ዋና አመልካቾች

- ለየሥራው የተዘጋጁና ሥራ ላይ የዋሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ብዛት፣
- በየሥራ መስኩ የሰለጠኑ ሰራተኞችና ባለሙያዎች ብዛት
- የልማት አቅጣጫንና የቀበሌውን ነዋሪ መሠረት አድርገው የፋይናንስ ዕቅድ ያዘጋጁ ከተሞች ብዛት፣
- ለከተሞች ተስማሚ ሆኖ የተዘጋጀውን የበጀት ማሻሻያ የአዘገጃጀትና አሠራር ሥርዓት የተገበሩ ከተሞች ብዛት፣
- ወጪ ቆጣቢ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች ብዛት
- አዲሱን የሂሣብ አያያዝ እንደ የክፍያ አፈፃፀሙ ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች ብዛት፣
- ዘመናዊ የገቢ አስተዳደር ማሻሻያ ሥርዓት የተተገበረባቸው ከተሞች ብዛት፣
- የከተሞች የገቢ መጠን ዕድገት
- በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች ብዛት
- የፋይናንስ ድጋፍ የተደረገላቸው ከተሞች ብዛት፣
- የውስጥና የውጭ ኦዲት አሠራር ሥርዓት የተዘረጋባቸው ከተሞች ብዛት፣
- ወዘተ.።

## ሐ. የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም ዋና ዋና አመልካቾች

- የከተማ አስተዳደር አቋም ያላቸው የከተሞች ብዛት፤
- አደረጃጀታቸውንና የሰው ኃይል ልማታቸውን በራሳቸው የማቀድና የመተግበር አቅም ያላቸው የከተሞች ብዛት፤
- በመዋቅሮቻቸው ሥር ለሚኖሯቸው የሥራ መደቦች በሙሉ የተሟላ የሥራ መዘርዝር ያላቸው የከተሞች ብዛት፣
- ለሚኖሯቸው የሥራ መደቦች የሥራ አፈጻጸም መለኪያዎች ያዘጋጁ የከተማ አስዳደሮች ብዛት፤
- ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸም ምዘና የሚያከናውኑ የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ብዛት፣
- የከተማ አስተዳደሮች ካሏቸው የሥራ መደቦች ውስጥ በባለሙያ የተሞሉ የሥራ መደቦች ብዛት/መቶኛ፣
- ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከሕዝብ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ብዛት፤
- የግሉ ማኅበረሰብና ማኅበራት በማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ያላቸው ተሣትፎ፣
- የተቀናጀ የከተማ መረጃ ያሰባሰቡና ያደራጁ ከተሞች ብዛት፣

- የሰው ኃይል መረጃ አያያዝና የሰው ኃይል ሥራ አመራር በኮምፒዩተር እንዲታገዝ ያደረጉ ከተሞች ብዛት፣
- በተለያዩ ሞያ የሰለጠኑ በለሞያዎችና የአመራር አካላት፣
- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ያደረጉና ውጤታማ የሆኑ ከተሞች ብዛት፣
- በከተማ ሥራ አመራር የረጅም ጊዜ ሥልጠና ያገኙ ባለሞያዎችና አመራሮች ብዛት፣
- የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶችን የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የሥነ-ምግባር ደንብ ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞችና ቀበሌዎች ብዛት፣
- በከተሞችና የቀበሌ ምክር ቤቶች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ኮሚቴዎች መቋቋማቸው፣
- ለምክር ቤቶችና በውስጣቸው ለሚቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተሰጡ ስልጠናዎች፣ የሰልጣኞች ብዛት፣
- በብዙሃን ማኀበራት የታቀፉ ወጣቶችና ሴቶች ብዛት፣
- የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰበት ከተማ-አቀፍ ራዕይ መኖሩና ራዕዩን በመቅረጹ ሂደት የተሳተፉ ሕዝብ/አካላት ብዛት፣
- የተቋቋሙ የትብብር ፎረሞች ብዛትና ዓይነት፣
- ለግሉ ሴክተር በተሻለ መልኩ እንዲቀርቡ የተደረጉ የከተማ አገልግሎቶች ብዛት፣
- የማኀበራዊ ፍርድ ቤቶችን ያቋቋሙ ከተሞች ብዛት፣
- ደንብ የማስከበር አገልግሎትን ያቋቋሙ ከተሞች ብዛት፣
- በከተሞች የሥነ-ምግባር መተላለፍና የሙስና ወንጀሎችን የመጠቆምና መርምሮ ለሕግ የማቅረብ አቅም መጎልበት፣
- በከተሞች በመንግሥት ባለሞያዎችና ተሿሚዎች የሚከናወኑ የሥነ-ምግባር መተላለፍና የሙስና ወንጀሎች መቀነስ፣
- ወዘተ…።

## 6.5 የፕሮግራም አፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት

ሀ. በፕሮግራሙ የተቀመጡትን ግቦችና መለኪያዎች መሠረት ያደረገ ግምገማ በየደረጃው በመደበኛነት ማካሄድ፣

ለ. የክልል ፈጻሚ አካላት የፕሮግራሙን አፈጻጸም በየወሩ ይገመግማሉ፣ የግምገማውንም ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋሉ፣

ሐ. የክልልና የፌዴራል ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የፕሮግራሙን አፈጻጸም በየሩብ ዓመቱ በጋራ ይገመግማሉ፣

መ. የክልልና የከተማ ምክር ቤቶች የፕሮግራሙን አፈጻጸም ከአስፈጻሚ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ በጋራ ይገመግማሉ፣

ሠ. የፕሮግራሙ አፈጻጸም ያስገኘው ፋይዳና ውጤት፣ የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች፣ የተገኙ የተሻሉ ልምዶች… ወዘተ በተመለከተ ሙያዊ ጥናት በማካሄድ ለተሻለ ቀጣይ አፈጻጸም መጠቀም፣

ረ. በሚደረጉ ግምገማዎችና ጥናቶች በየዘርፉ የሚለዩ የተሻሻሉ ልምዶች በዝርዝር እንዲጠኑ ይደረጋል፣ ፋይዳቸው ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝም እንዲቀመሩ ይደረጋል፣ ለሌሎች የማስተላለፍ ሥራም ይከናወናል።

## 6.6 የቅንጅት ሥርዓት

ሀ. ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ ለተቀረጹት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ኃላፊነቱን በግልጽ ወስዶ በባለቤትነት የሚያስፈጽም አካል በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

ለ. በፌደራል ደረጃ ከፍተኛ ውሳኔ፣ ማስተባበርና ክትትል ለሚያስፈልጋቸው ሥራዎች ብቻ ባለድርሻ የፌደራል አካላት አባል የሆኑበት የፌዴራል አስተባባሪ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣

ሐ. በክልል ደረጃ ከፍተኛ ውሳኔ፣ ማስተባበርና ክትትል ለሚያስፈልጋቸው ሥራዎች ብቻ ባለድርሻ የክልል አካላት አባል የሆኑበት የክልል አስተባባሪ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣

መ. የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስፈጻሚ አካላት መደበኛ የግንኙነት ጊዜ ለይተው ያለ ዝንፈት እየተገናኙ ሥራዎቻቸውን ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፡፡

## II. የፋይናንስ ፍላጎት

ፕሮግራሙን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ትክክለኛ የበጀት መጠን ይህንን ፕሮግራም መሠረት በማድረግ ዝርዝር ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚታወቅ ሲሆን፣ በዚህ ሰነድ ዝግጅት ወቅት ብር 1.04 ቢልዮን የሚጠጋ ገንዘብ ሊያስፈልግ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ ይህ መጠን ክልሎችና ሌሎች አስፈፃሚ አካለት ፕሮግራሙን ለማስፈፀም የሚበቃ በጀት ለመመደብ ከወዲሁ እንዲዘጋጁ ጠቋሚ ነው፡፡

| ተ.ቁ | የንዑስ-ፕሮግራም/ፕሮጀክት ሥም | የፋይናንስ ፍላጎት (በሺ. ብር) | |
|---|---|---|---|
| 1 | **የመሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም** | | **63,500** |
| | የመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ ፕሮጀክት | 60,000 | |
| | የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት | 1,500 | |
| | የከተማ ፕላን አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | 1,200 | |
| | የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | 800 | |
| 2 | **የታክስና የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም** | | **15,200** |
| | የታክስ ሥርዓትና የገቢ አቅም መሻሻያ ፕሮጀክት | 3,200 | |
| | የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ፕሮጀክት | 10,000 | |
| | የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | 2,000 | |
| 3 | **የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም** | | **25,000** |
| | የከተማ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | 2,000 | |
| | የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | 20,000 | |
| | የየፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት | 3,000 | |
| | **ጠቅላላ** | | **103,700** |

# III. የአፈፃፀም መርሃ-ግብር

# የከተማ መሬትና ፕላን ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| **የመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃና ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ግብ አንድ<br><br>የመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ሥርዓት የሕግ ማዕቀፍ፣ የተቋምና የአሠራር ሥርዓት ተዘጋጅቶለት በተመረጡ ከተሞች ሥራ ላይ ይውላል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በረቂቅ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ እና ማቋቋሚያ አዋጆች፣ የካዳስተር ቀያሽ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅና አፈጻጸም ደረጃ መወሰን ደንብ ላይ ማስተካከያ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በከተሞች ሕጋዊ ካዳስተር (legal cadastre) ለመገንባት የቤዝ ማፕ ዝግጅትን/ወቅታዊ የማድረግ ሥራን ማከናወን፣ | ካርታ ሥራዎች ድርጅት፣ ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የመሬትና መሬት ነክ ንብረት የመረጃ ሥርዓት በከተሞች ተግባራዊ የሚሆንበት የቴክኖሎጂና የመረጃ ኢንፍራስትራክቸር የአፈጻጸም ደረጃ በጥናት መወሰንና የመሬት መረጃ ሶፍትዌር ማዘጋጀት፣ | ፌደራል/የመረጃ ደህንነት ኤጀንሲ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ለምዝገባ ሥራ የሚያገለግሉ መመሪያዎችና የምዝገባና የካዳስተር ቅየሳ አሠራርና የመረጃ አጠቃቀመም ስታንዳርድ ማንዋሎች ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ሕጋዊ ካዳስተር ( Legal cadastre ) የሚመራ፣ የሚያስተዳድርና የሚከታተል አካል በፌዴራል፣ በክልልና በሕዝብ ብዛታቸውና የልማትና የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም አፈፃፀም ብቃታቸው በተመረጡ 20 የከተማ አስተዳደሮች በአዋጅ ማደራጀት፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | ከአንድ የከተማ መሠረታዊ ካርታ የሚዘጋጀው ሕጋዊ የካዳስተር (Legal cadastre) ማፕ ለሌሎች የከተማ ካዳስተርና መረጃዎች ( ለታክስ፣ መሠረተ-ልማት፣ ፕላን፣ ወዘተ... ) መነሻ ግብዓት እንዲሆን በጥንቃቄ ማዘጋጀትና የመረጃው ጥራትና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ የሚጠበቅበትን ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ/የመረጃ ደህንነት ኤጀንሲ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | በመሬትና መሬት-ነክ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር የተሰማሩ ባለሞያዎችና የሥራ ኃላፊዎች የሚተዳደሩበት የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተፈፃሚ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | በመሬትና መሬት-ነክ መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መስራት፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | ብቃትና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የሰው ኃይል በጥንቃቄ መልምሎ በመረጃ ሥርዓት አስተዳደር መዋቅር ማሰማራት፣ ለዚህም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በከተማ ሥራ አመራር በማስተርስ ዲግሪ የሚመረቁትን በዋናነት መጠቀም፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 10 | የሚመለከታቸው አካላት ከኢንፎርሜሽን ኔትዎረክ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመሆን የሚደራጀው መረጃና ኔትዎረክ ጥራትና ደህንነቱ አስተማማኝ መሆኑን በየደረጃውና በየጊዜው ማረጋገጥ፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ/የመረጃ ደህንነት ኤጀንሲ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 11 | ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የመሬት መረጃ ሥርዓትን በተመለከተ አጫጭር ሥልጠናዎች በቋሚነት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 12 | ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ዋና ከተሞችን ጨምሮ የአነስተኛና የመካከለኛ ከተሞች የመሬትና የመሬት-ነክ መረጃ ፍላጎታቸውን በመለየት የመሬት ምዝገባና መረጃ አያያዝ ሥርዓት ለመዘርጋት (የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የአደረጃጀት፣ ወዘተ) የልማት ፕሮግራም መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ ከተመረጡ ፓይለት ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት ለተለያዩ ከተሞች ተስማሚ የሆነ ተቋማዊና የመረጃ ኢንፍራስትራክቸር መረጣ በማድረግ መገንባት፡፡ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br><br>የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫና ግብይት፣ እንዲሁም የመሬት አስተዳደር ሥራ በትክክለኛ መረጃና አሰራር የተደገፈ ይሆናል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የንብረት ግምትና የግብር አሠራር ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የመሬትና ንብረት ዝውውር እንዲሁም ባለቤትነት ማስረጃ ተገቢ የአሰራር ሥርዓት ተቀምጦለት በወቅቱ ተመዝግቦ የሚሰራበትን መመሪያ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | ከመሬት ገበያው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቅርብ ለተቆራኙ መሬት ነክ መረጃ ፈላጊዎች የሚደርስበት አሰራር መፍጠር ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ልዩ ልዩ የማስታወቂያና የማስተማሪያ መድረኮች በመፍጠር ሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የንብረት ግምት አሠራር ፣ ባለቤትነት ማረጋገጫና የንብረት ዝውውር አሠራር አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | የተገኙ ጠቃሚ ልምዶችን በመለየትና በመቀመር የሰለጠነ የሰው ኃይል በማደራጀት በቀጣይ በሌሎች ከተሞች ተከታታይ ሥራ የሚከናወንበት ስትራቴጂና ኘሮግራም መቅረፅ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | በከተሞች የመሬት መረጃ ሥርዓት አፈጻጸም ሂደትን መከታተል፣ መደገፍ፡፡ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አንድ**<br><br>የሊዝ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የተሟላ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የከተማ አስተዳደር በተቋቋመባቸው ከተሞች ሥራ ላይ እንዲውልና በቀጣይነትም እንዲሻሻል ማድረግ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በክልሎች የተዘጋጀው የሊዝ ደንብ ሁሉም ከተሞች በሊዝ ሥርዓት ብቻ እንዲተዳደሩ በመደንገግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ መስጠት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 2 | የሊዝ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ በሆነባቸው ከተሞች በምሪት ይዞታ የሚተዳደሩ መሬቶች ወደ ሊዝ ሥሪት የሚሸጋገሩበትን የአፈፃፀም ስትራቴጂ በመንደፍ ለክልሎች ማስተላለፍ፣ ለተግባራዊነቱም ድጋፍ መስጠት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የሊዝ ሥርዓትን በተመለከተ በተለያዩ የኅብረተሰብና አስፈፃሚ አካላት ያለውን የተሳሳተ አመለካከት የማጥራት ተግባራትን በማከናወን የጋራ ግንዛቤ መፍጠር፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በከተማ አስተዳደሮች አዲስ የሚሰጥ መሬት በሊዝ ሥርዓት እንዲሆን ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት ለክልሎች ማሰራጨትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ጨረታ መሬት በሊዝ የሚቀርብበት ብቸኛው አሠራር እንዲሆን ማድረግና አሠራሩን ግልፅና በመደበኛነት የሚከናወን ለማድረግ በማገ የተደገፈ፣ ጨረታ ስለወጣበት አካባቢ የተሟላ መረጃ በተለያየ ሚዲያና አግባብ የሚሰጥ እና በማዕከል በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ማድረግ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | በሊዝ የተወሰደ የከተማ መሬት ላይ ግንባታ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም በሊዝ ላይ የሚከፈለውን ቅድመ-ክፍያ ወጥ ማድረግ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | ለኢንቨስትመንት የሚሰጡ ቦታዎች የመጠንና የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ስታንዳርዶች ማዘጋጀት፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | ለኢንቬስትሜንት የሚቀርብ መሬት ንብረቶች ያልሰፈሩበትና የይገባኛል ክርክር የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥና የሳይት ፕላን በማዘጋጀት ለተጫራቾች ማሳወቅ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | የሊዝ መነሻ ዋጋ መለኪያ ስታንዳርድ እና የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት ክልሎች አጽድቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ማድረግ። | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br>የከተማ መሬት አቅርቦቱ ግልፅ ቅደም ተከተል እና የአፈፃፀም ሥርዓት ኖሮት መፈፀም ይጀምራል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ለቤት ልማት የሚሰጥ የከተማ መሬት ቅድሚያ ለተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ መስጠት፣ የኮንዶሚኒየም ግንባታ በሚካሄድባቸው ከተሞች ለማኅበራትና ለግለሰቦች በቀጥታ ማደልን ማስቆም፣ እንዲሁም በመካከለኛና ትላልቅ የግል ሪል ስቴት ኩባንያዎች ለሚገነቡ የመኖሪያ ሕንፃዎች የሚቀርብ ቦታ በጨረታ፣ የከተሞቹን ፕላንና የከተማውን የሸንሻኖ ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በግል ሪል ስቴት ኩባንያዎች ለሚገነቡ የቢዝነስ ሕንፃዎችና ሆቴሎች የሚቀርብ ቦታ በጨረታ፣ የከተሞቹን ፕላንና የከተማውን የሸንሻኖ ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቬስትሜንት የሚውል የኢንዱስትሪ ዞን ዝግጅት በመሬት ፍላጎት ላይና በከተሞቹ የማደግ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄና የተሟላ መመሪያ ኖሮት እንዲፈፀም ማድረግ፣ የመሠረተ-ልማት የተሟላለትና ለዚህ ጉዳይ የወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ክላስተሮችን ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሰጠው የከተማ ቦታ የመሠረተ-ልማት የተሟላለትና ለዚህ ጉዳይ የወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ እንዲሆን ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | በቀጣይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የሚቀርብ የከተማ ቦታ በጥንቃቄ፣ በቁጠባና ከፍተኛ የማምረቻ ቦታ ችግር ላለባቸው ብቻ በግልፅነት ማቅረብ፣ | ከተማ | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| 6 | መንግሥት ለሚገነባቸው ት/ቤቶችና የጤና ተቋማት የቦታ አቅርቦት ማመቻቸት እና በግል ለሚገነቡ ተመሳሳይ ማኅበራዊ ተቋማት ቦታ በጨረታ ብቻ ማቅረብ፡፡ | ከተማ | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| **ግብ ሦስት**<br>ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበት ሕግ ማስፈጸሚያ ደንብ፣ የአፈጻጸም መመሪያና ማንዋል የተሟላና ወጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ለሕጉ አፈጻጸም የሚረዱ ሞዴል የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀትና ማፀደቅ፣ | ፌደራል/ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በደንብ፣ በሞዴል መመሪያ እና ማንዋል ላይ እስከታችኛው የአመራር፣ አስፈጻሚ እና የባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር፣ | ፌደራል/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| 3 | የወጡት ሕጎች የተሟላና ወጥ ተፈፃሚነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በየደረጃው ክትትል መኖሩን ማረጋገጥ፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 4 | ለእነዚህ ሕጎች ተገዢ የማይሆኑ ዜጎች ላይ በሕጉ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ፈጥኖ በመውሰድ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| 5 | ለልማት ከሚውል መሬት ላይ ለሚነሱ ቀድሞ በግብርና ይተዳደሩ ለነበሩ ገበሬዎች ወደ ከተማ እንቅስቃሴ እንዲገቡ የሚያስችል የቢዝነስ ፕላንና ነፃ የማማከር አገልግሎት ማቅረብ፣ እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋት የሚደረገውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡ | ከተማ | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| **ግብ አራት**<br>በከተሞች ለልማት የሚፈለግን መሬት ቀድሞ በመለየት፣ በመያዝ እና በማልማት ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **1** | ከአገልግሎት በታች የዋሉ መሬቶችን ቀድሞ በመለየት፣ በማዘጋጀት እና በመያዝ (Land Banking)፣ ለተሻለ ልማት ለማዋል የሚያስችል የአሰራር ስልት መንደፍ፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| **2** | የመሬት ልማትን በተመለከተ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ሞዴል ደንብና መመሪያ ማዘጋጀትና የጋራ መግባባት በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| **3** | ለማንኛውም ዓይነት ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶችን በማዘጋጀት በንብረት መዝጋቢው ድርጅት (registry) መሬቶቹን ቆጥሮ በማዘጋጃ ቤቱ ስም እንዲመዘገቡ በማድረግ መያዝ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| **4** | ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚቀርቡ የቦታ ስፋት መጠን ስታንዳርድ (Optimum Plot Size) እና የሽንሻኖ ሥርዓት መመሪያ ማዘጋጀትና የጋራ መግባባት በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በመሬት ላይ በሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተረቀቀው ደንብ እንዲፀድቅና ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ፣ ደንቡ በፀደቀባቸው ክልሎች ደግሞ ተግባራዊነቱን ማጠናከር፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ሕገ-ወጥነትን የሚከላከሉና የሚቆጣጠሩ በየደረጃ የሚገኙ አካላትን አቅም ( በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀት፣ በአሰራር፣ ወዘተ…) ማጠናከር፣ | ክልል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 3 | የመሬት ሕገ-ወጥነትን በተመለከተ በየደረጃው ያለውን የአመለካከት ችግር ለመቅረፍ ለሕብረተሰቡ፣ ለአስፈፃሚ አካላትና ለአመራሩ ትምህርት መስጠት፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የከተማ አመራር ለችግሩ ትኩረት በመስጠት ሕገ-ወጥነትን በመከላከልና በመቆጣጠር ለተሰማሩ አስፈፃሚ አካላት የተጠናከረ ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 5 | የተፈፀሙ ሕገወጥ የመሬት ወረራዎችንና ግንባታዎችን የተሟላ መረጃ በመያዝ ማፍረስ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | አዲስ ሕገወጥነትን ሳያበረታታና የከተሞች ፕላን አተገባበርን ሳያደናቅፍ ነባር ሰነድ አልባ ይዞታዎችን መልክ ለማስያዝ የሬጉላራይዜሽን ሕግና ወጥ የሆነ የአፈፃፀም ሥርዓት በማስቀመጥ ተፈፃሚ ማድረግ፣ በዚህም ሰነድ አልባ ይዞታዎች የተሟላ ሕጋዊነት እንዲኖራቸው ማድረግ። | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| | **የከተማ ፕላን የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አንድ**<br><br>የከተማ ፕላን ዝግጅትንና አፈፃፀምን በተሟላ መልኩ ለማከናወን፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም በፌደራል፣ በክልሎችና በከተሞች ይገነባል። | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 1 | የተዘጋጀውን የከተማ ፕላን አዋጅ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ይበልጥ ማስተዋወቅ፣ ክልሎችና ከተሞች የሚየዘጋጇቸው ፕላኖች አዋጁ በሚያዘው መሠረት መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የፌደራል የከተሞች ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ለግሉ ዘርፍ ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት እንዲችል የሰው ኃይል አቅም መገንባት፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 3 | የከተማ ፕላኑን አዋጅ ለማስፈፀም የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ በየክልሉ እንዲፀድቅ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ቀደም ሲል የተዘጋጁት የከተማ ፕላን ማንዋሎችና ለአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ካርታ አዘገጃጀት የተረቀቁ ማንዋሎች/መመሪያዎች ለሁሉም ክልሎች/ከተሞች እንዲዳረሱና ባለሞያዎችም እንዲሰለጥኑባቸው ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |

**ግብ አምስት**

በመሬት ላይ የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራትን የማስቆምና የማስተካከል ሥራ ግልፅ ፣ ፍትሐዊና ከከተማው ኢኮኖሚ ጋር በተሳሰረ ሁኔታ መፈፀም ይጀምራል፡፡

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | የሚዘጋጁት ፕላኖች በየከተማው ምክር ቤት ፀድቀው የየከተማው ሕግ እንዲሆኑና እንዲከበሩ ማድረግ፣ በዚህ መልክ የጸደቁ ፕላኖች ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ የከተማ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፣ | **ክልል** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | የፌደራል የከተሞች ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ለክልሎችና ለከተሞች በከተማ ፕላን ዝግጅት፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ የመስጠትና ግሉን ዘርፍ የማጠናከር ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣ | **ፌደራል** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የከተማ ፕላን እንዲዘጋጅ የከተማ ፕላን ሥራ ፍቃድ የሚሰጥና ተገቢውን ቁጥጥር የሚያደርግ አካል በፌደራል መሰየም፣ | **ፌደራል** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | በክልሎች ተቋቁመው ሥራ የጀመሩ የከተማ ፕላን ተቋማትን ማጠናከር፣ ተቋማቱ ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች ተቋቋመው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን፣ | **ፌደራል/ክልል** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | በሁሉም ከተሞች የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖችን የሚያስፈፅሙ አካላትን ማጠናከርና አቅማቸውን መገንባት፡፡ | **ክልል** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br><br>በከተማ ፕላን ዘርፍ ያለውን ፍላጎት ለማርካት ብቁ የሆነ እንዲሁም ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችል የግል ዘርፍ ይፈጠራል | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የፀደቀውን የከተማ ፕላን አዋጅ እና በየክልሉ እንደሚፀድ የሚጠበቀው የማስፈፃሚያ ደንብን መሠረት በማድረግ የግሉ ዘርፍ በከተማ ፕላን ዝግጅት የሚሳተፍበትን መመሪያ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በቤቶች ልማት ፕሮጀክት አዳዲስ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን በማደራጀት ዙሪያ የተገኘውን ልምድ በመጠቀም ግልፅ በሆነ አሰራር የግል የከተማ ፕላን አማካሪዎችን ማደራጀት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በመመሪያው መሠረት የሥራና የንግድ ፍቃድ አውጥተው ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉትን የግል አማካሪዎች በተዘጋጁት ሕጎችና ማንዋሎች ዙሪያ ስልጠናና የተለያዩ ድጋፎች ( ብድር፣ የሥራ ትስስር፣ ወዘተ... ) እንዲያገኙ ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የግል አማካሪዎች የሚያዘጋጇቸው ካርታዎችና ፕላኖች በአዋጁና በተዘጋጁት ማንዋሎች/መመሪያዎች እንዲሁም የጥራት ደረጃ/ ስታንዳርድ ወጥቶላቸው በዚያ መሠረት መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ በየክልሉ ቁጥጥር ማጠናከር፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | የፀደቀውን የከተማ ፕላን አዋጅ እና በየክልሉ እንደሚፀድ የሚጠበቀው የማስፈፃሚያ ደንብን መሠረት በማድረግ የግሉ ዘርፍ በከተማ ፕላን ዝግጅት የሚሳተፍበትን መመሪያ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 6 | የግል አማካሪዎች በፕላን ዝግጅት ብቻ ሳይሆን በአፈፃፀም ለከተሞች ድጋፍ የሚሰጡበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡ | ክልል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br>**የከተማ ፕላን ዝግጅት ባለሞያዎችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት የሚያስችል የትምህርትና የስልጠና አቅም ይፈጠራል፡፡** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን በከተማ ፕላን ዘርፍ ተቀብሎ የማሰልጠን አቅም በአመት ወደ አንድ ሺ ማሳደግ፣ | ፌደራል | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | |
| 2 | በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅና በሌሎች የሃገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች በከተማ ፕላን ዘርፍ የማስተርስ ስልጠናዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | ፌደራል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | |
| 3 | በከተማ ፕላን ዘርፍ በስልጠና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ እንዲከናወን ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | |
| 4 | ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋራ ጠንካራ የትብብር ግንኙነት በመፍጠር የማሰልጠን አቅምን ማሳደግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | ■ | ■ | ■ | |
| 5 | የከተማ ፕላን አዘገጃጀት፣ አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ አጫጭር ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ |
| 6 | እጩ ተመራቂዎች በኢንተርንሺፕ ፕሮግራም የሚታቀፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| **ግብ አራት**<br>የከተማ ልማት ሥራዎች የአገር አቀፍ የከተማ ልማት ፖሊሲንና ፖሊሲውን መሠረት አድርገው የሚዘጋጁ ክልላዊ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን መሠረት አድርገው የሚከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ለትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች በውጭ አማካሪዎች የተዘጋጁትን ረቂቅ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ከወጣው የከተማ ልማት ፖሊሲና ከየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመፈተሽ ማፅደቅ፣ | ክልል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | የሌሎች ክልሎችን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ለጋምቤላ፣ ለአፋር፣ ለሶማሌና ለሐረሪ ክልሎች እንደዚሁም ለአዲስ አበባና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት፣ | ፌደራል/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | |
| 3 | የተዘጋጁ ክልላዊ ስትራቴጂዎችን ማስተዋወቅ /ግንዛቤ ማስጨበጥ/፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | ■ | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 4 | የተዘጋጁ ክልላዊ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን መተግበር፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | በክልል ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የክልል የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን አስመልክቶ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፡፡ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አምስት**<br>በክልል ደረጃ ለከተሞች የሚሠጡ ድጋፎች በከተማጠገጠር እና በከተሞች መካከል ያለውን ትስስር በሚያጠናክሩና ቀጣይነት ያለው ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የገጠርንና የከተማን ትስስር ለማጠናከር የሚያስችል ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በየክልሉ የሚገኙ የትልልቅና አነስተኛ ከተሞችን ሚና በመለየት ትስስራቸውን ማጎልበት የሚያስችሉ የልማት ድጋፎችን መስጠት፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የከተሞችን ሚና የሚመጥን ፈርጀ ብዙ የልማት ድጋፍና አቅርቦት በማካሄድ የከተሞችን ትስስር ማጎልበት፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ስድስት**<br>አነስተኛና መካከለኛ ከተሞች በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች ጋር ተሳስረውና ተቀናጅተው እንዲያድጉና ለቀጣይና ለዘላቂ ልማት ተገቢውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በ15 የናሙና ከተሞች የሳተላይት ምስልን በመጠቀም መሠረታዊ ካርታና ፕላን ለማዘጋጀት እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ውጤታማነት ከወጪ፣ ከጊዜና ከጥራት አንፃር መገምገምና ርምጃ መውሰድ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ድርጅት ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ካርታዎችን/ፕላኖችን በፍጥነትና በአነስተኛ ወጪ ማዘጋጀት ስለሚቻልበት ስልት ጥናት አድርጎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሰባት**<br>የከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል አደረጃጀት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ይሻሻላል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል አደረጃጀትን በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 2 | በእስካሁኑ ተሞክሮ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራምን ከማስፈፀም አኳያ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የታዩትን መልካም ተሞክሮዎች በመቀመር፣ በክልልና በከተማ ደረጃ በከተማ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትል በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን መቅረፅ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 3 | እንደ የከተሞቹ ደረጃ የተለዩትን የሥራ ሂደቶች ተፈፃሚ ማድረግ። | ክልል/ከተማ | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| **የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አንድ**<br>በመሬት ልማትና አስተዳደር ያሉትን ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች እንዲሁም አደረጃጀቶችን በመፈተሽ ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ ስታንዳርዳይዝ ይደረጋል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የመሬት ልማትና አስተዳደርን በተመለከተ በፌደራል፣ በክልልና በከተማ ደረጃ በተለይም በአዲስ አበባ ያሉትን ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች በመፈተሽ ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ ስታንዳርዳይዝ አድርጎ ማቅረብ፣ | ፌደራል/ክልል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | በመሬት አስተዳደር ዙሪያ ለማምጣት ከሚታሰበው መሠረታዊ መሻሻል አንፃር በየክልሉ የተዘጋጁ የመሬት ጉዳይን የተመለከቱ የሥራ ሂደቶች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በወሳኝነት ለመቅረፍ የሚያስችሉ መሆናቸውን መፈተሽና ማረጋገጥ፣ | ፌደራል/ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በየደረጃው የሚፈጠሩ አደረጃጀቶች ወጥና በከተማ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን የሥራ መጠንና ስፋት ሊሸከሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ። | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br>የመሬት ልማትና አስተዳደር፣ እንዲሁም የመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ አገልግሎቶች በቂ እውቀት፣ ክሕሎትና ቀና አመለካከት በያዘ የሰው ኃይል ይመራል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በመሬት ልማትና አስተዳደር፣ እንዲሁም በመሬትና የመሬት-ነክ ንብረት ምዝገባ የአቅም ግንባታ ስልትና የስልጠና መርሃ ግብር መንደፍ፣ | ፌደራል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | የስልጠና ሞጁሎች እንዲዘጋጁ በማድረግ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ | ፌደራል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 3 | ስልጠናዎቹን ለበለሞያዎችና ለአመራር አካላት በምዕራፍ መስጠት<br>▪ በመሬት ቅየሳ፣ በካዳስተር ሰረቬይንግ፣ በመሬት ነክ ንብረት ዋጋ ትመና፣ በንብረት ግምገማ (Appraisal)፣ በሊዝ ሕግና የአፈጻጸም ሥርዓት አሠራር፣ በመሬት ልማትና አያያዝ (Land Banking) በመሬት መረጃ አያያዝ፣ በመሬት ሊዝ አዋጅና ደንብ፣ በጨረታ አሠራር ስልት፣ በሊዝ መነሻ ዋጋ ስታንዳርድ፣ በካሳ ሕግ፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች፣ ወዘተ… | ክልል | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ |
| 4 | ከሞያ ማሳደጊያ ስልጠናዎች በተጓዳኝ አገልገሎቶቹን በሚሰጡ ሠራተኞችን አመለካከትና ሥነ-ምግባር የማሻሻያ ተከታታይ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | | | ■ | | | | | ■ |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | የስልጠናውን ሂደትና ውጤት መገምገም፣ ለተከታታይ የአቅም ግንባታ ኘሮግራም ማሻሻያ በግብዓትነት መጠቀም፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | በመሬት ልማትና አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ፣ በሊዝ አሰራር፣ በካሣ አከፋፈል፣ በመሬትና መሬት-ነክ ንብረት ግምት አሠራር የኅብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት መብቱን የሚያስከብር ነዋሪን መፍጠር፡፡ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |

## የከተሞች የታክስ ሥርዓትና የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ-ፕሮግራም

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | **የታክስ ሥርዓትና የገቢ አቅም ማሻሻያ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ አንድ**<br>ከአገር አቀፍና ከክልል የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ጋር በተጣጣመ መልኩ የከተሞችን ገቢ ለማሳደግ የሚረዱና ገቢ የመሰብሰብ አቅምን የሚያሳድጉ፣ አሰባሰብና አጠቃቀምን የሚያሻሽሉ መመሪያዎችና ማንዋሎችን በማዘጋጀት በከተሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የታክስ ማሻሻያ ኘሮግራም ዓላማዎችንና ሕግጋትን መሠረት በማድረግ ከተሞች በአዋጅ የተሰጣቸውን ታሪፍ የማውጣት ስልጣን በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችላቸው ደንብና መመሪያዎች በክልሎች እንዲወጡ ማድረግ፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ተጠንተው በክልሎች እጅ የሚገኙትን የከተሞች ታሪፎች ከመጽደቃቸው በፊት በየደረጃው እስከ ቀበሌ ድረስ ኅብረተሰቡ እንዲወያይባቸውና በመጨረሻም በየክልሉ ም/ቤት$ እንዲፀድቁና በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በግልጽ መስፈርት ላይ የተመሠረተ የከተሞች ፍትሐዊ የግብር ምደባ፣ የግብር ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ከእዚህ ጋር በተያያዘም በየከተማው ያለውን ግብር ከፋይንና ያለበትን ውዝፍ የግብር መጠን በመለየት በአግባቡ መመዝገብና በወቅቱ መሰብሰብ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ከተሞች ከንግድ አገልግሎት ገቢ፣ ከከተማ ቦታና ቤት ግብር እና ከሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች የሚገኙ ገቢዎችን አስተዳደር ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት እና ሌሎች በኮምፒዩተር የተደገፉ የአሠራር ማንዋሎች ማዘጋጀትና መተግበር፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | የገቢ አስተዳደር ማሻሻያ ሥርዓት በተዘረጋላቸው ከተሞች የገቢ አሰባሰብ ባልተማከለ መልኩ /ለምሣሌ በቀበሌዎች፣ በባንኮች እና በመሳሰሉት/ እንዲከናወን ማድረግ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 7 | የግብር አሰባሰብ ውጤታማነት ደካማ በሆነበት የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት እንዲሳተፉ ማድረጢ ከአዋጭነትና ከቅልጥፍና አንፃር በክልል ደረጃ በተማከለ መልኩ እንዲሁም በትልልቅ ከተሞች ድጋፍ የአነስተኛና በአቅራቢያ የሚገኙ ከተሞች ገቢ የሚሰበሰብበትን መንገድ መቀየስ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | ከግብር ከፋዩ ስለተሰበሰበው የገቢ አፈፃፀም እና አጠቃቀም ለኅብረተሰቡ መረጃ የሚቀርብበትን የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ሥርዓት ለከተሞች ተስማሚ በሆነ መልኩ መቅረጽ እና በተወሰኑ ናሙና ከተሞች ሥራ ላይ ማዋል፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | ኅብረተሰቡ የተሳተፈበትና ልማትን ማዕከል ያደረገ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ ወይም ማሳደጊያ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ማድረግና መተግበር | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br><br>ከተሞች ፍትሐዊ፣ ግልጽና አስተማማኝ የፋይናንስ /የበጀት/ ድጋፍ የሚያገኙበት ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በተለይ መሰረተ-ልማትን ከማስፋፋት አኳያ ከፌደራል መንግሥት ለከተሞች የሚደረጉ ድጋፎችን ግልፅና ወጥነት ባለው ሁኔታ ለመምራት የፋይናንስ ድጋፍ ማስተላለፊያ ፖሊሲ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ክልሎች ለከተሞቻቸው የፋይናንስ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችላቸውን ቀመር ለማዘጋጀት የሚረዳቸው የገንዘብ አደላደል አጠቃላይ መመሪያ ወይም ናሙና ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በክልሎችና በከተሞች መካከል የገቢና የወጪ የፋይናንስ ኃላፊነቶችን በአግባቡ በመለየት ክልሎች ለከተሞቻቸው እንደ ሁኔታው የተለያዩ /ጥቅል፤ በዓላማ የተገደበ ወዘተ../ የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጡበትን ቀመር አሻሽለው እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በክልሎች የተዘጋጀው የከተሞች የሃብት ክፍፍል ቀመር እንዲተገበር ማድረግ፡፡ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br><br>የታክስ ሥርዓቱ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ የሚያደርቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የታክስ አሰባሰብና አስተዳደር የተሟላ የሕግ ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በከተሞች ፍትሃዊና ውጤታማ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠር፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3 | በከተሞች የታክስ ሥርዓቱን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ የሚችል፣ የሚያስተዳድርና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ ሥነ-ግባሩ የተጠበቀ የሰው ኃይል ማፍራት፣ | ገኢልሚሐሥክልሚ | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 4 | የታክስ ሥርዓት ማሻሻያውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ፣ | ገኢልሚ | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 5 | የግብር አወሳሰን ሂደትን አስመልክቶ ግልፅነት እንዲፈጠር እና ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ እንደሆነ የአመራሩን፣ የባለሞያውንና የሕዝቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎችን መስራት፣ | ክልልሐከተማ | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | |
| 6 | የታክስ አወሳሰንና አስተዳደር ሥርዓት አስፈፃሚ ባለሞያዎች የሥነጠምግባር ደንብ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| **የፋይናንስ አስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አንድ**<br><br>በከተማ አስተዳደሮች በሕግ፣ ደንብና መመሪያዎች የሚመራ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ክልሎች የከተሞቻቸውን ኃላፊነትና ተግባራት፣ ተጠያቂነትን እና የሃብት አጠቃቀምን ግልጽ የሚያደርጉበትና የሚመሩበት የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች ከአገር አቀፍ ደንብና መመሪያ ጋር በማጣጣም ማውጣትና በከተሞች ተግባራዊ የሚሆኑበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ | ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በፌደራልና በክልሎች ደረጃ የወጡትን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግና ከከተሞች አደረጃጀት ጋር በተጣጣመ መልኩ ከተሞች የሚመሩበትን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ ማውጣት፣ ማጽደቅና ተግባራዊ ማድረግ፣ | ገኢልሚ/ሥክልሚ/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 3 | የከተሞች ማቋቋሚያ አዋጆች በክልልና በከተማ አስተዳደሮች መካከል ያሉትን ፋይናንስ ነክ ኃላፊነቶች ግልጽ ባደረገ መልኩ እንደገና እንዲፈተሹ ማድረግ፣ | ገኢልሚ/ሥክልሚ/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | |
| 4 | በፌደራልና በክልል የወጡትን ወጥነት ያላቸው ስታንዳርድ የጨረታ ግዥ የመወዳደሪያ ሰነዶች /standard Bid Document/ ለከተሞች በሚሆን መልኩ አጣጥሞ ማዘጋጀትና ተግባር ላይ ማዋል፣ | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 5 | በከተሞች የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ እና ስታንዳርድ የጨረታ ሰነዶች አፈፃፀምን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡ | ክልል | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| **ግብ ሁለት**<br><br>ከከተሞች ስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ የተቀናጀና ልማትን ማዕከል ያደረገ የከተሞች ፋይናንስ ዕቅድ አሠራር ሥርዓት በከተሞች ይዘረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ለከተሞች የተዘጋጁትን የፋይናንስ ዕቅድ አዘገጃጀት ማንዋሎችን መሠረት በማድረግ ከተሞች የመካከለኛ ጊዜ የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ እንዲያዘጋጁና ይህንንም ለዓመታዊ የበጀት ዝግጅት መነሻ በማድረግ በከተማ ምክር ቤት እንዲያፀድቁ ማድረግ፣ | ክልል/ከተማ | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የከተማው ነዋሪ ኅብረተሰብ /በተለይም ሴቶች፣ ወጣቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ወ.ዘ.ተ. /በልማት ኘሮጀክቶች ወይም በካፒታል የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ችግሮችንና ፍላጐቶችን ከመለየትና ቅደም ተከተል ከማውጣት አኳያ በንቃት እና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚሳተፉበትን ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና ይህንንም ለመተግበር የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | አሠራር ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈጻጸም መከታተል፣ መገምገም እና የማጠናከሪያ እርምጃዎችን መውሰድ፣ | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በወጪ ማዕከላት ላይ የተመሠረተ እና የተጠቃለለ የከተሞች የበጀት አሠራር እንዲኖር የሚያደርግ የበጀት አወቃቀር ሥርዓት መዘርጋት እና ከፌደራልና ከክልሎች ጋር የተጣጣመ የከተሞች የበጀት አሠራር ማንዋል አዘጋጅቶ ማሰራጨት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የበጀት ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈፃፀም መከታተል፣ መገምገም እና የማጠናከሪያ እርምጃ መውሰድ:::: | ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br><br>ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ ሥርዓት በመዘርጋት ብክነትን የሚከላከል የግዥ፣ የንብረት አስተዳደር እና አወጋገድ ሥርዓት በከተሞች እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የከተሞች የአገልግሎት አጠቃቀም /የነዳጅ፣ መኪና ጥገና፣ የጽሕፈት መሣሪያ፣ ወዘተ./ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ ኖርሞችንና የውስጥ አሠራር መመሪያ ማዘጋጀት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ወጪ ቆጣቢ ሥርዓቱን ለማጠናከር በሦስተኛ ወገን ሊሰጡ የሚችሉትን የአገልግሎት ዓይነቶችን መለየት፣ ለዚህም ከቅልጥፍና፣ ከውጤታማነትና ከዋጋቸው አንፃር አዋጭነታቸውን ለማወቅ፣ ሥራውን ለማከናወን የተደራጀ የፋይናንስና የቴክኒክ ብቃት ያላቸው ተዋዋይ ድርጅቶች መኖራቸውን እና የመሳሰሉትን ለመለየት የሚረዱ መመዘኛዎችን የያዘ መመሪያ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | ከተሞች ያላቸውን ውስን ሀብት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንዲችሉ በየደረጃው ላሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የግንዛቤ ማዳበሪያ ዓውደ ጥናቶችና ሴሚናሮችን በማዘጋጀት የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በአጠቃቀም ሂደት ለብክነት የሚጋለጡ ወጪዎችን በየጊዜው በመፈተሽና በመገምገም ወጪ ቆጣቢ ሥርዓቱን ማስተካከል፡፡ | ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አራት**<br><br>በከተሞች ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ ግልጽና ትክክለኛ የሂሣብ መግለጫ ማቅረብ የሚያስችል የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | ለከተሞች በመዘጋጀት ላይ ያለው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ የገቢና የወጪ መደብ /Chart of Accounts/ እና የአሠራር ማኑዋል፣ በፌደራልና በክልል ካለው የአሠራር ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ እንዲጠናቀቅ ማድረግና ማሰራጨት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 2 | በየደረጃው ለሚገኙ የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ስለ ሂሣብ አያያዝ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር/ዐውደ ጥናት ማካሄድ፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | ■ | | | | | | | | | |
| 3 | ከተሞች ያለፉትን ዓመታት ሂሣባቸውን ዘግተው በማጠናቀቅ ለኦዲት የሂሣብ አሠራር ዝግጅት እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ | ክልል | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ |
| 4 | የሂሣብ አሠራሩን ከነጠላ ሂሣብ አመዘጋገብ /single Entry/ ወደ ድርብ የሂሣብ አመዘጋገብ /Double Entry/ ሥርዓት መቀየር፣ | ክልል/ከተማ | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 5 | የከተማው የሂሣብ አያያዝ /የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተቀላጠፈና ወጪ ቆጣቢ አሠራር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የአንድ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል /Single Pool/ የአሠራር ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋል፣ | ከተማ | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 6 | የሂሣብ አያያዝ ማሻሻያ ኘሮግራሙ በአግባቡ መተግበሩን በየደረጃው መከታተልና መገምገም፡፡ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| **ግብ አምስት**<br>በየደረጃው በከተሞች ግልፅ እና ወጥነት ያለው የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ የተደረገውን የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ማሻሻያ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ለከተሞች መመሪያዎችንና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ ማፀደቅ፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 2 | የነጠላ የትሬዠሪ የባንክ ሂሣብ አሠራርን /Single treasury Account/ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሠራር መመሪያ አዘጋጅቶ የባንክ አገልግሎት ባላቸው ከተሞች በሥራ ላይ ማዋል፣ | ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 3 | የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈጻጸም ማሻሻያ ፕሮግራምን አፈፃፀም መከታተል፣ መገምገም እና ለቀጣይ ተግባራዊነቱም ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፡፡ | ክልል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| **ግብ ስድስት**<br>የከተሞች ሃብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆጣጠር እና በየደረጃው ያለውን አካል ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የተጠናከረ የውስጥና የውጪ ኦዲት /ቁጥጥር ሥርዓት/ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጀውን የኦዲት መመሪያና የአሠራር ማንዋል ለከተሞች እንደሚሆን አጣጥሞ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 2 | ለከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች በውስጥ ኦዲት አደረጃጀትና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3 | ከተሞች ሂሣባቸውን በወቅቱ በመዝጋት የውጭ ኦዲተር ቀጥረው እንዲያስመረምሩ ለማድረግ የሚያስችልና አስፈላጊውን በጀት የሚመድቡበትን የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ | ክልል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 4 | ከተሞች የተጠናከረ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲችሉ የየክልሉ ኦዲት ቢሮዎች ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣ | ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| 5 | በውጭ ኦዲተሮች የተዘጋጀው የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት በወቅቱ ለከተማው ም/ቤት የሚቀርብበትን የአሠራር ሥርዓትና በውጭ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተጠቀሱ የማሻሻያ እርምጃዎችን እና በከተማው ም/ቤት የሚሰጡ አስተያየቶችን በወቅቱ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ | ክልል/ከተማ | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 6 | በመርሃ ግብሩ ዓመታት በናሙና ከተሞች ውስጥ የክንዋኔ ኦዲት ሙከራ ማድረግ፣ የኦዲት ማሻሻያ ፕሮግራም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን መከታተልና መገምገም፡፡ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ |
| **ግብ ሰባት**<br>በወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ይሻሻላል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ያለበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚረዳ የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ማከናወን፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በዳሰሳ ጥናቱ የተገኙትን እጥረቶች ለመቅረፍና የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት መለየት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 3 | የአፈፃፀም መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | ክልል/ከተማ | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | |
| **የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አንድ**<br>በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻያዎች በብቃት ተግባራዊ የሚያደርግ በቂ የሰው ኃይል ይሰለጥናል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና እና መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 2 | ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በታሪፍ ደንብና መመሪያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 3 | ለ4320 የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 4 | ለ4320 ባለሙያዎች በበጀት አዘገጃጀት ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 5 | 4320 ለሚሆኑና በ432 ከተሞች ለሚገኙ የሂሣብ ባለሞያዎች በሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 6 | 4320 ለሚሆኑ ባለሞያዎች በጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ አፈፃፀም ማሻሻያ ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 7 | ለ864 ኦዲተሮች የፋይናንስና የክንዋኔ ኦዲት ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 8 | 2160 ለሚሆኑና በ432 ከተሞች ለሚገኙ በገቢ አሰባሰብ ለተሰማሩ ሠራተኞች በገቢ አስተዳደር ሥርዓት ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ ለዚህም የሚያገለግሉ ማንዋሎችንና አሰልጣኞችን ማዘጋጀት፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | በ42 ከተሞች ለሚገኙ 168 ለሂሣብ እና የበጀት ባለሞያዎች፣ ገቢ ሰብሳቢዎችና ኦዲተሮች በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅት፣ የሂሣብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ላይ በተግባር የተደገፈ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት፣ | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 10 | በየከተማው በሚገኙ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የፋይናንስ ባለሙያዎች እና ጽ/ቤቶቹን በበላይነት ለሚያስተዳድሩ የቦርድ አባላት አሰልጣኞችን በመለየት እንደአግባብነቱ በፕሮጀክት ሰነድ እና በቢዝነስ ዕቅድ /Business Plan/ አዘገጃጀት፣ የሂሣብ አያያዝ እና በገቢ አስተዳደር ላይ 10 ቀናት ስልጠና መስጠት፡፡ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br><br>በየደረጃው በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ፣ የበጀት ዝግጅት፣ የሂሣብ አያያዝ እና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ አሠራሩ ዘመናዊና የፋይናንስ የመረጃ ፍሰቱም ቀልጣፋ ይሆናል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በከተሞች የኮምፒዩተር መረጃ መረብ እንዲዘረጋ ማድረግ፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 2 | የተዘጋጀውን የኮምፒዩተር አሠራር ሥርዓት ለመተግበር የሚረዳ የአጠቃቀም ማንዋል እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ | ገኢ.ልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3 | የማሻሻያ ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች የኮምፒዩተር እና ሌሎች ተጓዳኝ ዕቃዎች የፍላጐት ጥናት ማካሄድ፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 4 | ቀደም ሲል በፌዴራል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና በየክልሉ የፋይናንስ ቢሮዎች ውስጥ የተቋቋሙትን የኮምፒዩተር አሠራር ድጋፍ ሰጪ ዩኒቶች እንዲጠናከሩና ለከተሞች ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | |
| 5 | የኮምፒዩተር ፕሮግራም በሚዘረጋባቸው ከተሞች ሁለገብ የኮምፒዩተር ባለሙያ እንዲኖር ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 6 | ስለማሻሻያ ፕሮግራሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር ለኃላፊዎች እንዲሰጥ ማድረግ፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 7 | የማሻሻያ ፕሮግራሙን በቅድሚያ በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች፣ በመቀጠልም በየደረጃው በሌሎች ከተሞች መዘርጋትና አፈፃፀሙን መከታተል። | ክልል | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br><br>በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር፣ የገቢና የንብረት አስተዳደር እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሥራ ሂደት ለውጥን መሰረት ያደረጉ አደረጃጀቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ የተሻሉ ልምዶችን መቀመር እና የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ፣ | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 2 | በከተሞች የገቢ አሰባሰብና የገቢ አቅምን ከማሳደግ አኳያ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ የተሻሉ ልምዶችን መቀመር እና የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ። | ገኢልሚ/ሥከልሚ/ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በከተሞች የገቢ አቅምን ከማሳደግ አኳያ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ የተሻሉ ልምዶችን መቀመር እና የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ፣ | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 4 | በዚሁ መሠረት ጠንካራ አደረጃጀቶች መፈጠራቸውን ማረጋገጥ። | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |

## የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የከተማ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| **ግብ አንድ**<br><br>**የከተሞችና የቀበሌ ምክር ቤቶችን ግልፅነትና ወጥነት ባለው ሥርዓት ለመምራት፣ አባላቱም ኃላፊነታውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው የምክር ቤት የአሠራርና የአባላት የሥነ ምግባር ደንብ ጸድቆ ተግባራዊ ይሆናል፡፡** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በፌደራል የተዘጋጀውን ሞዴል የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንቦች ክልሎች እንደየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አሻሽለው እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | በክልሎች የተዘጋጁትን የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንቦች በክልል ምክር ቤቶች ማፀደቅና ተግባራዊ ማድረግ፣ | ክልል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 3 | በክልሎች የተዘጋጁትን የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሁለት**<br><br>**20000 የከተማ ምክር ቤት አባላት በየክልሉ የመንግሥት ሥራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋማት በከተማ ሥራ አመራር፣ በመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በአመራር ክህሎት ይሰለጥናሉ፡፡** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅት ማጠናቀቅ፣ | ፌደራል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | የአሰልጣኞች ምልመላ ማከናወንና የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ | ፌደራል/ክልል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 3 | የምክር ቤት አባላት የስለጠና መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ ስልጠናውን መስጠት፣ | ክልል | | | | | | ■ | | | ■ | | | | | | | |
| 4 | ስልጠናው በተገቢው የጥራት ደረጃ መካሄዱን መከታተልና መደገፍ፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | | ■ | | | ■ | | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br><br>**በየደረጃው ለሚገኙ የምክር ቤት አባላትና በምክር ቤቶች ለሚቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎች በከተማ ጉዳዮች ላይ የተሻለ ግንዛቤና የተሳትፎ አቅም እንዲኖራቸው እንዲሁም ከኃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ በሚገናኙ ጉዳዮች የተለያዩ ሥልጠና በመስጠት ተሳትፎአቸው ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል፡፡** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | በከተሞች ምክር ቤቶች የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም እና ምክር ቤቶቹ ሕጎችን የማውጣትና የሚወጡትን ሕጎች አፈጻጸም በአግባቡ እንዲከታተሉ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣<br>▪ የበጀት ኮሚቴ፣ የመሠረተ ልማት ኮሚቴ፣ የከተማ ቦታና ቤት ልማት ኮሚቴ፣ የቅሬታ ሰሚና የፀረ-ሙስና ኮሚቴ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ኮሚቴ፣ የትምህርት ኮሚቴ፣ የጤና ጥበቃና አደጋ መከላከል ኮሚቴ፣ የገጠር ቀበሌዎች ጉዳይ ኮሚቴ። | ክልል/ከተማ | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 2 | በቀበሌ ምክር ቤቶች የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም እና ኮሚቴዎቹ የተቋቋሙበትን ዓላማ እንዲያሳኩ ስልጠናዎችን መስጠት፣<br>▪ የበጀት ኮሚቴ፣ የአካባቢ ልማት፣ የከተማ ቦታና ቤቶች ጉዳይ ኮሚቴ፣ የባሕል የማኅበራዊና አደጋ መከላከል ኮሚቴ፣ ቅሬታ ሰሚና የሥነ-ምግባር ኮሚቴ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ኮሚቴ፣ የትምህርት ኮሚቴ፣ የጤና ጉዳዮች፣ የአካባቢ ጥበቃ ውበትና የከተማ ግብርና ኮሚቴ፣ የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ እና የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ። | ክልል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | |
| ግብ አራት<br>በከተሞች የሕዝብ ተሳትፎን ለማጠናከር የተለያዩ የሕብረተሰብ አካላትን አመኔታ ያገኙ አሳታፊ አደረጃጀቶችና መድረኮች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ለማድረግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎን በአግባቡ አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎ ማንዋል/ መመሪያ ይዘጋጃል፣ ጸድቆ ተግባራዊ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ለልማት፣ ለማኅበራዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ንቅናቄ ለመፍጠርና የቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎን በተቃና ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣ | ክልል/ከተማ | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 3 | ወጣቶችና ሴቶች በብዙሃን ማኅበራት መታቀፍ የወል ጥቅምንና መብትን ለማስከበር ወሳኝ መሆኑን ተረድተው በወጣቶችና በሴቶች ማኅበራት እንዲደራጁ የማሳወቅና የቅስቀሳ ስራዎችን ማከናወን፣ | ክልል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በቀበሌዎች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ከነዋሪዎች የተውጣጡ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከኃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ በሚገናኙ ጉዳዮች ላይ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ማድረግ፣<br>• የአካባቢ ጥበቃና ፅዳት ኮሚቴ ማቋቋም<br>• የአካባቢ ማሻሻያ ሥራዎች ኮሚቴ ማቋቋም<br>• የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ኮሚቴ ማቋቋም<br>• የፀጥታና ሕገ ወጥነትን የመከላከል ኮሚቴ ማቋቋም | ከተማ | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | የከተማ ነዋሪውን ወሳኝ በሆኑ የከተማ ጉዳዮች ላይ በግንባር ለማነጋገር የሚያስችሉ ሕዝባዊ ኮንፍረንሶችን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ማካሄድ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | በከተማ መሪ ኘላን፣ በከተማ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዙሪያ በተለይ ከፍተኛ ወጪን በሚያስከትሉ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ቅደም ተከተል ላይ የተለያዩ የኀብረተሰብ አካላት በየደረጃው እንዲመክሩበት ማድረግ፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ዕድሮች፣ ከግሉ ዘርፍ፣ ከብዙሃን ማኅበራትና ከሞያ ማኅበራት የከተማ አስተዳደር የጋራ የትብብር መድረክ መመስረትና ቋሚ የምክክር መርሃ-ግብር ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | የአካባቢ ማሻሻያ ኘሮጀክቶች ነዋሪው በተለይም ተጠቃሚው የተለያዩ አግባቦችን በመጠቀም አቅምን ባገናዘበ መልኩና በፍቃደኝነት ላይ ተመርክዞ ወጪን እንዲጋራ በማድረግ ተሳትፎውን ማጎልበት፣ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | የግሉ ሴክተር በከተሞች የተለያዩ ብቁና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን በመስጠት ተሳታፊ እንዲሆን አዋጪ የሆኑ የከተማ አገልግሎቶችን ለግሉ ሴክተር outsource ማድረግ፡፡ | ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | **የአስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ አንድ**<br>የከተማ መልካም አስተዳደር ፕሮግራምንና የከተማ ልማት ፕሮግራምን ውጤታማ በሆነ መልኩ ከማስፈፀም አኳያ ከተሞች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ የሚጠቀሙባቸው የከተማ አስተዳደር የሥራ ሂደቶች ይፈጠራሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | እስካሁን ከተደረገው እንቅስቃሴ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን ተሞክሮዎች መዳሰስና ምርጥ ልምዶችን በመቀመር ማስተላለፍ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | በፌደራል ደረጃና በክልሎች የተለዩ የሥራ ሂደቶችን የማቀራረብና ተደጋጋፊ የማድረግ ተግባራትን ማከናወን፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የተጠኑት ጥናቶች ሳይሸራረፉ ወጥና የተሟላ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ክትትልና ድጋፍ መስጠት፡፡ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| **ግብ ሁለት**<br>የከተሞች አደረጃጀት ሞዴል የሕግ ማዕቀፍ ለማስፈፀም የሚረዱ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የከተሞች አደረጃጀት ሞዴል የሕግ ማዕቀፍ የአፈፃፀም መመሪያዎች ክፍተቶችን በመለየት የአፈፃፀም ስልትና ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ሞዴል መመሪያዎችን ዐውደጥናት በማዘጋጀት ሀገራዊ ልምዶች እንዲዳሰሱና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በውይይት የዳበሩትን ሞዴል መመሪያዎች ለክልሎች መላክና ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ መስጠት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የአፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሦስት**<br>የከተሞች የትብብር ግንኙነት ማጠናከሪያ ቋሚ መድረክ እና የከተሞች ቀን ይመሠረታል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም የታቀፉ ከተሞች መስራችነት ሌሎች አባላትን በየደረጃው እየጨመረና ግንኙነቱን እያጠናከረ የሚመጣ የግኑኙነት መድረክ አደረጃጀትና አሠራር ጥናት ማጠናቀቅና ማፅደቅ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ከክልሎችና ከተሞች ጋር ውይይት ማድረግና መግባባት ላይ መድረስ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የመድረኩ ጽ/ቤት በሚፈለገው የሰው ኃይል፣ ቢሮና ማቴሪያል እንዲሟላ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በከተማ ልማት ዘርፍ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችንና የተገኙ ውጤቶችን የሚዘግብ አመታዊ መጽሔት (State of Ethiopian Cities) ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ | የትብብር መድረክ ጽ/ቤት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን አከባበር መነሻ ጥናታዊ ሰነድ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | በዚሁ መነሻ ሰነድ መሠረት የከተሞች ቀን አፈፃፀም ዕቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድርግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | በክልሎችና በከተሞች መካከል የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ትግበራ ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው የሚሸለሙበትና ለሌላው አርዓያ የሚሆን ሥራቸው የሚቀርብበት ሥርዓት መዘርጋት፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| **ግብ አራት**<br>ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ፣ የፖሊሲና ፕሮግራም ሃሣቦችን ለማመንጨት የሚያስችሉ የከተማ መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ ይደራጃሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በከተማ ልማት ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ዋና ዋና ተቋማትን የመረጃ ፍላጐት ማጥናት፣ የሚፈለጉ መረጃዎችን መለየት፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | አግባብነት ባላቸው የፌዴራልና የክልል መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙትን የከተማ ልማትን የሚመለከቱ የመረጃ ሃብቶች ማሰባሰብና በዘመናዊ መንገድ ማደራጀት፣ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | መረጃዎችን ወቅታዊ ለማድረግ፣ ለተጠቃሚዎች ሳይዛቡና ሳይፋለሱ በቀላሉ ለማድረስ የሚያስችል የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፡፡ | ፌደራል/ክልል/ከተማ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ አምስት**<br>የከተማ ሥራ አመራር ባለሞያዎችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት የከተማ ሥራ አመራር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የባለሞያ አቅርቦት በጥራትና በመጠን ተሻሽሎ ውጤታማ ይሆናል፣ በከተማ ሥራ አመራር በድህረ ምረቃ ኘሮግራም የማሰልጠን አቅም በዓመት ወደ አንድ ሺህ ያድጋል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የስልጠና ፕሮግራሙ ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የሥልጠና ዕቅድ መሠረት እየተከናወነና ጥራቱም የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ክትትልና የአፈፃፀም ድጋፍ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የተሳታፊዎች ምልመላ በጥንቃቄ ወቅቱን ጠብቆ መከናወኑን ማረጋገጥ፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በፕሮግራሙ የሰለጠኑ ተመራቂዎች በከተሞች አግባብ ባላቸው የሥራ ቦታዎች ላይ ተመድበው እያገለገሉ መሆኑን መከታተል፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ሥልጠናው በሥራ ላይ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ መገምገም፣ | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የስልጠውን ጥራት ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎች መውሰድ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ስድስት**<br>የ450 የከተማ አስተዳደር ፣ የማዘጋጃ ቤት ከተሞችና ታዳጊ ከተሞች 6000 የከተማ አሰተዳደር አስፈጻሚ አካላት የሥራ አመራር ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በከተማ ልማት ፖሊሲ፣ በከተሞች የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅና በመልካም አስተዳደር ፕሮግራም፡ እንዲሁም በስትራቴጂክ ዕቅድ ዝገጅት፣ በአመራር አሰጣጥና ማስተባበር (Leadership) በኘሮጀክት ማኔጅመንት፣ የኮንትራት አስተዳደር፣ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ አጋርነትን መምራት፣ በአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት በተከታታይ ዙሮች አጫጭር ሥልጠና ይወስዳሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | የሥልጠና ዕቅድ ማዘጋጀትና እንዲፀድቅ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ስትራቴጂው በከተማና በቀበሌ በየደረጃው የሚገኙ የሥራ አመራር አካላት የውሳኔ አሠጣጥ፣ የማስተባበርና የመምራት ክህሎታቸውን የሚያሳድጉ ፣ ክልልና ከተሞች የሚገኙ የተለያዩ ሴክተሮችን ለሚመሩ አካላት በተቀናጀ የከተማ ስትራቴጂክ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ተመሳሳይ ቀኝት እንዲኖራቸው፣ እና ሲቪል ሰርቪሱን ለለውጥ የሚያንቀሳቅሱበትና አመለካከቱን በሚፈለገው አቅጣጫ እንዲሆን የሚያግዙ የስልጠና ዓይነቶችን በዋናነት እንዲያካትት ማድረግ። | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የሥልጠና ማንዋሎች ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የአሰልጣኞች ስልጠና ማዘጋጀትና መስጠት፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 5 | አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 6 | ወቅታዊ የተሃድሶ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማመቻቸት። | ፌደራል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ሰባት**<br>በማሠልጠኛ ተቋማት ገብተው መሣተፍ እድል ያላገኙና በክልልና ከተማ አስተዳደሮች በተለያዩ የሙያ መስክ በማገልገል ላይ ለሚገኙ 12000 ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖች በከተማ ሥራ አመራር የአጭርና ረጅም ጊዜ የርቀት ትምህርት ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የስልጠና ስትራተጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | ከክልል ቢሮዎች ማሠልጠኛ ተቋማትና ተጠቃሚዎች ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር፣ | | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 3 | የሥልጠና ካሪኩለምና ኘሮግራም ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 4 | ሥልጠናውን የሚያግዝ ተቋማዊ አደረጃጀት ማስተካከል፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 5 | የሠልጣኞች ምርጫ መመዘኛ ማዘጋጀትና ምልመላ ማካሄድ፣ | ፌደራል | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | |
| 6 | የሥልጠና አፈጻጸም ሂደት ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| 7 | የተሃድሶ ስልጠና በማመቻቸት የአቅም ግንባታውን ሥራ ቀጣይነት ማረጋገጥ፣ | ፌደራል | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ |
| 8 | ሥልጠናው በሥራ ላይ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ መገምገም። | ፌደራል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ግብ ስምንት**<br>የከተማ ልማት ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ ዝግጅት ይጠናቀቃል፣ ይፀድቃል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በረቂቅ ስትራቴጂው ላይ ከበላይ አመራሩ ጋር ውይይት በማድረግ የጋራ ግንዛቤና አቅጣጫ መያዝ፣ | ፌደራል | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | |

| | ዝርዝር ተግባራት | ፈፃሚ አካል | 2001 | | | | 2002 | | | | 2003 | | | | 2004 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ስትራተጂው በሀገራችን በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ እየታየ ያለውን ዕድገት ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 3 | በረቂቅ ስትራቴጂው ላይ ከባለሞያዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | ■ | | | | | | | | | |
| 4 | ሀገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ማዘጋጀትና ከክልሎች ጋር የጋራ ግንዛቤ መያዝ፣ | ፌደራል | | | | | | | | ■ | | | | | | | | |
| 5 | የመጨረሻውን ረቂቅ ማዘጋጀትና እንዲፀድቅ ማድረግ፡፡ | ፌደራል | | | | | | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የፍትሕ ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ አንድ**<br><br>በከተሞች የሚወጡ ሕጎች የሚፈለገውን ልማት ለማምጣት እንዲቻል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውን የሚያበረታቱ እንዲሆኑና የዜጎችን መብት እንዲያስከብሩ ይሻሻላሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ያልተማከለ የአስተዳደር መርህን መሠረት በማድረግ የከተሞች ማቋቋሚያና ሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንድምታ ያላቸውን ሕጎችን አግባብነት መፈተሽ፣ | ክልል | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| 2 | በክልልና በከተማ ደረጃ የወጡ አዋጆችን በክልልና በከተሞች ምክር ቤቶች እንደየአግባቡ ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላት በታዩ ማነቆዎችና በተዘጋጁ ረቂቆች ላይ አስተያየት እንዲሰጡባቸው ማድረግ፣ | ክልል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 3 | የተሻሻሉ የሕግ ረቂቆቹን ለሚመለከተው የከተማ ወይም የክልል መክር ቤት አቅርቦ ማፀደቅ፣ | ክልል/ከተማ | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 4 | የሕግ ሰነዶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡ | ክልል | | | | | | | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ | ■ |
| | **ግብ ሁለት**<br><br>በከተሞች የማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው ሥራ ይጀምራሉ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በከተሞች የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ሥራ በተመለከተ ያለውን ልምድ መቀመርና ለሌሎች ከተሞች ስለሚተላለፍበት ስልት መቀየስ፥ | ፌደራል/ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የማህበራዊ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብን ረቂቅ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል | | | | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 3 | በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ክልሎች፣ ከተሞች፣ አግባብነት ያላቸው አካላትና ባለሞያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 4 | በተገኘው አስተያየት መሠረት ረቂቁን በማዳበርና በማዘጋጀት ለክልሎች ማሠራጨት፣ | ፌደራል | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 5 | ደንቡ በክልሎች/በከተሞች እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ | ፌደራል | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | |
| 6 | ፍርድ ቤቶቹ ተደራጅተው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠት፡፡ | ፌደራል/ክልል | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | |
| | **ግብ ሦስት**<br><br>በከተሞች የደንብ ማስከበር አገልግሎት ይበልጥ ይጠናከራል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | በከተሞች የደንብ ማስከበር አገልግሎት ሥራን በተመለከተ ያለውን ልምድ መቀመርና ለሌሎች ከተሞች ስለሚተላለፍበት ስልት መቀየስ፣ | ፌደራል/ክልል | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |

| | | |
|---|---|---|
| 2 | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የከተሞች የደንብ ማስከበር አገልግሎት ማቋቋሚያ ደንብ ረቂቅ ማዘጋጀት፣ | ፌደራል/ክልል |
| 3 | በረቂቅ ደንቡ ላይ ክልሎች፣ የከተማ አስተዳደሮች አግባብነት ያላቸው አካላትና ባለሞያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣ | ፌደራል |
| 4 | በተገኘው አስተያየት መሠረት ረቂቁን በማዳበር ሞዴል ደንቡን ለክልሎች ማሠራጨት፣ | ፌደራል |
| 5 | ደንቡ በክልሎች/በከተሞች እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ | ፌደራል |
| 6 | የደንብ ማስከበር አገልግሎቶቹ ተደራጅተው ሥራ እንዲጀምሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ መስጠት፡፡ | ፌደራል/ክልል |
| **ግብ አራት**<br><br>የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ የደንብ አስከባሪ አካላት እና የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በማድረግ ይሻሻላል፡፡ | | |
| 1 | የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤትን፣ የደንብ አስከባሪ አካላትን እና የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችንና የታዩ እጥረቶችን መገምገም፣ | ፌደራል |
| 2 | በእስካሁኑ ተሞክሮ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሙን ከማስፈፀም አኳያ በከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ በከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ በደንብ አስከባሪ አካላት እና በፖሊስ አገልግሎት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የታዩትን መልካም ተሞክሮዎች መቀመር፣ | ፌደራል/ክልል |
| 3 | የከተሞች የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ በከተሞች የከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ በደንብ አስከባሪ አካላት እና በፖሊስ አገልግሎት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተሻሉ የሥራ ሂደቶችን መቅረፅ፣ ተግግባራዊ ማድረግ፡፡ | ፌደራል/ክልል |
| **ግብ አምስት**<br><br>በከተማ አስተዳደር ሙስናን ለመከላከልና ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜም በቀላሉ ለይቶ በማውጣት የሕግ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ | | |
| 1 | በከተማ-ነክ ፍርድ ቤቶች ለሚገኙ ዳኞች፣ ለከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕጎች፣ ለፖሊስ እና ለሌሎች የፍትሕ አካላት በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚከሰቱ የሙስና ወንጀሎችን ለመመርመር፣ ለመክሰስና ለመዳኘት የሚያስላቸውን አቅም ለማጎልበት ተከታታይ ስልጠናዎችን መስጠት፣ | ክልል |
| 2 | በከተሞች ለፖለቲካ ተሿሚዎችና ለመንግሥት ሠራተኞች የሥነ ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ | ክልል |
| 3 | የከተማ-ነክ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የደንብ አስከባሪ አካላት፣ የአቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ባለሞያዎች እና ፖሊሶችን ተጠያቂነት ለማጠናከር የፍትሕ አካላት የሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ | ክልል |
| 4 | በከተሞች በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሥነ ምግባር ትምህርትን የሥርዓተ ትምህርቱ አካል ማድረግ፣ | ክልል |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ኅብረተሰቡን የፀረ ሙስና ዘመቻው አካል ለማድረግ በተለያዩ ሚድያዎች በመቀስቀስ የአመለካከት ለውጥና የተቆርቋሪነት ስሜት እንዲፈጠር ማድርግ፣ | ክልል/ከተማ |
| 6 | በክልል/ከተሞች ለሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ የሚከሰት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን የመመርመርና በአግባቡ የመዘገብ አቅማቸውን ለማሰደግ የምርመራ ጋዜጠኝነት /Investigative Journalism / ሥልጠና መስጠት፣ | ፌደራል/ክልል |
| 7 | ሕዝባዊ ማኅበራትና የተለያዩ የሞያ ማኅበራት በከተማ አስተዳደሮች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን በወኪሎቻቸው አማካይነት በከተሞች ምክር ቤቶች ለሚቋቋሙ የቅሬታ ሰሚና የፀረ-ሙስና ኮሚቴዎች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት መዘርጋት፣ | ክልል |
| 8 | በመንግሥት መ/ቤቶችና በመገናኛ ብዙሃን መካከል የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ | ክልል |
| **ግብ ስድስት**<br>የከተማ ሁለገብ የልማት መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ የሚሆኑበት ሥርዓትን በመዘርጋት ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የከተሞች አስተዳደር ይገነባል፡፡ | | |
| 1 | የከተሞች የስትራቴጂክ ዕቅድን፣ ዓመታዊ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን፣ የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎችን፣ የኦዲት ሪፖርቶችን፣ የጨረታ አሠራር ሂደቶችን የሚዘግቡ ሰነዶች፣ ለኢንቨስትመንት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን ያደራጁ አነስተኛ መፅሐፍት ቤቶች ማቋቋም፣ ወይም በሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ውሰጥ የተለየ ማዕዘን ይዘው እንዲደራጁ ማድረግ፣ | ከተማ |
| 2 | ለኢንቬስትመንት የሚያገለግሉ መረጃዎችንና የተለያዩ ደንቦችና መመሪዎችን ለፈላጊዎች የሚያቀርብ የሽያጭ መስኮት በከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች ማቋቋም፣ | ከተማ |
| 3 | በመንግስት ተቋማትና በቀበሌዎች ወቅታዊ የከተማ መረጃዎችን በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች በተቀመጡ የማስታወቂያ ሠሌዳዎች ላይ መለጠፍ፣ | ከተማ |
| 4 | በመንግስት ተቋማትና በቀበሌዎች የተገልጋዩን አስተያየት ማሰባሰቢያ ሳጥኖች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች በማስቀመጥ አስተያየቶችን በመሰብሰብ ጥቅም ላይ ማዋል | ከተማ |
| 5 | የተለያዩ ብዙሃን መገናኛን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎች ለነዋሪው እንዲያቀርቡ ማድረግና የሕዝቡን አስተያየቶችና ጥቆማዎችን መቀበል፣ | ከተማ |
| 6 | የተለያዩ የከተማ መረጃዎችን በኢንተርኔት መረብ ለማሰራጨት የሚረዳ የከተማ አስተዳደር ድረ-ገጽ መክፈት፡፡ | ከተማ |